ጣስ ፡ (ዝ) ፤ ባሬታ ፡ መክፈያ ፡ የሽንት ፡ የልባም ፡ መቀበያ ።

ጦስ ፤ (ፀወሰ ። ዕብ ፡ ጣሽ ፤ ተወ) ፤ በያይነቱ ፡ ውጥንቅጥ ፡ እኽል ፡ ቅቤም ፡ ሳይቀር ፤ ደንቃራ ፡ ቆርት ፡ በበሽተኛ ፡ ላይ ፡ አዙረው ፡ በመንገድ ፡ የሚጥሉት ፡ የሚተዉት ፤ ደዌን ፡ ከታ መመው ፡ ወዳልታመመው ፡ ማስተላለፊያ ፤ የረገጠው ፡ ልምሾ ፡ (ሽባ) ፡ ይኾናል ። በጉራጌ ፡ አገር ፡ ግን ፡ ቍጋ ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ ተቀብሎ ፡ ወስዶ ፡ ይበላዋል ።

ጦስ ፤ ሰበብ ፡ መዘዝ ፡ ምክንያት ።

ጦሰኛ ፡(ኞች) ፤ ባለጦስ ፡ ቆርተኛ ፡ ሰበበኛ ።

ጦስራኤል ፤ የቀበሌ ፡ ስም ፤ በላይ ፡ ወግዳ ፡ በስተምሥራቅ ፡ ያለ ፡ አፋፍና ፡ ገደል ፤ የእስራኤል ፡ መዘዝ ፡ ማለት ፡ ይመስላል ። ጕዲትን ፡ እይ ።

ጠሰጠሰ ፤ (ዕብ ፡ ጣሽጤሽ ፤ አጠፋ ፡ ደመሰሰ) ፤ (ተገብሮ) ፡ ፈጽሞ ፡ አረጀ ፡ አፈጀ ፡ (ኢዮ፲፫ ፡ ፳፰) ።

ጠሰጠሰ ፤ (ገቢር) ፡ መታ ፡ ደበደበ ። ጠዘጠዘን ፡ ተመልከት ።

ጥስጥስ ፤ የጠሰጠሰ ፡ አሮጌ ፡ ከብት ፡ ሰው ።

አንጠሰጠሰ ፤ ዐመሰ ፡ ቄላ ።

(ጦሸጦሸ) ፤ **አንጦሸጦሸ** ፤ አንጣጣ ፡ በተን ።


ማንጦሸጦሸ ፤ ማንጣጣት ፡ መበተን ።

ጦሽ ፡ አለ ፤ **(ዕብ ፡ ጣሽ ፤ በረረ)** ፤ ጮኸ ፡ ድምጥ ፡ ሰጠ ፡ እሳት ፡ የገባ ፡ ዕንጨት ፤ ተበተነ ፡ የፍም ።

ተንጦሸጦሸ ፤ ጦሸ ፡ ጦሸ ፡ አለ ፤ ተንጣጣ ።

መንጦሸጦሸ ፤ መንጣጣት ፡ መበተን ።

ጦስኛ ፤ (ጥስን) ፤ የቅጠል ፡ ስም ፤ ዐጪ



ጦስኛ ፡

ርና ፡ ቀጪን ፡ የሐረግ ፡ ዐይነት ፡ ቅጠል ፡ በዋና ፡ ደጋና ፡ በወይናደጋ ፡ የሚበቅል ፡ ሽታው ፡ የሚጥም ፡ የሚጣፍጥ ፡ ለወጥ ፡ ቅመም ፡ የሚኾን ። ሕፃናት ንም ፡ ትክትክ ፡ በያዛቸው ፡ ጊዜ ፡ እናቶቻቸው ፡ ከ ወተት ፡ ጋራ ፡ አፍልተው ፡ ያጠጧቸዋል ።

ጠሰቀ ፤ ጠረነቀ ፤ ብዙ ፡ በላ ፡ ወጠቀ ፡ ጠቀጠቀ ፡ እያረፈ ፡ እያሸራሸረ ።

ጠሰቀ ፤ በዱላ ፡ መታ ፡ ደሰቀ ።

ጠሳቂ ፤ የጠሰቀ ፡ የሚጠስቅ ፤ ወጣቂ ፡ ደሳቂ ።

መጠሰቅ ፤ መወጠቅ ፡ መደሰቅ ።

መጠሰቂያ መወጠቂያ ፡ መምቻ ፡ እጅ ፡ በትር ።

ተጠሰቀ ፤ ተወጠቀ ፡ ተጠቀጠቀ ።

ተጠሰቀ ፤ ተመታ ፡ ተደሰቀ ።

ጥስቅ ፤ የተጠሰቀ ፡ የጠገበ ፡ ሆድ ፤ ጥርንቅ ፡ ያለ ፡ ገላ ።

ጥስቅ ፡ አደረገ ፤ ሆዱን ፡ መላ ፡ አጠገበ ።

አጠሳሰቅ ፤ አወጣጠቅ ፤ መጠሰቅ ።

ጣሰሰ ፤ ጣሰ ፡ አወደቀ ።

መጣሰስ ፤ መጣስ ፡ ማውደቅ ።

ጡት ፤—በቁሙ ፤—ጠባ ፤ (ጠበወ) ።

ጣት ፡ (ቶች) ፤ የእጅና ፡ የእግር ፡ የመንሽ ፡ የሹካ ፡ ጫፍ ፤ ዐጽቅ ፡ ቅጥይ ፤ መያዣና ፡ መጨበጫ ። አውራ ፡ ጣት ፡ ሌባ ፡ ጣት ፡ መካከለኛ ፡ ጣት ፡ የቀለበት ፡ ጣት ፡ ታናሽ ፡ ጣት ፡ እንዲሉ ። ጣት ፡ የወጣት ፡ ከፈል ፡ ነው ፤ ምስጢሩም ፡ መውጣትንና ፡ በላይ ፡ መኾንን ፡ ያሳያል ። በግእዝም ፡ ፃት ፡ ይባላል ። (ተረት) ፤ ዘሩ ፡ የጣቱ ፤ ምድሩ ፡ ያባቱ ። በቄማጣ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ጣት ፡ ብርቅ ፡ ነው ።



ጣት ፡ ይጠባል ፤ ሕፃን ፡ ነው ፤ አላዋቂ ፡ ነው ።

ጣተ ፤ ጣትን ፡ አነሣ ፡ ቀሰረ ።

መጣት ፤ ማንሣት ፡ መቀሰር ።

ጢት ፤—ንጋት ፤—ጠባ ፤ (ጸብሐ) ።

ጢት ፤—የፊደል ፡ ስም ፡ ጠ ፤—ጠይት ።

ጨ

ጨ ፤ የጠ ፡ ዲቃላ ፤ የጸፀ ፡ ወራሽ ፡ ወይም ፡ ተለዋዋጭ ። (ማስረጃ) ፡ ጠመቀ ፡ ጨመቀ ፤ ጸቄን ፡ ጨቄን ፤ ፀረረ ፡ ጠረረ ፡ ጨረረ ፤ ፀርሰ ፡ ጨረሰ ። እንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ የቀ ፡ ወራሽ ፡ ኹኖ ፡ ይገኛል ። ቂርቆስ ፡ ጨርቆስ ፤ ቃቂል ፡ ቃጭል ፤ እንቃቅላ ፡ እንጫጭላ ።

ጨ ፤ የጀ ፡ ተለዋዋጭ ። ጀጐለ ፡ ጨጐለ ።

ጨ ፤ የቸ ፡ ተወራራሽ ። ችሣኝ ፡ ጭጉኝ ።

ጫ ፡ አለ ፤—ዝም ፡ አለ ፤—(ጫጫ) ።

ጫ ፡ አለ ፤—ከሳ ፤—ጭው ።

ጨባ ፤ የዛፍ ፡ ስም ፤ ከሰል ፡ የሚኾን ፡ ዕንጨት ።

ጨቦ ፤ በጉራጌ ፡ አጠገብ ፡ ያለ ፡ አገር ።

ጭቤ ፤ አፋ ፡ ካራ ፡ ጉዶ ፡ ማረጃ ፡ ማወራረጃ ።

ጭባ ፤ ዐጪር ፡ ቀጪን ፡ ሰው ፡ ድንክ ።

ጭቦ ፤ እከይ ፡ ክፋት ፡ ልግም ፡ ሀኬት ።

ጭቦኛ ፡ (ኞች) ፤ እከየኛ ፡ ክፋተኛ ።

ጮባ ፤ በምንጃር ፡ በኩል ፡ ያለ ፡ አገር ፤ ትርጓሜው ፡ ጠብታ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ጮቤ ፤ ዝላይ ፡ መርታ ።

ጮቤ ፡ መታ ፤ ዘለለ ፡ መር ፡ መር ፡ አለ ፤ በእግሮቹ ፡ ተረከዝ ፡ ቂጡን ፡ መታ ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከጪቦ ፡ እስከ ፡ ጮቤ ፡ ያለው ፡ ጋልኛ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ዝምሮ ፡ ካማርኛ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ተቀላቀለና ፡ ስለ ፡ ተለመደ ፡ ተጻፈ ፤ ገጽ ፡ ፱፫ና ፡ ፱፩ ፡ እይ ።

ጨቦደ ፤ ጠበጠ ። ጨቦደ ፡ የባላገር ፤ ጠበጠ ፡ የከተማ ።

ጨቡዴ ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ጨባጭ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ጨቡድ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፡ ያዝ ፡ ጨብጥ ።

መጨቦድ ፤ መጨበጥ ።

ጨበጠ ፤ (ፀበጠ) ፤ ያዘ ፡ እጅ ፡ አደረገ ፡ (ምሳ፭ ፡ ፩) ። ነገሠን ፡ እይ ።

ጨበጠ ፤ ነፈገ ፡ አስወደደ ፤ የገበያ ።

ጨበጠ ፤ አድበለበለ ፡ ጭብጦ ፡ አበጀ ።

ጨበጠ ፤ እግርን ፡ ኰረመተ ።

ጨባጭ ፡ (ጮች) ፤ የጨበጠ ፡ የሚጨብጥ ፤ ያዥ ፡ ንፋግ ።

ጨበጣ ፤ ደንጊያን ፡ ጦርን ፡ መጨበጥ ፤ ሳይወረውሩ ፡ በዚያው ፡ ለመውገር ፡ ለመውጋት ። የደንጊያ ፡ ጨበጣ ፤ የጨበጣ ፡ ውግ ፡ እንዲሉ ።

ጨበጣ ፤ የማገር ፡ ስም ፤ በስተውስጥ ፡ በኩል ፡ ያለ ፡ የጣራ ፡ ማገር ፡ በእጅ ፡ እየተጨበጠ ፡ የሚታሰር ።

ጭበጣ ፤ የመጨበጥ ፡ ሥራ ፤ ይዘታ ።

ጨብጥ ፤ (ፀብጥ) ፤ የዕመም ፡ ስም ፤ የወንድን ፡ ብልት ፡ የሚያሳብጥ ፡ ጭብጦ ፡ የሚያስመስል ፡ ሽንት ፡ የሚከለክል ፡ የሴትን ፡ ማሕፀን ፡ የሚዘጋ ፡ መውለድን ፡ የሚነሣ ፡ ደዌ ፡ እዥም ፡ መግላም ። ጨብጥና ፡ ቂጥኝን ፡ በግራኝ ፡ ጊዜ ፡ ወዳጎራችን ፡ ያመጡ ፡ የፑርቱጌዝ ፡ ወታደሮች ፡ ናቸው ፡ ይባላል ።

ጨበጥ ፤ (ትግ) ፤ ልምጭ ፡ ጨንገር ።

መጨበጥ ፤ መያዝ ፡ መንፈግ ፡ ማስወደድ ፡ ማድበልበል ፡ መኰርመት ።

መጨበጫ ፤ መያዣ ፤ ማድበልበያ ፡ ውስጥ ፡ እጅ ፡ እጅታ ።

ጨባበጠ ፤ የጨበጠ ፡ ድርብ ፤ መላለሶ ፡ ጨበጠ ፡ ኰረማመተ ።

መጨባበጥ ፤ የመጨበጥ ፡ ድርብ ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መጨበጥ ፡ መኰረማመት ።

አስጨበጠ ፤(አፀበጠ) ፤ አሲያዘ ፡ እጅ ፡ አስደረገ ።

አስጨበጠ ፤ ጭብጦ ፡ አስበጀ ።

አስጨባጭ ፤ ያስጨበጠ ፡ የሚያስጨብጥ ፤ አሲያዥ ።

ማስጨበጥ ፤ ማሲያዝ ።

ተጨበጠ ፤ (ተፀብጠ) ፤ ተያዘ ፡ እሰው ፡ እጅ ፡ ገባ ።

ተጨበጠ ፤ ተወደደ ፡ ዋጋው ፡ በዛ ።

ተጨበጠ ፤ ተድበለበለ ፡ ጭብጦ ፡ ኾነ ።

ተጨበጠ ፤ ተኰረመተ ፡ እጁና ፡ እግሩ ፡ ሰውነቱ ።

ተጨባጭ ፤ የሚጨበጥ ፡ የሚያዝ ።

ጨባጣ ፤ ኰርማታ ፡ ደረቱና ፡ ጕልበቱ ፤ የገጠመ ።

(ጥብ) ጭብጥ ፤ የተጨበጠ ፡ ኵርሙም ፡ ቡጢ ፡ ጡጫ ፤ ባንድ ፡ እጅ ፡ የተያዘ ፤ ጥቂት ፡ (ኢሳ፵ ፡ ፲፪ ። ፩ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፪ ። ፳ ፡ ፲ ። ሕዝ፲፫ ፡ ፲፱) ። ጭብጥ ፡ ጥጥ ፡ ጭብጥ ፡ ሣር ፡ እንዲሉ ።

ጭብጥ ፡ አደረገ ፤ ያዝ ፡ አደረገ ፤ ጨበጠ ።

ጭብጥ ፡ አለ ፤ ኵርምት ፡ አለ ፤ ተጨበጠ ፤ ዐዘነ ።

(ላብ) ጭብጥ ፤ ከዳኛ ፡ ላስመስከረ ፡ የተሰጠ ፡ ቍርጥ ፡ ነገር ።

ጭብጥ ፡ አፈሰሰ ፤ ጭብጥን ፡ ለመስከረ ፡ ነገረ ፡ ገለጠ ፡ አስረዳ ።

ጭብጥ ፡ ቅጽል ፤ ይህ ፡ ይኸ ፡ እሊህ ፡ እለዚህ ፡ የሚባል ፡ የስም ፡ ምትክ ።

ጭብጦ ፡ (ዎች) ፤ ጭፍቆ ፡ ተጋግሮ ፡ ሳይበርድ ፡ ትኵሱን ፡ እንደ ፡ ጎብስት ፡ የተድበለበለ ፡ ክብ ፡ እንጀራ ፤ እንክብል ፡ ማርና ፡ በሶ ፡ ሽሚት ፡ የሻያጅ ፡ የመንገደኛ ፡ ሥንቅ ። (ተረት) ፤ አካኼዱን ፡ አይተሽ ፡ ጭብጦውን ፡ ቀማው ። ይኸ ፡ ኹሉ ፡ ግርግር ፡ የኔን ፡ ጭብጦ ፡ (ቂጣ) ፡ ለመቀማት ፡ ነው ፡ እንዲሉ ።

ተጫበጠ ፤ እጅ ፡ ለጅ ፡ ተያያዘ ፡ ተግናኘ ፤ ሰላምታ ፡ ተሰጣጠ ።

መጫበጥ ፤ መያያዝ ፡ መግናኘት ።

ተጨባበጠ ፤ ተኰረማመተ ።


ጭብጥብጥ ፤ የተጨባበጠ ፤ ኵርምትምት ።

ጭብጥብጥ ፡ አለ ፤ ኵርምትምት ፡ አለ ፤ ተጨባበጠ ።

መጨባበጥ ፤ መኰረማመት ።

አጫበጠ ፤(አስተፃበጠ) ፤ አያያዘ ፡ እጅ ፡ ለጅ ፡ አገናኘ ።

አማበጠ ፤ ጭብጦ ፣ አሳጀ ።
ማማበጥ ፤ ማያያዝ ፣ ማገናኘት ።
አጨባበጠ ፤ አኰረማመተ ።
ማጨባበጥ ፤ ማኰረማመት ።
አጨባበጥ ፤ አያያዝ ፤ መጨበጥ ።
ጨበጨበ ፤ (ትግ ፡ ጨብጨበ) ፤ አፈጠፈጠ ፣ አቈጠቈጠ ፤ ለመለመ ፣ ቅጠል ፣ አወጣ ፣ አጀፈጀፈ ፣ (ኢዮ፲፬ ፣ ፯ ፣ ፱ ። ማሕፄ ፣ ፲፫ ። ኢሳ ፳፯ ፣ ፯) ።
ጭብጭቦ ፤ የጨበጨበ ፤ ደፍጀር ፣ (ኢዮ ፲፬ ፣ ፯) ።
ጭብጭቦች ፤ ጀፍጀፎች ፣ ቅርንጫፎች ፣ (ኢዮ፲፭ ፣ ፴) ።
መጨብጨብ ፤ ማፈጥፈጥ ፣ ማቈጥቈጥ ፣ መለምለም ።
መጨብጨቢያ ፤ ማቈጥቈጫ ፣ መለምለሚያ ።
አጨበጨበ ፤ (ጠፍሐ) ፤ የቀኑንና ፣ የግራ ፣ ውስጥ ፣ እጁን ፣ እግታ ፤ ቸብ ፣ ቸብ ፣ አደረገ ፣ (ኢሳ፶፭ ፣ ፲፪ ። ሕዝ፮ ፣ ፲፭ ። ማቴ፲፭ ፣ ፲፯) ።
አጨብጫቢ ፡ (ቦች) ፤ ያጨበጨበ ፣ የሚያጨበጭብ ።
አጨብጫቢ ፤ የነገር ፣ ረዳት ፣ አዳማቂ ።
ማጨብጨብ ፤ እጅን ፣ ከእጅ ፣ ጋራ ፣ መጽፋት ።
ማጨብጨቢያ ፤ እጅ ፣ ዘፈን ፣ ማሕሌት ፣ ለቅሶ ፤ ሰሌዳ ፣ ጎዲን ። ፈረንጆች ፣ ሰምባል ፣ ይሉታል ።



ማጨብጨቢያ ፣

አስጨበጨበ ፤ አጨብጭቡ ፣ አለ ፤ ጭብጨባን ፣ አስተማረ ።
አስጨበጨበ ፤ ነገሩን ፣ ስብከቱን ፣ አስወደደ ፣ አስመሰገን ፣ በጭብጨባ ።
አስጨብጫቢ ፤ ያስጨበጨበ ፣ የሚያስጨበጭብ ፤ ዘፋኝ ፣ አልቃሽ ፣ ዛር ፣ ፈረስ ።
ማስጨብጨብ ፤ ቸብ ፣ ቸብ ፣ ማስደረግ ።
ማስጨብጨቢያ ፤ ስፍራና ፣ ጊዜ ።
ጭብጨባ ፤ የመጨብጨብ ፣ የማጨብጨብ ፣ ሥራ ፣ ችኖቱ ፣ የዘፈን ፣ የለቅሶ ፣ ማድመቂያ ።
ተጨበጨበ ፤ ኾነ ፣ ተደረገ ፣ ጭብጨባው ። እከሌ ፣ ስብቅል ፣ ነገር ፣ ስለ ፣ ተናገረ ፣ ተጨበጨበለት ።
አጨባጨበ ፤ ጭብጨባን ፣ ረዳ ፣ አስተባበረ ፣ አዳመቀ ።
ማጨባጨብ ፤ ማስተባበር ፣ ጭብጨባን ።
አጨባጨብ ፤ አለማለም ፤ መጨብጨብ ፣ ማጨብጨብ ።
ጨበረ ፤ (ፀመረ) ፤ ከጥቅረት ፣ ወደ ፣ ንጣት ፣ ተለወጠ ፤ ነጭ ፣ ኾነ ፤ ሌላ ፣ መልክ ፣ አመጣ ፣ ጨመረ ፤ (ሽበተ) ።
ጨበር ፡ (ሮች) ፤ ጸበል) ፤ ነጭ ፣ በቅሎ ፣ አስቀድሞ ፣ ዋርዳ ፣ የነበረ ። ግራማን ፣ እይ ።
ጨበርማ ፤ (ጸበላዊ) ፤ የጨበር ፣ ዐይነት ፣ ወገን ፤ ነጭነት ፣ የተነፋበት ፣ ዐመድማ ። ጨበርማ ፣ በቅሎ ፣ እንዲሉ ።
ጨበራይ ፤ (ትግ) ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ፤ ለእንስሳ ፣ ኹሉ ፣ ይነገራል ።
ጨበሬ ፤ ጨበራዊ ፤ ቀይ ፣ ዐፈር ፣ ቅላት ፣ ከብጣንት ፣ ያለው ፤ ድልኽማ ፣ ወርቅማ ፤ ዐይን ፣ አበባ ፣ መሬት ። ጠመንን ፣ ተመልከት ።
አጭበረበረ ፤ (ትግ ፡ ጠበረ ፤ አባበለ ፡ ሸነገለ) ፤ አጥበረበረ ፣ አንጸባረቀ ፤ እንደ ፣ ጨበሬ ፣ ዐይንን ፣ በዘበዘ ፤ ማየት ፣ ከለከለ ።
አጭበረበረ ፤ አታለለ ፣ አሳሳተ ፣ አደናገረ ፤ አላዋቂነቱን ፣ በመንቀፍ ፣ ሰወረ ። ጠበረን ፣ አስተውል ።
አጭበርባሪ ፡ (ሮች) ፤ ያጭበረበረ ፣ የሚያጭበረብር ፤ አሳሳች ፣ አደናጋሪ ። ገረዘ ፣ ብለኽ ፣ ገራዥን ፣ እይ ።
አጭበርባሪነት ፤ አጭበርባሪ ፣ መኾን ፤ አሳሳችነት ።
ማጭበርበር ፤ ማጥበርበር ፣ ማንጸባረቅ ፣ ማሳሳት ፣ ማደናገር ።
ማጭበርበሪያ ፤ ማሳሳቻ ፣ ማደናገሪያ ።
ተጭበረበረ ፤ እንደ ፣ ጉጉትና ፣ እንደ ፣ ሌት ፣ ወፍ ፣ ኾነ ፤ ብርሃን ፣ ማየት ፣ አቃተው ፤ ተሳነው ።
ተጭበረበረ ፤ አውነት ፣ እያለው ፣ የሌለው ፣ መሰለ ፤ ተሳሳተ ፣ ተደናገረ ።
ጭብርብር ፤ የተጭበረበረ ።
መጭበርበር ፤ መሳሳት ፣ መደናገር ።
መጭበርበሪያ ፤ መሳሳቻ ።
ጫብራ ፤ የዛፍ ፣ ስም ፤ በጣና ፣ ዳር ፣ የሚበቅል ፣ ዕንጨት ።
(ጨበረቀ) ፤ ጸብረቀ) ፤ ጭብርቅርቅ ፡ ብጭርቅርቅ ፡ አለ ፤ (አንያረረ) ፤ ተንሸዋረረ ፤ ሳይደምቅ ፡ ሳያምር ፡ ቀረ ፡ ዘፈኑ ፡ ማሕሌቱ ፡ አስተያየቱ ።

ጨበረረ ፤ (ጨፈረረ ፤ ጨረፈፈ) ፤ ደረቀ ፥ ቆመ ፥ የጎርት ፥ ወስፌ ፥ መሰለ ፤ የሸፍታ ፥ የናዝራዊ ፥ የሐዘነተኛ ፥ ያረመኔ ፥ ጠጮር ።

መጨብረር ፤ መድረቅ ፥ መቆም ።

አንጨበረረ ፤ አቃጠለ ፤ አደረቀ ፥ አቆመ ፥ አንጨፈረረ ።

እንጭብር ፤ ጭብር ፤ የታናሽ ፥ ቅጠል ፥ ስም ፤ ደሙ ፥ ቀይ ፥ ጨበሬ ፥ የሚመስል ፥ ሐረግ ፥ ቅጠለ ፥ ሻካራ ፤ ሥሩ ፥ ከቅቤ ፥ ጋራ ፥ ለሳል ፥ መድ ኀኒት ፥ ይኾናል ። እንጭብርና ፥ ምንጭርር ፥ አንድ ፥ ስም ፥ ነው ።

እንጭብሬ ፥ (ሌ) ፤ ራስ ፥ ብትን ፥ ዘንጋዳ ፥ ደረቅ ፥ መሳይ ፥ እንጭፍሬ ።

ማንጨብረር ፤ ማቃጠል ፥ ማንጨፍረር ።

ተንጨበረረ ፤ (ጨበረረ) ፤ ተቃጠለ ፤ ተንጨፈረረ ።

ጨበረር ፤ ጨብራራ ፤ የተንጨበረረ ፥ የተቃጠለ ፤ ጨፈረር ፥ ጨፍራራ ፤ ቁም ፥ ጠጮር ።

ጨብራራ ፤ የጨብራራ ፥ ዐይነት ፤ ደረቅ ፥ ጠጮሩ ፥ እንደ ፥ እሾኽ ፥ የሚዋጋ ፥ የሚለበልብ ። አባ ፥ ጠብራራ ፥ እንዲሉ ፥ አባ ፥ ጨንሬ ፥ ሲሉ ።

ጭብርር ፤ የጨበረረ ፥ የተንጨበረረ ።

ጭብርር ፥ አለ ፤ ተንጨበረረ ።

መንጨብረር ፤ መቃጠል ፥ መንጨፍረር ።

አጨበራረር ፤ አደራረቅ ፤ መጨብረር ።

(ጨበሰ) ፤ ጠበሰ) ፤ አጭበሰበሰ ፤ አላስነድድ ፥ አላሳይ ፥ አለ ፤ አጨሰ ፤ በትክክል ፥ መንደድን ፥ ማየትን ፥ ከለከለ ፤ አጭፈነፈን ። ጨነበሰን ፥ እይ ፤ የዚህ ፥ ዘር ፥ ነው ።

ማጭበስበስ ፤ ማጨስ ፥ ማጭፈንፈን ።

ተጭበሰበሰ ፤ አላይ ፥ አልነድ ፥ አለ ፤ በሽ ተኛ ፥ ዐይን ፥ ርጥብ ፥ ዕንጨት ።

መጭበስበስ ፤ መጭፈንፈን ፥ መጨስ ።

ጫጉ ፤ የማር ፥ መስፈሪያ ፤ ብዙውን ፥ ጕ ንዱ ፥ አንድ ፥ የሚያደርግ ፥ ማድጋ ።

ጨገገ ፤ (ጠገገ ። ጸገመ) ፤ ቅፍፍ ፥ አለ ፤ ጭጋግ ፥ ኾነ ።

ጨገገ ፤ ተጠጋ ፥ ተጣበቀ ።

ጭጋግ ፤ (ጽጋግ ፥ ቆባር) ፤ ጉም ፥ የሚ መስል ፥ ዐቢራ ፥ በአየር ፥ በምድር ፥ የሚታይ ።

ጭጋግ ፥ ፌት ፤ ፊቱን ፥ የማይጠዳው ፥ ፊተ ፥ ጨፍጋጋ ፥ ሰው ።

ጭጮጮት ፥ (ቶች) ፤ ቅጥነቱም ፥ መጠ ኑም ፥ እንደ ፥ መርፌ ፥ የኾነ ፥ ጥቅር ፥ እሾኽ ። በ ጣፋ ፥ ከልብስ ፥ ከበርኖስ ፥ የሚጣበቅ ፥ ሻካራ ፥ ጠጮር ፥ አለው ፤ የንጨቱ ፥ ኹናቴ ፥ የኑግ ፥ አገዳ ፥ ይመስላል ። ቢላንና ፥ ፍቅሩ ፥ ጥኑን ፥ እይ ።

ጭጮጮት ፥ ፌት ፤ ፊተ ፥ መጥፎ ፥ አይ ጠዳሽ ።

ጨገው ፤ (ጸገወ) ፤ ለምለም ፥ ስንደዶ ።

ጨጮለ ፤ (ጸቈነ) ፤ ጀጮለ ፤ ቀየደ ፥ ከሰበ ፥ ጋረደ ፥ በሐር ፥ ባበባ ፥ ሸፈነ ፤ አስጌጠ ፥ ሸለመ ፥ አሳመረ ፥ አንቈጠቈጠ ። ጨነጮለን ፥ እይ ።

ጨጓይ ፤ የጨጮለ ፥ የሚጨጮል ፤ አስጊ ያጭ ።

መጨጮል ፤ መከበብ ፥ መጋረድ ፥ መሸፈን ፥ ማስጌጥ ።

መጨጮያ ፤ ማስጊጫ ፥ ማሳመሪያ ፤ ዘንባ ባን ፥ አሓያን ፥ ጥድን ፥ ጽጌ ፥ ረዳን ፥ የመሰለ ፥ ቅ ጠላቅጠል ።

ተጨጮለ ፤ ተጀጮለ ፤ ተከበበ ፥ ተጋረደ ፥ ተሸፈነ ፥ ተጌጠ ፥ ተሸለመ ፥ አማረ ፥ ሰመረ ፥ ተን ቈጠቈጠ ።

ማጭሳ ፥ (ዎች) ፤ የሙሽራ ፥ ቤት ፥ በሐር ፥ የተንቈጠቈጠ ፥ ባበባ ፥ ያጌጠ ። (ግጥም) ፤ እቴ ፥ ሸንኰራ ፤ ማጭሳሽ ፥ አብቢል ፥ ዛሬ ። በግእዝ ፥ ጸቈን ፥ ይባላል ። ሙሽራውና ፥ ሙሽራዋም ፥ ከነ ሚዜዎቹ ፥ በማደሪያቸው ፥ ስም ፥ ማጭሳ ፥ ይባላሉ ። የማጭሳ ፥ ቤት ፥ እንዲሉ ።

አጨጓጮል ፤ አጀጓጮል ፤ መጨጮል ።

ጭጭኝ ፤ (ተገነ) ፤ የጎፍረት ፥ ጠጮር ፤ የጮያ ፥ ችግኝ ።

ጨጮፈ ፤ ጨጮረ ፤ ጠጮሩ ፥ በዛ ፥ በኹለ ንተናው ፥ ላይ ።

ጨጓፋ ፤ የጨጮፈ ፥ ባለብዙ ፥ ጠጮር ፥ ከ ብት ፥ ሰው ።

ጨጮፍ ፤ ብዛት ፥ ያለው ፥ ጠጮር ።

ጨጮፈ ፤ ጨጮፋም ፤ ፊቱ ፥ ጨጮፍ ፥ የለ በሰ ።

መጨጮፍ ፤ ጨጓፋ ፥ መኸን ።

ጨጮረ ፤ (ጸጮረ) ፤ ጠጮራም ፥ ኾነ ፤ ዐ ረም ፥ በቀለበት ፤ ጨገራ ፥ መሰለ ።

ጨጓራ ፤ በሆድ ፥ ውስጥ ፥ ያለ ፥ የምግብ ፥ ከረጢት ፥ (ቋት) ፥ ሥጋዊ ፥ ጠጮር ፥ ያለው ፥ (ዘፀ ፲፪ ፥ ፱) ። የሚያመሰኳ ፥ እንስሳ ፥ ግን ፥ ጨጓራው ፥ ፪ ፥ ነው ። ፩ኛው ፥ የሽርክት ፤ ፪ኛው ፥ የልዝብ ። ፈረንጆች ፥ ጨጓራን ፥ እስቶማክ ፥ ይሉታል ። ዶሰ ተን ፥ እይ ።

ጨጓር ፤ (ጸጓር) ፤ ጠጮራም ፥ ጭገራም ፤ ባለጠጮር ፥ ጠጮሩ ፥ የበዛ ፥ የረዘመ ።

ጨጓሬ ፤ (ጸጮራዊ ፥ ዘጸጮር) ፤ ዝኒ ፥ ከ ማሁ ፤ የጨጓራ ፥ ዐይነት ፥ ወገን ፤ ኹለንተናው ፥ ጠጮር ፥ የኾነ ፤ ጠጮር ፥ የለበሰ ፥ ትል ። አባ ፥ ጨ ጓሬ ፥ እንዲሉ ። ጨብራሬን ፥ ተመልከት ።

ጭገር ፤ ጠጮር ። (ተረት) ፤ ዐጸኝ ፥ ውሻ ፥ ጭገር ፥ ባኹ ፤ በትር ፥ ትርኹ ።

ጭገር ፤ ጭጮኝ ።

ጭገራም ፤ ጭገረ ፡ ብዙ ፡ ባለጭገር ።

ጭገሬታ ፤ መልክ ፡ መሰል ፡ ምልክት ፡ ሕብር ፡ ዐይነት ፤ ፍለጋ ፡ ጭገር ፡ ያረፈበት ፡ የወደቀበት ። ጭገሬታው ፡ ጠፋ ፡ እንዲሉ ።

መጨጮር ፤ ጠጮራም ፡ መኾን ፤ ዐረም ፡ ማውጣት ።

አጨጮረ ፤ ጠጮር ፡ ጭገር ፡ አበቀለ ፤ ዐረም ፡ አወጣ ።

ማጨጮር ፤ ጨጓራ ፡ ማስመሰል ።

ጨገተ ፤ (ጠጋ ፡ ተጠጋ) ፤ ጫነት ፡ ጭጮት ፡ ሠራ ፡ አበጀ ።

ጫገት ፡ (ቶች) ፤ ዐጪር ፡ የጠጣ ፡ ወጥ መድ ፤ በላዩ ፡ ደንጊያ ፡ ያለበት ፡ ጣራና ፡ ግድግዳ ። ጠጣው ፡ ይገባና ፡ በገመድ ፡ ታስሮ ፡ በመካከሉ ፡ የተንጠለጠለውን ፡ ያገዳ ፡ ራስ ፡ በሳበው ፡ ጊዜ ፡ መዝጊያው ፡ ወዲያው ፡ በቶሎ ፡ ይዘጋል ፤እሱንም ፡ ሰዎች ፡ በጦር ፡ እየወጉ ፡ ይገድሉታል ።

ጫገት ፡ ሬት ፤ ፊተ ፡ መጥፎ ፡ አስቀያሚ ።

ጭገታ ፤ ዝኒ ፡ ከማው ፡ ለጫገት ።

ጭጮት ፡ (ቶች) ፤ የግንብ ፡ ሣጥን ፡ የዕቃ ፡ ማስቀመጫ ፡ ማናሪያ ፤ ዳግመኛም ፡ ጕልት ፡ ይባላል ።

ጭዳ ፤ (ጋላ) ፤ የሰርግ ፡ ስም ፤ ሰርግ ።

ጭዳ ፤ (ጭዳን) ፤ የከብት ፡ ቀላ ፤ አረማውያን ፡ (የቀድሞ ፡ ሰዎች) ፡ የበጉን ፡ ቀላ ፡ ፍሬውን ፡ አውጥተው ፡ በውስጡ ፡ ገለባ ፡ ይጨምሩና ፡ ሰፍተው ፡ ከፈረስ ፡ ወንዣት ፡ ያጠልቁታል ፤ ስሙንም ፡ መጨቻ ፡ ይሉታል ።

ጭዳ ፡ አለ ፤ በቤት ፡ ውስጥ ፡ በአድባር ፡ ሥር ፡ ለጣዖት ፡ ለሰይጣን ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋ ፤ የበግና ፡ የፍየል ፡ ወጠጤ ፡ ወይፈን ፡ ኰርማ ፡ (የቀላ) ከብት ፡ ዐረደ ። ግንባሩንና ፡ የፈረሱን ፡ ግንባር ፡ በደም ፡ ቀባ ፤ ወይም ፡ ደሙን ፡ በጋሻው ፡ ቀዳ ፤ አምልኮ ፡ ባዕድ ፡ አደረገ ። ወደ ፡ ሰርግ ፡ ቤት ፡ ደም ፡ ረግጦ ፡ ገባ ፡ አሻረተ ።

ጭድ ፤ (ዐጪደ ፡ ዕጭድ) ፤ የጤፍ ፡ ገለባ ፡ ፈጥኖ ፡ የሚነድ ፤ የበሬ ፡ መኖና ፡ ጭቃ ፡ መርገጫ ፡ (ኢሳ፲፩ ፡ ፮) ። እከሌና ፡ እከሌ ፡ እሳትና ፡ ጭድ ፡ ናቸው ፡ እንዲሉ ።

ጨደደ ፤ ከፈለ ፡ ቈረጠ ፡ ቀደደ ፡ ሠነጠቀ ።

ጨዳደ ፤ ከበበ ፡ ዞረ ፤ የፊተኛው ፡ እንዳይኼድ ፡ የኋለኛው ፡ እንዳይከተል ፡ (እንዳይለጥቅ) ፡ አገደ ፡ ከለከለ ፡ መለሰ ።

ጨደደ ፤ በዙሪያ ፡ ዐጨደ ፡ ሠራ ።

ጨደደ ፤ ከበደ ፡ ተማነ ፡ ቀፈፈ ። ዛሬ ፡ ቀኑ ፡ ጨድዷል ። ፈቴን ፡ ይጨድደኛል ።

ጨዳጅ ፤ የጨደደ ፡ የሚጨድድ ፤ ከፋይ ፡ ከባቢ ።

ጨድድ ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ከፈል ፡ ጣስ ፡ ከበብ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ጨድዴ ፤ የጨድድ ፡ ወገን ፡ ጣሴ ፤ ሐር በኛ ፡ የጦር ፡ ገበሬ ፡ በጠላት ፡ ጦር ፡ ሰራዊት ፡ መካከል ፡ የወንድ ፡ በር ፡ የተሰጠው ፡ (ፎሳሙ ፡ ፳፫ ፡ ፲፯) ።

መጨደድ ፤ መክፈል ፡ መቍረጥ ፡ መክበብ ።

መጨደጃ ፤ መቍረጫ ፡ መክበቢያ ።

አስጨደደ ፤ አስቈረጠ ፡ አሠነጠቀ ።

አስጨደደ ፤ አስከበበ ፤ አሳገደ ።

ተጨደደ ፤ ተከፈለ ፡ ተሠነጠቀ ፡ ተቈረጠ ።

ተጨደደ ፤ ተከበበ ፤ ታገደ ፡ ተከለከለ ፡ ተመለሰ ።

ጭድድ ፤ የተጨደደ ፡ ተቈርጦ ፡ የቀረ ፡ ምልስ ፤ ዙሪያውን ፡ የተከበበ ፡ የታጠደ ፡ የተሠራ ።

ጨሃ ፤ ዳባ ፡ ሳም ፤ ትክክል ፡ ስፍር ፡ ዕልፍ ፡ ትርፍ ፡ የሌለው ፤ በትግሪኛ ፡ ደፍደፍ ፡ ይባላል ።

ጨዋ ፤—ማይምን ፤—ጨው ።

ጨው ፡ (ዎች) ፤ ጼው) ፤ ምግብን ፡ ጕሉ ፡ የሚያጣፍጥ ፡ ደንጊያ ፡ ማዕድንነትና ፡ ገንዘብነት ፡ ያለው ፤ በውሃ ፡ የሚቀልጥ ፡ የሚሸሻ ፡ ጋን ፡ ፉር ፡ ልመደው ፡ አሞሌ ፡ ዐሸቦ ፡ አሻል ። (ተረት) ፤ ጨው ፡ ይወዱኝ ፡ ብለኸ ፡ ጣፍጥ ፤ አለዚያ ፡ ግን ፡ ደንጊያ ፡ ብለው ፡ ይጥሉኻል ። የጨው ፡ ገደል ፡ ሲናድ ፡ ሞኝ ፡ ይልላል ፤ ብልኅ ፡ ያለቅሳል ። (የወር ፡ ጨው) ፤ ለቤት ፡ መፍቅድ ፡ በወር ፡ የሚወጣ ፡ ገንዘብ ። ወረፈ ፡ ብለኸ ፡ ወረፍኩኽን ፡ እይ ። (የንግሊዝ ፡ ጨው) ፤ ሲጠጡት ፡ የሚያስቀምጥ ፡ ሐሞት ፡ የሚያሰጣ ፡ መራራ ፡ ጨው ፡ እንግሊዝ ፡ እያበጀና ፡ እያዘጋጀ ፡ ለዓለም ፡ የሚሼጠው ።

ጨው ፡ በሌ ፤ የወንዝ ፡ ስም ፤ በሚጣቅ ፡ አቅራቢያ ፡ ያለ ፡ ወንዝ ። የነጋዴ ፡ ጨው ፡ ስለ ፡ ወሰደ ፡ በዚህ ፡ ስም ፡ ተጠራ ፡ ይላሉ ።

ጨው ፡ ባሩድ ፤ የሚቃጠል ፡ የባሩድ ፡ ጨው ፡ የቦረቦቹ ፡ ደንጊያ ። ባሩድን ፡ ተመልከት ።

ጨው ፡ ጨው ፡ አለ ፤ ጣፈጠ ፤ ጣም ፡ ሰጠ ።

(ጨወየ) ፤ አጨወየ ፤ ጨው ፡ ጨዋ ፡ አደረገ ፤ በጨው ፡ ዐጀለ ።

ማጨውየት ፤ ማድረግ ፡ መጨመር ፡ ጨውን ።

ተጨወየ ፤ ጨው ፡ ጨዋ ፡ ኾነ ፤ ጨው ፡ ተንሰነሰበት ።

ጨዋ ፡ (ዎች) ፤ ፈደል ፡ ያልቈጠረ ፡ ትም ርት ፡ ያልተማረ ፡ ማይምን ።

ጨዎች ፤ አሞሌዎች ፡ ጋንፋሮች ።

ጨዎች ፤ ጨዋዎች ፡ ማይምኖች ።

ጨዋ ፤ (ልሂቅ) ፤ ዐዋቂ ፡ ዐዛውንት ፡ ሽማግሌ ፡ አስታራቂ ፡ ገላጋይ ። ጨዋ ፡ ዐር ፡ ያበ ላል ፡ እንዲሉ ። ጨዋ ፡ በልጅነቱ ፡ ሲሠራው ፡ የነ በረውን ፡ ልጆች ፡ ሲሠሩት ፡ ቢያይ ፡ ይነቅፋል ። ጨው ፡ ምግብን ፡ ኹሉ ፡ እንደሚያሰማማ ፡ ጨ ዋም ፡ መክሮ ፡ ዘክሮ ፡ አንተም ፡ ተው ፡ አንተም ፡ ተው ፡ ብሎ ፡ የተጣላን ፡ ያስታርቃል ፤ በጠብ ፡ የተ ለያየውን ፡ በፍቅር ፡ አንድ ፡ ያደርጋልና ፤ ጨው ፡ እ ንደ ፡ ግለት ፡ ጨዋ ፡ ተባለ ። ጌታችን ፡ ደቀ ፡ መዛ ሙርቱን ፡ እናንተ ፡ የምድር ፡ ጨው ፡ ናችኹ ፡ እን ዳለ ፡ (ማቴ፭ ፡ ፲፫) ።

ጨዋነት ፤ ጨዋ ፡ መኾን ፡ ሽምግልና ።

ጨዋ ፤ (ሐራ) ፤ የንጉሥ ፡ አሽከር ፡ ዘማች ፡ ወታደር ፡ የጦር ፡ ሰው ፡ ምሪተኛ ፡ ስላገልግሎቱ ፡ በባላገር ፡ ላይ ፡ እየተሠራ ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ መል ከኛ ፡ ባላባት ፡ የኾነ ፤ ይኸውም ፡ ዐማራ ፡ (ዐም ፡ ሐራ) ፡ ነው ። የጨዋ ፡ ልጅ ፡ እንዲሉ ። የጨዋ ፡ ልጅ ፡ ተዋርዶ ፡ ዕንጨት ፡ ሰበራ ፡ ቄሳ ፡ ወርዶ ፤ ሲያነደው ፡ ያድራል ፡ ሌሊቱን ፡ ቀን ፡ የሰበረውን ፡ (አዝማሪ) ። ዳግመኛም ፡ ጨዋ ፡ ግእዝ ፡ ዴዋ ፡ ካለው ፡ ቢወጣ ፡ የምርኮኛን ፡ ባላባትነት ፡ ክብ ርና ፡ ማዕርግ ፡ ያሳያል ፡ (ዳን፩ ፡ ፫ ፡ ፩—፮ ። ፫ ፡ ፲፱) ።

ጫዊ ፤ የቄሳ ፡ ቍስል ፡ እግርን ፡ ጨው ፡ የ ሚያስመስል ፤ ጕርምጥ ።

ጭው ፤ (ጸውዖ ፡ ጸዊት) ፤ መጮኽ ።

ጭው ፡ አለ ፤ ጮኸ ፤ ጩኸት ፡ አሰማ ፤ የገሮሮ ፡ የጫጩት ፡ የወፍ ።

ጭው ፡ አለ ፤ ጨዋም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኾነ ። ጭው ፡ ያለ ፡ በረሓ ፡ እንዲሉ ፡ (መዝ፻፮ ፡ ፵፬) ።

ጭው ፡ አለ ፤ ከሳ ፡ ደረቀ ፡ ቀለለ ፤ የፊት ፡ የደም ፡ ግባት ።

ጪ ፡ አለ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ።

ጭው ፡ ጭው ፡ አለ ፤ መላልሶ ፡ ጮኸ ።

ጨውናና ፤ ፈተ ፡ መጣጣ ፤ ዐሸቦ ፡ የነፋ በት ፡ የሚመስል ፡ ሰው ።

ጨወተ ፤ (ጸወተ) ፤ ተነገረ ፡ ኾነ ፡ ተደ ረገ ፡ ጨዋታው ።

ጨዋታ ፤ ነገር ፤ ሩጫ ፡ ልፊያ ፡ ዘፈን ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ሣቅ ፤ ሥላቅ ፤ ኳስ ፡ መወርወር ፡ ጥንግ ፡ መምታት ። በገና ፡ ጨዋታ ፡ አይቈጡም ፡ ጌታ ፡ እንዲሉ ።

ጨወት ፤ ጨዎት ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ከፉና ፡ በጎ ።

ጨወታ ፤ ጨዎታ ፤ ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ከማሁ ፡ (ዘዳ፳፰ ፡ ፴፪ ። ፩ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፩) ። ጨወት ፡ ጨወታ ፡ የመሠሀራን ፡ ንግግር ፡ ነው ።

ጨውት ፤ (ጸውት) ፤ ጩኸት ፡ ጫጫታ ።

ጨውቴ ፡ (ዎች) ፤ የጨውት ፤ የዝንጀሮ ፡ ልጅ ፤ ጨዋታ ፡ ዐዋቂ ፡ ሰው ።

ጨውቴነት ፤ ጨውቴ ፡ መኾን ።

አስጫወተ ፤ ማንኛውንም ፡ ጨዋታ ፡ አስ ደረገ ።

ተጫወተ ፤ (ተጸወተ) ፤ ሥጋዊና ፡ መን ፈሳዊ ፡ ነገር ፡ ተናገረ ፤ ተላፋ ፤ ዘፈነ ፡ አዘመረ ፤ አላገጠ ። እከሌ ፡ በእከሌ ፡ ተጫወተበት ፡ እንዲሉ ። የሀብታም ፡ ልጅ ፡ ሲጫወት ፡ የድኻ ፡ ልጅ ፡ ይሞት ።

ተጫዋች ፡ (ኞች) ፤ የተጫወተ ፡ የሚጫ ወት ፤ ዘፋኝ ፡ አዝማሪ ፡ አማሪት ፡ ገንቦኛ ፡ አረኽ ።

መጫወት ፤ መናገር ፡ መላፋት ፡ መሮጥ ፡ መጋለብ ፡ ገና ፡ መምታት ።

መጫወቻ ፤ መሮጫ ፡ መላፊያ ፡ ስፍራ ፡ ሜዳ ፡ ጊዜ ፤ ኳስ ፡ ዕሩር ፡ ጊጤ ፡ አሻንጉሊት ፡ ገበጣ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ክራር ፡ ማሲንቆ ፡ በገና ፡ ከ በሮ ፡ ነጋሪት ፡ ሙዚቃ ፡ ዋሽንት ፡ እንቢልታ ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። (ተረት) ፤ አንበሳ ፡ ቢያረጅ ፡ የዝንብ ፡ መጫወቻ ፡ ይኾናል ።

መጫወቻ ፤ ማላገጫ ፡ ሞኝ ፡ ሰው ።

ተጨዋወተ ፤ ተነጋገረ ፤ ጨዋታ ፡ ተመላ ለሰ ፡ ተለዋወጠ ።

ጭውውት ፤ ንግግር ።

መጨዋወት ፤ መነጋገር ፤ እንዲህ ፡ ኾነ ፡ መባባል ።

አጫወተ ፤ (አስተጸወተ) ፤ ወሬ ፡ አ ወራ ፡ ወግ ፡ አወጋ ፡ ነገር ፡ አነጋገረ ፤ አላፋ ፡ አ ሣቀ ፡ ደስ ፡ አሠኘ ፡ (ምሳ፯ ፡ ፳፪ ። ግብ ፡ ሐዋ፲፭ ፡ ፩) ። ቄለን ፡ አይ ።

አጫዋች ፡ (ኞች) ፤ ያጫወተ ፡ የሚያጫ ውት ፤ አነጋጋሪ ፡ አሥቂኝ ፡ ጥርስ ፡ የሚያስከድን ፡ አሉቃ ፡ ገብረ ፡ ሐናን ፡ አባ ፡ ምን ፡ ይዋብን ፡ ከሉን ፡ የመሰለ ፡ የጨዋታ ፡ ፈላስፋ ፤ አዝማሪ ፡ ሲያውቅ ፡ አበድ ፡ ቀልደኛ ። (የምድር ፡ አጫዋች) ፤ ድንክ ፡ ሰው ።

አጫዋች ፤ የወንድና ፡ የሴት ፡ ስም ።

አጫዋች ፤ የቤተ ፡ ክሲያን ፡ ጕልላትና ፡ ሰበሰብ ፡ የበቅሎ ፡ ዐልቦ ፡ መርገፍ ፡ በነፋስ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ እየተጋጨ ፡ ድምፅ ፡ የሚሰጥ ።

አጫውተኝ ፤ የሰው ፡ ስም ።

ማጫወት ፤ ማነጋገር ፡ ማላፋት ።

ማጫወቻ ፤ ጊዜና ፡ ቦታ ።

አጨዋወተ ፤ ጨዋታን ፡ አለዋወጠ ፡ አቀ ባበለ ።

አጨዋወት ፤ አነጋገር ፤ መጫወት ።

ጨጨ ፤ የጠንቋይ ፡ ጽፈት ። ራፎንን ፡ ተመ ልከት ።

ጨጨ ፤—ታናሽ ፡ ልጅ ፤—ማጨ ።

ማጨ ፤ (ፃእዕአ) ፤ አነሰ ፡ ኰሰሰ ፤ ከሳ ፡ ቀጠነ ፡ መነመነ ፡ ኰሰመነ ፡ ሰለለ ።

ጨጨ ፡ (ም፟ች) ፤ በቤት ፡ መንግሥት ፡ የሚያድግ ፡ ሕፃን ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ በሺዋ ፡ ባንክ በር ፡ ማዕርት ፡ ፮ኛ ፡ ክፍል ፡ የኾነ ።

ጨጨ ፤ የሰው ፡ ስም ፤ የጨጨ ፡ ወገን ፡ ግለት ፡ ነው ።

ጭጭን ፤ (ፃፄ) ፤ ጕንዳን ፡ ዘመሚት ፡ ቀጫጭ ።

ማጨት ፤ (ጸጹት) ፤ የዶሮ ፡ የወፍ ፡ ያሞራ ፡ ልጅ ፡ ታናሽ ፡ ፍጥረት ። በግእዝ ፡ ግን ፡ ትን ኻም ፡ ጸጹት ፡ ይባላል ። ሲበዛ ፡ ማጨቶች ፡ ይላል ፡ (ዘሌ፲፪ ፡ ፮ ። ኢዮ፴፱ ፡ ፴) ።



ማጨቶች ፡

ጭጭት ፤ ብዙ ፡ ልጅ ፡ እንዳሸዋ ፡ በሜዳ ፡ ፍስስ ፡ ያለ ።

መጨጨት ፤ ግነስ ፡ መኰሰስ ።

አጨጨ ፤ (አፃእዕአ) ፤ አሳነሰ ፡ አኰ ሰሰ ፡ አቀጠነ ፡ አመነመነ ።

ማጨጨት ፤ ማኰሰስ ፡ ማክሳት ።

እንጭጭ ፡ (ፌች) ፤ ጥቃቅን ፡ ፍሬ ፡ ጨርቋ ፤ ግንኛውም ፡ ያልበሰለ ፡ እሸት ።

እንጮጭ ፤ ገረ ፡ ከግሁ ፤ መራራ ፡ የማ ይጣፍጥ ፤ እንጉይ ። እንጮጭ ፡ የቀጨሞ ፡ ፍሬ ፡ እንዲሉ ።

እንጫጭላ ፡ (ሎች) ፤ እንቃቅላ ፡ ዐራስ ፡ ልጅ ፡ ርጥብ ፡ ለጋ ፤ ቡችላ ።

ውጫጭ ፤ ውሪ ፡ ሙሚሊ ፡ የሰው ፡ የዝን ጀሮ ፡ ልጅ ።

(ጫጫ) ፤ አንጫጫ ፤ አንቻቻ ፡ አስ ጮኽ ። ዘሩ ፡ በግእዝ ፡ ጣእዋአ ፡ ነው ።

ጭጭ ፤ በታናሽ ፡ ቃል ፡ መጮኽ ። ወፍ ፡ ጭጭ ፡ ሰማይ ፡ ብልጭ ፡ ቢል ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ አይ ደረግም ።

ጭጭ ፡ አለ ፤ ድምፅ ፡ ሰጠ ፡ አሰማ ፤ ጮኽ ፡ እንደ ፡ ማጡት ።

ጭጭ ፡ አለ ፤ (ጸመወ) ፤ ዝም ፡ ዕክም ፡ ጸጥ ፡ አለ ፤ አፉን ፡ ያዘ ።

ጭጭ ፡ በል ፤ ዝም ፡ በል ።

ጭጭ ፡ አይበሉ ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ጠላ ቶች ፡ የወፍ ፡ ያኽል ፡ አይጡኹ ፡ አይናገሩ ፡ ግለት ፡ ነው ።

ጭጭ ፡ ምጭጭ ፤ (ጭጭ ፡ ምንም ፡ ጭጭ) ፤ ባሕታዊ ፡ ቅጠል ፡ ሲበላ ፡ ዕሥጭ ፡ ሚጥ ፡ ብትልበት ፡ የተሲያት ፡ እኽል ፡ ጭጭ ፡ ምጭጭ ፡ የለም ፡ አለ ፡ ይላሉ ።

ማንጫጫት ፤ ማንቻቻት ፡ ማስጮኽ ።

ማንጫጫ ፤ ማንቻቻ ፡ መታደያ ።

ተንጫጫ ፤ ተንቻቻ ፡ ጮኸ ፡ ተፋጀ ። (ተ ረት) ፤ ተልባ ፡ ቢንጫጫ ፡ በሙቀጫ ።

መንጫጫት ፤ መንቻቻት ፡ መጮኽ ።

መንጫጫ ፤ መንቻቻ ፡ ስፍራ ።

ጫ ፡ አለ ፤ ዝም ፡ ርጭ ፡ አለ ።

ጫ ፡ አለ ፤ ከሳ ፡ ቀለለ ፤ የፊት ።

ጫታ ፤ (ጽማቄ) ፤ ዝምታ ፡ ርጋታ ፡ ጸ ጥታ ።

ጫጫታ ፤ ቻቻታ ፡ ጩኸት ፡ ፍጅት ፡ የወ ፍና ፡ የልጅ ።

ጫጫቴ ፤ ጫጫታ ፡ የሚያደርግ ፡ ተኰል ኰሎ ፡ ብዛት ፡ ያለው ።

ጫጫ ፤ የገጦማ ፡ ስም ፤ በወግዳ ፡ መካከል ፡ የሚወርድ ፡ ታላቅ ፡ ዥረት ።

ጫጫት ፤ በታችኛው ፡ ወግዳ ፡ ከጫጫ ፡ በስተቀኝ ፡ ያለ ፡ አገር ፡ የገብራል ፡ አጥቢያ ።

ጮርጮ ፤ የስፌት ፡ ዕቃ ፤ የወተት ፡ ማለ ቢያ ፡ ቁጀ ፡ አኮሌ ።

ጮርጮ ፤ የወይባ ፡ ዐይነት ፡ ዕንጨት ፡ ከ ሰል ፡ የሚኾን ።

ጨጨሆ ፤ በበጌምድር ፡ ክፍል ፡ ያለ ፡ አ ገር ። ጨጨሆ ፡ በር ፡ እንዲሉ ። በትግሪኛ ፡ ነጭ ፡ ግለት ፡ ነው ።

ጭጭን ፤—ጕንዳን ፤—ማጨ ።

ጨጨረ ፤ (ፀፀረ) ፤ በጣም ፡ ጠጠረ ፡ ጠና ፡ ጠነከረ ፤ አልቈረጠም ፡ አልታኘኽ ፡ አለ ፤ የቈሎ ።

መጨጨር ፤ መጠጠር ፡ መጥናት ፡ መ ጠንከር ።

አጨጨረ ፤ አጠጠረ ፡ አጠና ፡ አጠነከረ ።

ማጨጨር ፤ ማጠጠር ፡ ማጠንከር ።

ጫጭት ፤—የዶሮ ፡ ልጅ ፤—ማጨ ።

ጫጫታ ፤—ጩኸት ፤—(ጫጫ) ።

ጫጫቴ ፤—ወፍ ፡ ልጅ ፤—(ጫጫ) ።

ጭጨት ፤ የከብት ፡ በረት ፡ ፍግ ፡ መራት ፡ የሚያሠባ ።

ጭማት ፤—ብዙ ፡ ልጅ ፤—ማጨ ።

ጠከ ፤—ደረቀ ፤—ጠከከ ።

ጨኮ ፤ በግራና ፡ በቀኝ ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ክንፍ ፡ ያለው ፡ ያረመኔ ፡ ጦር ።

ጫካ ፤ (ጋላ) ፤ ደን ። ጫካ ፡ ገበያ ፡ እን ዲሉ ።

ጭኮ ፤ (ጋላ) ፤ የመብል ፡ ስም ፤ በጨው ፡ በበርበሬ ፡ በቅመምና ፡ በንጥር ፡ ቅቤ ፡ የተዘጋጀ ፡ በሶ ፤ ጣም ፡ ያለው ፡ ምግብ ።

ጮኸ ፤ (ጸውዐ ። ዕብ ፡ ጸዋሕ) ፤ እሪ ፡ ቀሞ ፡ አለ ፤ ድምጥ ፡ አሰማ ፤ የሰው ፡ ያለኸ ፡ ድረሱልኝ ፡ አለ ፤ አገረረ ፤ ቡታ ፡ ሰደደ ። (ተረት) ፤ ቆቅና ፡ ባለጌ ፡ በራሱ ፡ ይጮኻል ። ወፍ ፡ እንዳገሯ ፡ ትጮኻለች ።

ጮኸ ፤ ለዳኛ ፡ ለንጉሥ ፡ አቤት ፡ አለ ።

ጮኸ ፤ ዜማ ፡ ተማረ ።

ጮኸ ፤ አገሣ ፡ (ራእ፤ ፡ ፫) ።

ጮኸ ፤ ዙሪሁ ፡ አለ ።

ጮኸ ፤ አናፋ ።

ጮኸ ፤ ተንጓጓ ፡ ተመመ ፡ ተንጫጫ ።

ጮኸ ፤ አዉ ፡ ዉዉ ፡ አለ ። (ተረት) ፡ ውሻ ፡ አበላበት ፡ ይጮኻል ። ዥብ ፡ ከኼደ ፡ ውሻ ፡ ጮኸ ።

ጮኸበት ፤ ተቈጣው ።

ጩኺ ፡ (ዎች) ፤ የጮኸ ፡ የሚጮኽ ፤ የተ በደለ ፡ አቤት ፡ ባይ ፡ (ኢሳ፮ ፡ ፱ ። ኤርሚ፳ ፡ ፵፰) ።

ጩኸት ፡ (ቶች) ፤ እሪታ ፡ ቀሞታ ፡ ፍ ጅት ፤ አቤቱታ ። ጩኸቴን ፡ ቀሙኝ ፡ እንዲሉ ።

ጩኸት ፤ ያውሬ ፡ የንስሳ ፡ የወፍ ፡ ድምጥ ። ጩኸት ፡ ለቀሩ ፡ መብል ፡ ላምራ ፡ እንዲሉ ።

ጩኸታም ፤ ጩኸት ፡ ወዳድ ፡ ባለጩኸት ።

ጩኸት ፡ ትርፌ ፤ ቀሞ ፡ ቢሉ ፡ ሰው ፡ የማይደርስበት ፡ ጉድጓዳ ፡ የቀማኛ ፡ ስፍራ ፡ እሪ ፡ በከንቱ ።

መጮኸ ፤ ቀሞ ፡ ማለት ፤ አቤቱታ ፡ ማቅ ረብ ።

መጮኺያ ፤ አፍ ፡ አፋፍ ፡ ተራራ ፡ የስ ላም ፡ መስጊድ ፤ በጉንደር ፡ ከተማ ፡ ውጭ ፡ የሚ ገኝ ፡ ስፍራ ። ትግሬ ፡ መጮኺያ ፡ እንዲሉ ።

ጩጩኸ ፤ መላልሶ ፡ ጮኸ ።

አጮኸ ፤ የጅራፍን ፡ የጣትን ፡ የማንኛ ውንም ፡ ነገር ፡ ድምጥ ፡ አሰማ ።

አጮኸ ፤ ገረፈ ፤ ምች ፡ መታ ።

አጩኺ ፤ ያጮኸ ፡ የሚያጮኽ ።

ማጮኸ ፤ ማትመም ።

ማጮኺያ ፤ ቡሔ ፡ ገለብ ፡ ቋጥኝ ፡ እጅ ።

አስጮኸ ፤ ቀሞ ፡ አሠኘ ፤ አስተመመ ። ውሃን ፡ ምን ፡ ያስጮኸዋል ፡ ቢሉ ፤ ድንጋይ ።

አስጩኺ ፤ ያስጮኸ ፡ የሚያስጮኽ ።

ማስጮኸ ፤ እንዲጮኽ ፡ ማስደረግ ።

ማስጮኺያ ፤ መርዶ ፡ በትር ፡ ዐለንጋ ።

ተጮኸ ፤ ቀሞ ፡ ውይ ፡ ተባለ ፡ ድረሱልኝ ፡ ለማለት ፡ ለማልቀስ ፡ እንባ ፡ ለማፍሰስ ። (ጥሮ) ቢጮኸ ፡ ጋላ ፡ እንዲሉ ።

ተጩጩኸ ፤ ጩኸትን ፡ ተቀባበለ ፤ ተ ፋጀ ።

መጩጩኸ ፤ በጩኸት ፡ መኪታተል ።

አጩጩኸ ፤ ቀሞ ፡ አባባለ ፤ ጩኸትን ፡ እዛመተ ፤ አፋጀ ።

ጮክ ፤ መጮኸ ።

ጮክ ፡ አለ ፤ በጣም ፡ ጮኸ ፤ ድምጡን ፡ አበረታ ።

ጨኸ ፤ እሪ ፡ በል ። (ተረት) ፤ ባላደራ ፡ ጨኸ ፡ በተራራ ። ለራስ ፡ ምታት ፡ ጨኸበት ፤ ለሆድ ፡ ቀርጠት ፡ ብላበት ።

ጨኻ ፤ ጮኻ ፤ (ተረት) ፤ ጨኻ ፡ የማታ ውቅ ፡ ወፍ ፡ ዕርኳን ፡ ብትጮኽ ፡ ዕለቁ ፡ ዕለቁ ።

አጨኳኸ ፤ አተማመም ፤ መጮኽ ።

ጠከከ ፤ ጠከ ፤ ደቀቀ ፤ ፈጽሞ ፡ አረጀ ፤ ደረቀ ። የጠከከች ፡ ባልቴት ፡ የጠከከች ፡ ዶሮ ፡ እንዲሉ ።

መጠከክ ፤ ማርጀት ፡ መድረቅ ።

ጠከክ ፡ አለ ፤ ቀዘዘ ፡ አለ ፤ ጠፃ ፡ ኾነ ።

ጠከነ ፤ (ጸቈነ) ፤ በረታ ፡ ቻለ ፡ ታገሠ ።

ጠከነ ፤ ከፋ ፡ ልቡ ፡ ጠና ፡ ከርኅራኄ ፡ ራቀ ፤ ደፈረ ፡ ጠነከረ ፡ (ነሐ፱ ፡ ፮) ።

ጠካኝ ፤ (ጥቡዕ ፡ ድሩክ) ፤ የጠከነ ፡ የሚጠክን ፤ ለበጎ ፡ ለክፉ ፤ ቻይ ፡ ታጋሽ ፤ ደፋር ፡ ቈራጥ ፡ ጥኑ ፡ ጠንካራ ፡ ልበ ፡ ብርቱ ፤ ከፋ ፡ እናት ፡ አይምሬ ፡ ምሕረት ፡ የለሽ ፡ (ጀሳሙ ፡ ፳፫ ፡ ፳ ፱ዜና ፡ ፲፯ ፡ ፲፯) ። ጠካኝና ፡ ጨስ ፡ መውጣ ፡ አያጣም ።

ጠካኞች ፤ ደፋሮች ፡ ብርቱዎች ፡ (ጀሳሙ ፡ ፳፫ ፡ ፲፯ ። ፱ዜና ፡ ፲፯ ፡ ፲፫ ። ኤርሚ፳ ፡ ፲፭) ።

ጠካኝነት ፤ ጠካኝ ፡ መኾን ።

ጭከና ፤ (ጥብዐት ፡ ትብዐት) ፤ ብር ታት ፡ ትግሥት ፤ የመጠከን ፡ የመታገሥ ፡ ሥራ ።

ጭካኔ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ከፋት ፡ ድርቅና ።

ጠከን ፤ መጠከን ።

ጠከን ፡ አለ ፤ ጠከነ ።

መጠከን ፤ መበርታት ፡ መታገሥ ፡ መ ቻል ፤ አለማዘን ፡ አለመራራት ።

መጠከኛ ፤ መቻያ ፡ መታገሻ ፡ ጊዜ ፡ ስ ፍራ ።

አጠከነ ፤ አበረታ ፤ ጠካኝ ፥ አደረገ ፤ አከፋ ።

አስጠከነ ፤ አስቻለ ፥ አስታገሠ ።

አስጠካኝ ፤ ያስጠከነ ፥ የሚያስጠክን ።

ማስጠከን ፤ ማስቻል ፥ ማስታገሥ ።

ማስጠከኛ ፤ ማስታገሻ ፤ ምክር ፥ ስብከት ።

ተጠከነ ፤ ኸነ ፥ ተደረገ ፥ ጭካኔው ።

ተጠካከነ ፤ ሳይተዛዘን ፥ ቀረ ።

አጠካከነ ፤ መተዛዘንን ፥ አጣፋ ።

አጠካካኝ ፤ ያጠካከነ ፥ የሚያጠካክን ።

አጠካከን ፤ አበረታት ፤ መጠከን ።

(ላሌ) ጠሌ ፤—የሣር ፥ ችግኝ ፤—ጠለ ጠለ ።

(ጥሌ) ጠሌ ፤—የጌጥ ፥ ስም ፤— ጠለ ጠለ ።

ጭል ፥ አለ ፤ (ጠረረ) ፤ ጭር ፥ ርጭ ፥ ጸጥ ፥ አለ ፤ እንቅልፍ ፥ ወሰደው ።

ጮለ ፤ (ጦለ) ፤ ብልኅ ፥ ኸነ ፥ ሠለጠነ ፥ ቀለጠፈ ፥ ፈጠነ ፥ ልጁ ፥ ፈረሱ ።

ጮለ ፤ በጥፊ ፥ ተመታ ።

ጮሌ ፥ (ዎች) ፤ የጮለ ፤ ብልጥ ፥ ብልኅ ፥ ቀልጣፋ ፥ ፈጣን ፥ ጅጭ ፥ ሽምጣጭ ። ጮሌ ፥ ፈረስ ፥ እንዲሉ ። ጮሌ ፥ ሲያረጅ ፥ መጋጥ ፥ ይኾናል ። አፍን ፥ እይ ።

ጮሌነት ፤ ጮሌ ፥ መኾን ፤ ብልኅነት ፥ ፈጣንነት ።

አጮለ ፤ አፈጠነ ፥ ነዳ ።

አጮለ ፤ በጥፊ ፥ መታ ፥ (ፏነገ ፥ ፳፪ ፥ ፳፬) ።

ማጮል ፤ ማፍጠን ፥ መምታት ።

ማጮያ ፤ ማፍጠኛ ፤ መምቻ ፥ ውስጥ ፥ እጅ ።

ጠለገ ፤ (ትግ ፥ ጸለገ) ፤ ሰቀለ ፥ ሰቀጠጠ ፥ ከለከለ ፥ ወተትን ፥ የላም ፥ ወሸ ።

ጠለገ ፤ ገፈፈ ፥ ጭልጊ ፥ አወጣ ።

ጭልጊ ፤ (ጅልጊ) ፤ ጭልጋዊ ፥ የጭልጋ ፤ የወይፈን ፥ ስልቻ ፥ ዐይበት ፥ አቅማዳ ፥ የቡና ፥ የጨው ፥ መክተቻ ።

ጭልጊ ፤ የሰው ፥ ስም ።

አጠለገ ፤ አንድ ፥ ዐይኑን ፥ ገድሎ ፥ ባንድ ፥ ዐይኑ ፥ አየ ፤ አወለገ ፥ አነጣጠረ ።

አጭላጊ ፤ ያጠለገ ፥ የሚያጠልግ ፤ አውላጊ ፥ አነጣጣሪ ።

አጭልግ ፤ ዝኒ ፥ ከማሁ ፤ አውልግ ።

ማጭለግ ፤ ማውለግ ፥ ማነጣጠር ።

ማጭለጊያ ፤ ማውለጊያ ፥ ቀስት ፥ ጠመንጃ ፥ ደን ።

ጭልጋ ፤ በጐንደር ፥ ክፍል ፥ ያለ ፥ አገር ።

ጭልጎች ፤ ዐይበቶች ፤ የጭልጋ ፥ ሰዎች ።

ጠለደ ፤ (ትግ ፥ ጣለደ) ፤ በጐን ፥ አወጣ ፥ አቀጠለ ፥ አፈጠፈጠ ፥ ለጠፈ ፤ ብዙ ፥ ወለደ ፤ ያገዳ ፥ አኸል ።

ጭላዳ ፥ (ዶች) ፤ የዝንጀሮ ፥ ልጅ ፥ ብዛት ፥ ብዙነት ፥ ያለው ፥ በገደል ፥ በሆድ ፥ ተለጥፎ ፥ የሚያድር ፥ የሚያድግ ።

ጭሉዳ ፤ ቅማ ።

ጭላሃ ፤ ዕንጐጅ ።

ጠለውታ ፤ (ትግ) ፤ ምች ፥ ግርፋት ፥ ገረፍታ ፤ ወረርሽኝ ፥ በሽታ ። ሥሩ ፥ በግእዝ ፥ ጸለወ ፥ ነው ።

ጠለጠ ፤ (ጸለጠ ፥ ሰለጠ) ፤ ጠርሶ ፥ ጠጣ ፤ አነቀረ ፥ (ወብድ፪ ፤ ፲፯) ። (ተረት) ፤ ጠል ጠሽ ፥ ጋግሪ ፥ ካለ ፥ ፈጣሪ ።

ጠላጭ ፥ (ጮች) ፤ የጠለጠ ፥ የሚጠልጥ ፥ አንቃሪ ።

ጭለጣ ፤ የመጠለጥ ፥ ሥራ ።

መጠለጥ ፤ ፈሳሽ ፥ ነገርን ፥ መጠጣት ፥ መጠረስ ፥ ማንቀር ።

መጠለጫ ፤ ዋንጫ ፥ ጥዋ ፥ ትንፋሽ ።

አስጠለጠ ፤ ውሃን ፥ ጠላን ፥ ጠጅን ፥ ወተትን ፥ ኮሶን ፥ አስጠጣ ፥ አስጠረሰ ።

ማስጠለጥ ፤ ማስጠረስ ፥ ማስፈጸም ።

ተጠለጠ ፤ ተጠረሰ ፥ ተነቀረ ።

ጭላጭ ፤ የውሃ ፥ የመጠጥ ፥ ቅሬታ ፥ ንቃሪ ።

ጭልጥ ፤ የተጠለጠ ፥ የተጠረሰ ፥ ያለቀ ።

ጭልጥ ፤ ዕልቅ ፥ ፍጽም ። ፋት ፥ ቢሉ ፥ ጭልጥ ፥ እንዲሉ ።

ጭልጥ ፥ አደረገ ፤ ሽምጥጥ ፥ አደረገ ፤ ጠለጠ ።

ጭልጥ ፥ አለ ፤ ተጠለጠ ።

ጭልጥ ፥ አለ ፤ ፈጽሞ ፥ ኼደ ፥ ነጐደ ፤ ጠፋ ፥ ታጣ ፤ ካይን ፥ ተሰወረ ።

መጠለጥ ፤ መጠረስ ፥ መፈጸም ፥ ማለቅ ።

ተጣለጠ ፤ ተጣረሰ ፥ ተቃዳ ፥ ተቃረረ ።

አጣለጠ ፤ አቃረረ ፥ ከዚያም ፥ ከዚያም ፥ አቃዳ ።

አጣላጭ ፤ ያጣለጠ ፥ የሚያጣልጥ ፥ የሚያቃዳ ።

ማጣለጥ ፤ ማቃዳት ፥ ማቃረር ፥ ማጣረስ ።

ማጣለጫ ፤ ጊዜና ፥ ዕቃ ።

አጨላለጥ ፤ አጨራረስ ፤ መጨለጥ ።

ጨለጨለ ፤ (ጠሊል ፡ ጠለ ፡ ጠለየ) ፤ ረጠበ ፡ ጨበጨበ ፡ ለመለመ ።

(ላሌ) ጨሌ ፤ (ጠላዊ ፡ ዘጠል) ፤ የሣር ፡ ች ግኝ ፡ ፍል ።

(ጥሌ) ጨሌ ፡ (ዎች) ፤ ጠለለ ፡ ጋረደ) ፤ እንደ ፡ ሰመግ ፡ ያለ ፡ ባለቀዳዳ ፡ ጥቃቅን ፡ ቅጠልያ ፡ ጌጥ ፡ ከሰደፍ ፡ ከብርጭቆ ፡ ዐፈር ፡ የተበጀ ፤ ነጭ ፡ ጥቁር ፡ ቀይ ፡ ብጫ ፡ አረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ የሀንድ ፡ አገር ፡ ሥራ ፤ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ባረመኔዎች ፡ ዘንድ ፡ የተለመደ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ያንዳንድ ፡ ነገደ ፡ ባላባቶችና ፡ ሚስቶቻቸው ፡ ጎፍረታቸውን ፡ ይከልሉበታል ። አረማውያንም ፡ ጨው ፡ ያልገባበት ፡ እንቀት ፡ ጌሾ ፡ የሌለበት ፡ ጮሽ ፡ አዘጋጅተው ፡ ጨሌውን ፡ ካንገታቸው ፡ ያጠልቁና ፡ የግንብ ፡ የውሃ ፡ የዘመቻ ፡ አቴቴ ፡ «አቴቴ ፡ ግንቢ ፡ አቴቴ ፡ ሐራ ፡ አቴቴ ፡ ዱላ» ፤ እያሉ ፡ በፎ ፡ ዐይነት ፡ አምልኮ ፡ ያመልኩታል ፤ ሌሎችም ፡ ያልተማሩ ፡ ሰዎች ፡ እንደነሱ ፡ ያደርጋሉ ። የአምልኮውንም ፡ ሥርዐት ፡ (ፈጣሳ) ፡ መዝራት ፡ ይሉታል ። ነጭንና ፡ ቀዩን ፡ የዱላ ፤ ጥቁሩንና ፡ ነጩን ፡ የግንቢ ፤ አረንጓዴውን ፡ የሐራ ፡ ይሉታል ። አቴቴን ፡ እይ ።

ጨሌ ፡ ጣይ ፤ ጨሌ ፡ የሚጥል ፡ በጨሌ ፡ የሚጠነቀል ፡ ኽርተኛ ። ስንድድን ፡ ተመልከት ።

ጭልጭል ፡ አለ ፤ መብቀል ፡ ዠመረ ።

ጭልጭል ፡ አለ ፡ ጨር ፡ ጨር ፡ አለ ፤ አነሰ ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ ወረደ ፡ ፈሰሰ ።

ጭልጭል ፡ አለበት ፤ እንደ ፡ ጨሌ ፡ ቀዳዳ ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ ታየው ፡ ታሰበው ። ጭላንጭልን ፡ እይ ።

አጨለጨለ ፤ (ላሌ) ጨሌ ፡ አበቀለ ፡ አወጣ ፡ አለመለመ ፡ በላይ ፡ አደረገ ።

አጨለጨለ ፤ ጭላንጭል ፡ አሳየ ።

ማጨልጨል ፤ ማብቀል ፡ ማለምለም ።

ጭልጭሌ ፤ ዐይነ ፡ ትንሽሽ ።

ጨለያ ፤ በርበሬ ፡ በብዙ ፡ የሚበቅልበት ፡ አገር ። በጋልኛ ፡ ምርት ፡ ማለት ፡ ነው ።

ጨለኸ ፤ (ጸልሐ) ፤ በጣም ፡ ደረቀ ፡ ቀለዘ ፡ ከረረ ።

ጨለኼ ፤ ደረቅ ፡ ከራራ ፡ ዕንጨት ፡ መጥረቢያ ፡ የሚያጠርስ ፡ የሚቸረችም ፤ በቁሙ ፡ ተልጦ ፡ የደረቀ ፡ ወይም ፡ ወድቆ ፡ ፀሓይና ፡ ዝናም ፡ የመታው ።

መጨለኸ ፤ መድረቅ ፡ መከረር ፡ መቅለዝ ።

ጨላላ ፤ (ጠለለ ፡ ጠላላ) ፤ ባዶ ፡ ሜዳ ፡ አውላላ ፡ ሣር ፡ ቅጠል ፡ የሌለበት ፡ ጭው ፡ ያለ ።

ጭልል ፡ አለ ፤ አንዳች ፡ አልባ ፡ ኾነ ፤ ባሕር ፡ መሰለ ።

ጭላሎ ፤ (ጽላሎት) ፤ ባሩሲ ፡ አውራጃ ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ተራራ ፡ ደናም ፡ ጉማም ።

ጨለመ ፤ (ጸልመ) ፤ ብርሃን ፡ ፀሓይ ፡ ታጣ ፡ ደመነ ፡ ደነገዘ ፤ ማታ ፡ ኾነ ፤ ላይን ፡ ያዘ ፤ አልታይ ፡ አለ ፤ ጠቁረ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጨለመ ፡ ፈንታ ፡ ተጨለመ ፡ ይላል ፤ ስሕተት ፡ ነው ፡ (ኤር፤፬ ፡ ፬) ። ጠለመን ፡ እይ ።

ጨለመ ፤ ጋረደ ፡ ከለለ ።

ጨለምኸኝ ፤ አላሳይ ፡ አልኸኝ ። (አትጨለመኝ) ፤ አትከልለኝ ።

ጨላሚ ፤ የሚጨልም ።

ጨላማ ፤ (ጥላማ) የጨለመ ።

ጨለማ ፤ (ጽልመት) ፤ የማታ ፡ የሌሊት ፡ ሰዓት ፡ ውድቅት ፤ ዐይን ፡ ቢወጉ ፡ የማይታይበት ፡ ጊዜ ። (የቀን ፡ ጨለማ) ፤ ጉም ፡ ዐፈና ፤ አለማየት ፡ ዕውርነት ።

ጨለማ ፡ ፌት ፤ ጠለምቱ ፡ ሻንቅላ ፡ ፌተ ፡ ጥቁር ።

ጨለማ ፡ ተገን ፤ የጨለማ ፡ ከለላ ። ዐለመ ፡ ብለኽ ፡ ዓለምን ፡ አስተውል ።

ጭለማ ፤ ጨለማ ፡ መኾን ፤ ጥቁረት ።

ጭልምታ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ድግዝታ ።

ጨለም ፤ (ጸሊም) ፤ መጨለም ።

ጨለም ፡ አለ ፤ ጨለመ ።

መጨለም ፤ ጨለማ ፡ መኾን ፡ መጥቁር ፡ መደመን ፡ መደንገዝ ።

መጨለሚያ ፤ ምሽት ፡ ማታ ።

ጨላለመ ፤ ጠቋቁረ ።

አጨለመ ፤ (አጽለመ) ፤ ሸፈነ ፡ ጨፈነ ፡ ዘጋ ፤ አጠቁረ ፤ አደነገዘ ፡ (ሰቈጀ ፡ ፩) ። ኹለተኛውን ፡ ጨለመ ፡ እይ ።

አጨላሚ ፤ ያጨለመ ፡ የሚያጨልም ፤ ጨለማ ፡ አድራጊ ።

ማጨለም ፤ ማጥቁር ፡ ማደንገዝ ።

ማጨለሚያ ፤ መድፈኛ ፡ መዝጊያ ።

አስጨለመ ፤ ጨለማ ፡ አስደረገ ።

አጭለመለመ ፤ አጭፈነፈነ ፡ አድመነመነ ።

ተጭለመለመ ፤ ተድመነመነ ፡ ተጭፈነፈነ ።

ጭልምልም ፤ ጭፍንፍን ።

ጭልምልም ፡ አለ ፤ ፈጽሞ ፡ ጨለመ ፤ ድንግዝግዝ ፡ ድምንምን ፡ አለ ።

ጭልምልምታ ፤ ድንግዝግዝታ ፡ ስልምልምታ ።

አጨላለም ፤ አከላለል ፤ መጨለም ።

ጭላንጭል ፤ (ጨለጨለ) ፤ ጥቃቅን ፥ የጣራና ፥ የግድግዳ ፥ ቀዳዳ ፥ የጨሌ ፥ ብስ ፥ የሚያካክል ፥ የጨረር ፥ ፍንጣቂ ፥ ሰልቶ ፥ የሚገባበት ። ሲበዛ ፥ ጭላንጭሎች ፥ ይላል ።

ጭላንጭል ፤ ከፉ ፥ ቀን ፥ ሲወጣ ፥ የነበረ ፥ ጊዜ ፤ የረኃብ ፥ ጨለማ ፥ እየፈገገ ፥ የጥጋብ ፥ ውጋጋን ፥ ሲታይ ፤ (አሲድ ፥ ተቀነሰ ፤ በረከት ፥ ተዝመረ) ።

ጨሌንካ ፤ የለምድ ፥ የካባ ፥ መጋጠሚያ ፥ ሳንቃ ።

ጨለፈ ፤ (ጠለፈ) ፤ ጠለቀ ፥ ቀዳ ፥ አወጣ ፥ ወጣን ።

ፀለፈ ፤ ነጠቀ ፥ ቀማ ።

ጨላፊ ፤ የጨለፈ ፥ የሚጨልፍ ፤ ወጠ ፥ ቀጂ ።

ጭለፋ ፤ የመጥለቅ ፥ የመቅዳት ፥ ሥራ ።

ጭልፋ ፥ (ፎች) ፤ ከንጨት ፥ ከብረት ፥ ከብር ፥ ከቅል ፥ የተበጀ ፥ ዕቃ ፥ ከድስት ፥ ወጥ ፥ መቅጃና ፥ ማውጫ ፥ ትልቁም ፥ ትንሹም ፥ (ዘጉሂ ፤ ፲፫ ፥ ፲፱) ።



ጭልፋ ፥

ጭልፊት ፥ (ቶች) ፤ ዶሮን ፥ ሥጋን ፥ ዓሣን ፥ የምትነጥቅ ፥ አሞራ ፥ ባምሌና ፥ በናሴ ፥ የማት ታይ ። ጭላትን ፥ ተመልከት ።



ጭልፊት ፥

ጭሉፋት ፥ (ቶች) ፤ እንደ ፥ ጭልፊት ፥ ድንገት ፥ የሚነጥቅ ፤ ጭልፊትዊ ፥ ቀማኛ ፥ ነጣቂ ።

መጨለፍ ፤ ወጥን ፥ መቅዳት ፥ ማውጣት ።

መጨለፊያ ፤ ጊዜ ፥ ጭልፋ ።

አስጨለፈ ፤ አስጠለቀ ፥ አስቀዳ ፥ ወጥ ፥ አስወጣ ።

አስጨላፊ ፤ ያስጨለፈ ፥ የሚያስጨልፍ ፤ አስቀጅ ።

ማስጨለፍ ፤ ማሰጠለት ፥ ማስቀዳት ።

ማስጨለፊያ ፤ ማስቀጃ ፥ ሳሕን ፥ ወጭት ።

ተጨለፈ ፤ ተጠለቀ ፥ ተቀዳ ፥ ከሰታቴ ፥ ከአፍላል ፥ ወጣ ።

ተጨላፊ ፤ የሚጨለፍ ፥ የሚቀዳ ።

ጭላፊ ፤ ጭልፍ ፤ የተጨለፈ ፥ የተቀዳ ፥ ወጥ ፥ መረቅ ።

አጫለፈ ፤ ወጥን ፥ በጭልፋ ፥ አቃዳ ።

አጨላለፍ ፤ አቀዳድ ፤ መጨለፍ ። ሞጨለፈን ፥ እይ ፤ የጨለፈ ፥ ዘር ፥ ነው ።

ጨለቀ ፤ (ትግ ፥ ጨለቀ ፤ ዐነጐተ) ፤ እንደ ፥ ዕንጉቻ ፥ ያለ ፥ የተልባን ፥ ልጥልጥ ፥ ዐሸ ፥ በጠበጠ ፤ ከግር ፥ ጋራ ፥ በውሃ ፥ መታ ። በግእዝ ፥ ሥሩ ፥ ጠለቀ ፥ ነው ። ደረጠን ፥ አስተውል ።

ጨላቂ ፤ የጨለቀ ፥ የሚጨልቅ ፤ ዐሺ ፥ በጥባጭ ።

መጨለቅ ፤ ማሸት ፥ መበጥበጥ ።

መጨለቂያ ፤ ማሻ ፥ ጣባ ፥ ገበቴ ።

አስጨለቀ ፤ አስበጠበጠ ፤ አስመታ ።

ተጨለቀ ፤ ታሸ ፥ ተበጠበጠ ፤ ተመታ ።

ጭልቃ ፤ የተጨለቀ ፥ የተበጠበጠ ፤ ብጥ ብጥ ፥ ተልባ ።

ጨላቃ ፤ ጨምጣማ ፥ ድፍርስ ፥ ዐይን ።

ጨለቅለቃ ፤ የተኛ ፥ ውሃ ፤ የሚያንጸበርቅ ፥ ኩሬ ፥ ጭቃማ ።

አጨላለቅ ፤ አበጣበጥ ፤ መጨለቅ ።

ጭላት ፤ ነጣቂ ፥ አሞራ ፥ የዶሮ ፥ የወፍ ፥ ጠላት ፥ ጭልፊት ፥ ሲላ ፥ ገዲ ፥ (ኢዮ፴፱ ፤ ፳፰) ።

ጫማ ፤ (ጸመወ) ፤ ለፋ ፥ ደከመ ፤ ጣመነ ፥ ካከመ ።

ጫማ ፤ ጫማና ፥ ጫሜ ፥ አበጀ ፥ ሠራ ። ያለፈው ፥ አንቀጽ ፥ የሚመጣው ፥ ስም ፥ መኾኑን ፥ አስተውል ።

ጭማ ፥ (ሞች) ፤ ሰኰና ፥ ከቀሩጭምጭሚት ፥ በታች ፥ ያለ ፥ የእግር ፥ ዠርባና ፥ ውስጥ ፥ መርገጫ ፥ መኼጃ ፥ (ጸማ) ፥ ድካም ፥ ጣመን ፥ የሚሰማው ፥ (ዘዳ፳፰ ፥ ፳፭) ። (የደም ፥ ጫማ) ፤ ጋሬጣ ፥ የወጋው ፥ ዕንቅፋት ፥ የመታው ፥ ደሙን ፥ ያፈሰሰው ።

ጫማ ፤ ርምጃ ፤ የጫማ ፥ ስፍር ፤ ወይም ፥ ልክ ።

ጭማ ፥ ሳመ ፤ ጭም ፥ አደረገ ።

ጫማ ፤ መጫሚያ ፥ የእግር ፥ ቤዛ ፥ (ማሕ ፯ ፥ ፱ ። ኢሳ፭ ፥ ፳፭ ። ዓሞ፪ ፥ ፮) ። ጫማ ፥ ሰፌ ፥ ነጠላ ፥ ጫማ ፥ ኩፍ ፥ ጫማ ፥ የወርቅ ፥ ጫማ ፥ የንጪት ፥ ጫማ ፥ እንዲሉ ። ጫማን ፥ መጫሚያ ፥ ማለት ፥ ጎዳሪ ፥ በማጎደር ፥ ነው ። ሰዎች ፥ በማለት ፥ ፈንታ ፥ ቤቶች ፥ እንዲሉ ። ነገር ፥ ግን ፥ ገላንና ፥ ዕቃን ፥ ባንድ ፥ ስም ፥ መጥራት ፥ አይገባም ።

ጭማሬ ፤ (ጭማዊ) ፤ የጫማ ፥ ዐይነት ፤ የጐራዴ ፥ ጫፍ ፥ ጌጥ ፥ ሎሚታ ፥ ያለውና ፥ የሌለው ፥ ከብርና ፥ ከወርቅ ፥ የተሠራ ፥ ሽልማት ። ከሰገባው ፥ ጋራ ፥ እንደ ፥ ጫማ ፥ ይዋደዳል ።

ተጫማ ፤ (ተሥእነ) ፤ ጫማ ፥ ለበሰ ፥ አጠለቀ ፤ ኹለት ፥ እግሩን ፥ ከጫማ ፥ አገባ ፥ (ኤፌ ፮ ፥ ፲፭) ።

ተጫሚ ፤ የሚጫማ ።

መጫማት ፤ ጫማ ፣ መልበስ ።

መጫሚያ ፤ የጫማ ፣ ማጌጃ ፣ ዐቃፋ ፣ ብረት ። ፈረንጆች ፣ ፖስፒዬ ፣ ይሉታል ።

መጫሚያ ፣ (ዎች) ፤ ሣእን) ፤ ጫማ ፣ የእግር ፣ ልብስ ፣ ከማስ ፣ ከነት ፣ ከባሕር ፣ ዐረብ ፣ ከሸራ ፣ የተሰፋ ፤ ከንጨት ፣ የተበጀ ፣ በወርቅ ፣ የተጌጠ ።



መጫሚያ ፣

አጫማ ፤ (አሥእነ) ፤ ለጫማ ፣ መጫሚያን ፣ አለበሰ ፤ ጠለፈ ፣ ዐዘበ ፣ ቄለፈ ፣ (ሕዝ፲፮ ፣ ፲) ። ነገር ፣ ግን ፣ የተጫማና ፣ የአጫማ ፣ ርግጠኛ ፣ ትርጓሜ ፣ ተላበሰና ፣ አላበሰ ፣ ነው ።

አጫሚ ፤ ያጫማ ፣ የሚያጫማ ።

ማጫማት ፤ መጫሚያ ፣ ማልበስ ።

ጮማ ፤ (ጋላ) ፤ ሥብ ፣ የሠባ ፣ ሥጋ ፣ ቅልጥ ፣ ያለ ።

ጮማም ፤ ጮማ ፣ ያለው ፣ ፍሪዳ ፣ (ጅነን ፣ ፩ ፣ ፱) ።

ጮማነት ፤ ጮማ ፣ መኾን ፤ ሥብነት ።

ጨመገገ ፤ ጨፈገገ ፤ ግንባሩን ፣ ጸጠረ ።

ተጨመገገ ፤ ተጨፈገገ ፤ ተጸጠረ ።

ጨምጋጋ ፤ ጨፍጋጋ ።

ጫመደ ፤ ተገረሙ ፣ ተበላ ። ሽመደን ፣ ተመልከት ።

አጫመደ ፤ ገረሙ ፣ በላ ፣ ገመጠ ፣ እንጀራን ፣ በብዙ ።

ጨመደደ ፤ (ጠመደ) ፤ ጨመተረ ፣ ሸበሸበ ፣ ልብስን ፣ ቄዳን ፣ ፊትን ፤ ትክክልነትንና ፣ ቀጥታን ፣ አራቀ ፤ ሸመቀቀ ። ወጥማዳን ፣ እይ ።

ጨመደደ ፤ አጥብቆ ፣ ያዘ ።

ጨምዳጅ ፤ የጨመደደ ፣ የሚጨመድድ ፤ ጨምታሪ ።

መጨምደድ ፤ መጨምተር ።

መጨምደጃ ፤ መጨምተሪያ ፣ መሸብሸቢያ ፣ መርፌ ፣ ወስፌ ፣ ክር ፣ ሚር ።

ተጨመደደ ፤ ተጨመተረ ፣ ተሸበሸበ ፤ ወጣ ፣ ገባ ፣ ጉነ ።

ጨመደድ ፤ ጨምዳዳ ፤ የተጨመደደ ፤ ጨምታራ ። (ተረት) ፣ ከቀዳዳ ፣ ይሻላል ፣ ጨምዳዳ ።

ጭምድድ ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ፤ ጭምትር ።

ጭምድድ ፣ አለ ፤ ጭምትር ፣ አለ ።

ተጨማደደ ፤ ተጨማተረ ፣ ተሸማቀቀ ።

ተጨማዳጅ ፤ የሚጨማደድ ፣ ልብስ ።

መጨማደድ ፤ መጨማተር ፣ መሸማቀቅ ።

መጨማደጃ ፤ መጨማተሪያ ፤ ያላዋቂ ፣ ስፌት ፣ እርጅና ፣ ጥብጣብ ፣ ሽምቀቆ ።

አጨማደደ ፤ አጨማተረ ፣ አሸማቀቀ ፣ አሸባሸበ ። ባልና ፣ አጨማደደ ፣ አለ ፣ ባማርኛ ፣ ይተባበራሉ ። (ግጥም) ፤ ያችን ፣ ቀጪን ፣ ኩታ ፣ ሆዴ ፣ እየወደዳት ፤ አላዋቂ ፣ ስፌ ፣ ባላጨማደዳት ።

ማጨማደድ ፤ ማጨማተር ፣ ማሸማቀቅ ።

ማጨማደጃ ፤ ማጨማተሪያ ፣ ማሸባሸቢያ ።

ጨመጨመ ፤ (ጸመ ፣ ፀመ) ፤ መላልሶ ፣ ሳመ ።

ጨመጨመ ፤ ጠመጠመ ፣ አሰረ ፣ ማገረ ፣ አጠጋጋ ።

ጨመጨመ ፤ በቀስታ ፣ ሰማ ።

ጨምጫሚ ፤ የጨመጨመ ፣ የሚጨመጭም ፤ ሳሚ ፣ ጠምጣሚ ፣ አሳሪ ፣ ማጋሪ ።

ጨምጨሞ ፣ (ዎች) ፤ በዋልታ ፣ ዙሪያ ፣ ያለ ፣ ብዙ ፣ ማገር ፣ የተጠጋጋ ፣ የተቀራረበ ።

ጭምጭማት ፤ የጨምጨሞ ፣ አሠራር ፣ ዅናቴ ።

ጭምጫሚ ፤ ጭምጭምታ ፤ (ጽሚት) ፤ ያልተረገጠ ፣ ድብቅ ፣ ወሬ ፣ በዝግታ ፣ የሚነገር ፣ የሚሰማ ።

መጨምጨም ፤ አፍን ፣ ካፍ ፣ ገጥሞ ፣ መላልሶ ፣ መሳም ።

መጨምጨም ፤ መጠምጠም ፣ ማሰር ፣ መማገር ።

መጨምጨሚያ ፤ መሳሚያ ፣ መማገሪያ ፣ ከንፈር ፣ ገመድ ፣ ጠንበለል ።

አጨመጨመ ፤ አመጨመጨ ።

አስጨመጨመ ፤ አሳመ ።

አስጨመጨመ ፤ አስጠመጠመ ፣ አሳሰረ ፣ አስማገረ ።

አስጨምጫሚ ፤ ያስጨመጨመ ፣ የሚያስጨመጭም ፤ አሳሚ ፣ አስማጋሪ ።

ተጨመጨመ ፤ ተሳመ ።

ተጨመጨመ ፤ ተጠመጠመ ፣ ተማገረ ፣ ተጠጋጋ ።

ተጨምጫሚ ፤ የሚጨመጨም ፤ ተሳሚ ፣ ተማጋሪ ።

ጭምጭም ፤ የተጨመጨመ ፣ የተሳመ ፣ የተማገረ ።

ጭም ፣ አደረገ ፤ ሳም ፣ አደረገ ።

ጭም ፣ ጭም ፣ አደረገ ፤ ሳም ፣ ሳም ፣ አደረገ ።

ጨምጫማ ፤ (ጸምላጥ) ፤ ቅንድቡ ፣ የተ

ጋጠመ ፤ ቄፍንፍን ፡ እንባው ፡ የማይቆም ። ዐይነ ፡ ጨምጣማ ፡ እንዲሉ ። መጨመጨን ፡ እይ ።

ተጨማጨመ ፤ ተሳሳመ ።

መጨማጨም ፤ መሳሳም ።

አጨማጨመ ፤ አሳሳመ ።

አጨማጨመ ፤ ጨምጨሞ ፡ አስተሳሰረ ፡ አማገረ ፡ አባጀ ።

አጨማጨም ፤ አሳሳም ፡ አመጋገር ፤ መጨምጨም ።

(ጨመለቀ) ፤ ተጨማለቀ ፤ ተደፋጨ ፤ ጭቃ ፡ ተቀባ ፡ ተበከለ ፡ ተኮለፈለፈ ። ጨለቀን ፡ እይ ፤ ሥሩ ፡ ርሱ ፡ ነው ።

ተጨማለቀ ፤ ነገር ፡ አበዛ ፤ ችክ ፡ ምን ችክ ፡ አለ ። ለፈደደን ፡ ተመልከት ።

ጨመለቅ ፤ ጨምላቃ ፤ የተጨማለቀ ፤ ነገረ ፡ በክ ፡ ችኮ ።

ጭምላቂ ፤ ጭምልቅ ፤ ጭምላቆ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ኩልፍልፍ ።

መጨማለቅ ፤ መበከል ፡ መኮለፍለፍ ።

መጨማለቂያ ፤ ጭቃ ፡ ረግረግ ።

ተጨመላለቀ ፤ የተጨማለቀ ፡ ድርብ ፤ በብዙ ፡ ወገን ፡ በፊት ፡ በኋላ ፡ በቀኝ ፡ በግራ ፡ ተዳደፈ ።

ጭምልቅልቅ ፤ የተጨመላለቀ ፡ ዅለንተናው ፡ ጭቃ ።

ጭምልቅልቅ ፡ አለ ፤ ኩልፍልፍ ፡ አለ ፤ ተጨመላለቀ ።

አጨማለቀ ፤ አጨቀየ ፡ አደፋጨ ፡ አረሰ ፡ ጭቃ ፡ አደረገ ፡ አሳደፈ ፡ አኮለፈለፈ ። ጨፈለቀን ፡ አስተውል ።

አጨማላቂ ፤ ያጨማለቀ ፡ የሚያጨማልቅ ።

ማጨማለቅ ፤ ማጨቅየት ፡ ማደፋጨት ።

ማጨማለቂያ ፤ ሊጥ ፡ ቅባት ፡ ቀለም ፡ ዘይት ፡ ዐዛባ ።

አጨመላለቀ ፤ የአጨማለቀ ፡ ድርብ ፤ አስተዳደፈ ።

ማጨመላለቅ ፤ ማስተዳደፍ ።

አጨመላለቀ ፤ አስተዳደፍ ፤ ማጨማለቅ ።

ጨመቀ ፤ (ጠመቀ ። ጸመቀ ፡ ዐጸረ) ፤ ርጥብ ፡ ልብስን ፡ የወይን ፡ እሸትን ፡ የሴቴ ፡ ወይራ ፡ ፍሬን ፡ ድፍድፍን ፡ ሰፈፍን ፡ አጥብቆ ፡ ጠበጠ ፡ ፍጨቴን ፡ ተማነ ፡ አድፈጠፈጠ ፤ ጠመዘዘ ፡ አጠራ ፡ አንጠፈጠፈ ፡ ውሃን ፡ ደምን ፡ ዘይትን ፡ ጠላን ፡ ሠምን ፡ ለማውጣት ።

ጨመቀ ፤ ካይኑ ፡ እንባን ፡ አፈሰሰ ።

ጨማቂ ፡ (ቆች) ፤ የጨመቀ ፡ የሚጨምቅ ፤ ጠምዛዥ ፡ አጥሪ ።

መጭመቅ ፤ መጨቈን ፡ መጫን ፡ መጠም ዘዝ ፡ ማፍሰስ ፡ ማጥራት ።

መጭመቂያ ፤ (ምክያድ) ፤ የወይን ፡ ጕድጓድ ፡ አለት ፡ እጅ ፡ ወንፊት ፡ ዝተት ፡ በለሴ ፡ ዋዲያት ፡ ማጥሪያ ።

ተጨመቀ ፤ ተጨቈነ ፡ ተጠመዘዘ ፡ ተንጠፈጠፈ ፤ ውሃው ፡ ጥሩው ፡ ወሰላው ፡ ወረደ ።

ጭማቂ ፤ የተጨመቀ ፤ ጥማቂ ። የዚህ ፡ ዓለም ፡ እሳት ፡ ለወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ እሳት ፡ የኔ ፡ ጊዜ ፡ ጭማቂው ፡ ነው ፡ ይባላል ፡ (አፈ ፡ ጨዋ) ።

ጭምቅ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ (ቅጽል) ።

(ጥቅ) ጭምቅ ፤ የቅጠል ፡ ስም ፤ መርዝነት ፡ ያለው ፡ ዕፅ ፤ ሰዎች ፡ በውዳቂ ፡ ሥጋ ፡ ላይ ፡ ብናኙን ፡ እየ ነሰነሱ ፡ እንበሳን ፡ ነብርን ፡ ዥብን ፤ በውሃ ፡ እየ በጠበጡ ፡ ዝንጀሮን ፡ የሚገድሉበት ፡ ክፉ ፡ መድ ኀኒት ፤ (ስም) ።

ጭምቆ ፤ ተጨምቆ ፡ በወንፊት ፡ የተጣራ ፡ ጮሽ ።

አጫመቀ ፤ አጠማዘዘ ፡ አጠናፈፈ ፡ አጣራ ።

አጨማመቅ ፤ አጠመዛዘዝ ፤ መጭመቅ ። ጠመቀን ፡ እይ ፤ ጨመቀ ፡ የሕዝብ ፤ ጠመቀ ፡ የክህናት ፡ ነው ።

ጨመረ ፤ (ፀመረ) ፤ አገባ ፡ ዶለ ፡ ከተተ ፡ አሰናዳ ።

ጨመረ ፤ አከለ ፡ ደበለ ፤ አንድ ፡ አደረገ ።

ጨማሪ ፡ (ዎች) ፤ የጨመረ ፡ የሚጨምር ፤ ከታች ፡ አሰናጂ ።

ጭመራ ፤ የመጨመር ፡ ሥራ ፤ አከላ ።

መጨመር ፤ ማግባት ፡ ማሰናዳት ፡ ማከል ፡ (ማቴ፯ ፡ ፭፪) ።

መጨመሪያ ፤ ማሰናጃ ፡ ማኪያ ፡ ውስጥ ።

ጨማመረ ፤ (ፀማመረ) ፤ አገባባ ፡ አሰነዳዳ ።

ጨማመረ ፤ አካከለ ፡ በላይ ፡ በላዩ ።

መጨማመር ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዅለት ፡ ጊዜ ፡ መጨመር ።

አስጨመረ ፤ አስገባ ፡ አስዶለ ፡ አስከተተ ።

አስጨመረ ፤ አሳከለ ፡ አስደበለ ።

አስጨማሪ ፤ ያስጨመረ ፡ የሚያስጨምር ።

ማስጨመር ፤ ማሳከል ፡ ማስደበል ።

ማስጨመሪያ ፤ ማስገቢያ ፡ ማስከተቻ ፡ ዕቃ ፡ ጊዜ ።

ተጨመረ ፤ (ተፀመረ) ፤ ገባ ፡ ተዶለ ፡ ተከተተ ፡ ተሰናዳ ፡ (ማቴ፭ ፡ ፭፫) ።

ተጨመረ ፤ ታከለ ፤ አንድ ፡ ዅነ ፡ ዐበረ ።

ተጨማሪ ፤ የሚጨመር ፥ የሚታከል ፤ ሌላ ፥ ኹለተኛ ። ተጨማሪ ፥ ዲያቆን ፥ እንዲሉ ።

ተጨማሪነት ፤ ተጨማሪ ፥ መኾን ፤ ዐባሪነት ።

ተጨምሮ ፤ ታክሎ ። (ተረት) ፤ በደንባሪ ፥ በቅሎ ፥ ቃጭል ፥ ተጨምሮ ።

ጭማሪ ፤ (ተውሳክ) ፤ ትርፍ ፥ ነገር ፥ ቀድሞ ፥ ያልነበረ ፥ ኋላ ፥ የታከለ ።

ጭምር ፤ (ዕሙር) ፤ የተጨመረ ፥ የገባ ።

ጭምር ፤ ንኡስ ፥ አገባብ ፤ አንድነት ፥ አድርጎ ። እከሌን ፥ ዐይኑን ፥ ጭምር ፥ ራሱን ፥ ያመዋል ። ጋራን ፥ ተመልከት ።

ተጨማመረ ፤ ተባበረ ፥ ተነባበረ ፥ ተደራረበ ።

ተጨማማሪ ፤ የሚጨማመር ፤ ተነባባሪ ።

ጭምርማሪ ፤ የተጨማመረ ።

አጫመረ ፤ አጨማመረ ፤ አጋባ ፥ አደጅ ፥ አካተተ ፥ አሰነዳዳ ።

አጫማሪ ፤ ያጫመረ ፥ የሚያጫምር ።

ማጫመር ፤ ማጨማመር ፤ ማጋባት ፥ ማካተት ።

አጨማመር ፤ አሰነዳድ ፤ መጨመር ።

ጨመተ ፤ (ጸመወ) ፤ አረመመ ፤ ዝምተኛ ፥ ኾነ ፤ ዝም ፥ ዕከም ፥ አለ ፤ (ኢዮ፤ ፳፮) ።

ጨመተ ፤ (ትግ) ፤ ደከረ ፥ አዘገበ ፥ አነጣጠረ ፥ በርጋታ ።

ጭምት ፥ (ቶች) ፤ ጽምው) ፤ የጨመተ ፥ የረጋ ፥ ደኅና ፥ ሰው ፥ ድምጡ ፥ የማይሰማ ፥ ዝምተኛ ፥ (ዘፍ፳፭ ፤ ፳፯) ። (ተረት) ፤ ጭምት ፥ ሲሞት ፥ ልቡን ፤ ንጉሥ ፥ ሲሞት ፥ ግንቡን ።

ጭምትነት ፤ ጭምት ፥ መኾን ።

ጭመታ ፤ (ጽማዌ) ፤ የመጨመት ፥ ሥራ ፤ ርጋታ ፥ ዝምታ ።

መጨመት ፤ ማርመም ፤ ዝም ፥ ማለት ፥ አለመናገር ፥ መርጋት ፥ ለነገር ፥ አለመቸኰል ፥ አለመለፍለፍ ፥ አለመቀባጠር ።

መጨመቻ ፤ ማርመሚያ ፥ ዝም ፥ ማያ ፥ ጊዜ ፥ ስፍራ ፥ በአት ።

አጨመተ ፤ ጭምት ፥ አደረገ ፤ አረጋ ።

አስጨመተ ፤ ዝም ፥ አሠኘ ፤ አስረመመ ።

ማስጨመት ፤ ዝምተኛ ፥ ማስደረግ ።

ጨምቶ ፤ ዝም ፥ ብሎ ፥ ረግቶ ፥ (ማር፭ ፤ ፲፩) ።

አጨማመት ፤ አረማመም ፤ መጨመት ።

ጨመተረ ፤ ኰመተረ ፥ ጨመደደ ፥ እሳት ፥ ቁዳን ፤ እርጅና ፥ ፊትን ። ጨረመተን ፥ አስተውል ፤ ከፊደል ፥ መዛወር ፥ በቀር ፥ ከዚህ ፥ ጋራ ፥ አንድ ፥ ነው ።

ተጨመተረ ፤ ተኰመተረ ፥ ተጨመደደ ።

ጨምታራ ፤ ኰምታራ ፥ ጨምዳዳ ።

ጭምትር ፤ የተጨመተረ ፤ ጭምድድ ።

ተጨማተረ ፤ ተኰማተረ ፥ ተጨማደደ ።

መጨማተር ፤ መኰማተር ፥ መጨማደድ ።

መጨማተሪያ ፤ መጨማደጃ ፥ ፀሓይ ፥ ምች ።

ተጨመታተረ ፤ ተኰመታተረ ፥ ተጨመዳደደ ።

ጭምትርትር ፤ የተጨመታተረ ፤ ኵምትርትር ።

ጭምትርትር ፥ አለ ፤ ኵምትርትር ፥ አለ ፤ ተጨመታተረ ።

አጨማተረ ፤ አኰማተረ ፥ አጨማደደ ።

አጨማታሪ ፤ ያጨማተረ ፥ የሚያጨማትር ፤ አጨማዳጅ ።

ማጨማተር ፤ ማኰማተር ፥ ማጨማደድ ።

አጨመታተረ ፤ አኰመታተረ ፥ አጨመዳደደ ።

ማጨመታተር ፤ ማጨመዳደድ ።

አጨመታተር ፤ አጨመዳደድ ፤ ማጨማተር ።

ጨኖ ፥ (ምች) ፤ ያውሬ ፥ ስም ፤ ገጥታው ፥ ኹናቴው ፥ የጭላዳ ፤ ጠጉሩ ፥ የጉሬዛ ። በታላቅ ፥ ተራራና ፥ በቋጥኝ ፥ ላይ ፥ ይኖራል ፤ ሥራሥርና ፥ የዛፍ ፥ ፍሬ ፥ ተንቀሳቃሽ ፥ ይበላል ። ፈረንጆች ፥ ዤላዳ ፥ ይሉታል ።



ጨኖ ፥

ጨኖ ፤ ያገር ፥ ስም ፤ በይፋት ፥ አውራጃ ፥ ያለ ፥ ገጠር ። ጨኖ ፥ ገበያ ፥ እንዲሉ ።

ጫነ ፤ (ጸዐነ) ፤ ኮርቻን ፥ ጭነትን ፥ በበቅሎ ፥ በፈረስ ፥ ባህያ ፥ በግመል ፥ በበሬ ፥ በዝሆን ፥ ዦርባ ፥ አደረገ ፥ አሰረ ፤ መጫኛን ፥ ላገ ፥ የተጫነውን ፥ ዐረቀ ። (ተረት) ፤ ጫን ፥ ያለው ፥ ኮርቻውን ፥ ለምን ፥ ያለው ፥ ስልቻውን ፥ አያጣውም ። ቀነበረ ፥ ብለኸ ፥ ቀንበርን ፥ አይ ።

ጫነ ፤ ማንኛውንም ፡ ሸክም ፡ ለሰው ፡ አሸከመ ፡ አሳዘለ ፤ በጨፈቃ ፡ በመቃብር ፡ በሚ ታረቅ ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ ደንጊያን ፡ ግንድን ፡ አከ በደ ፤ ባንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ (መዳፉን) ፡ አኖረ ።

ጫነ ፤ ዘውድ ፡ ደፋ ፡ ተቀዳጀ ፡ ነገሠ ፤ (አቀዳጀ ፡ አነገሠ) ።

ጫነ ፤ ቅኔ ፡ ቄጥሮ ፡ መንገር ፡ መቀኘት ፡ ለማይችል ፡ ተማሪ ፡ የራሱን ፡ ቅኔ ፡ ነገረ ፡ አስጠና ።

ጫኝ ፡ (ኞች) ፤ የጫነ ፡ የሚጭን ፤ ለጓሚ ፡ ጕረደማን ።

ጫኝ ፤ በጉዞ ፡ በዘመቻ ፡ ጊዜ ፡ የንጉሥ ፡ ዕቃ ፡ የሚጭን ፡ ሰራዊት ፡ ስም ፤ ደንቡ ፡ ጭነት ፡ የኾነ ፡ ጭፍራ ።

ጫና ፤ ጭቈና ፡ የመጨቈን ፡ ሥራ ። የአ ከሌ ፡ እዝ ፡ የጫና ፡ ነው ።

ጫን ፤ የቅርብ ፡ ወንድ ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፤ አንተ ፡ አሽከር ፡ ፈረሱን ፡ ጫን ።

ጫን ፤ የመጠን ፡ የስፍር ፡ ስም ፤ ፫ ፡ ዳ ውላ ፡ እኽል ፡ በቀ‹ና ፡ ፮ ፡ በግድጋ ፡ በእንቅብ ፡ ፯ ፡ በጕርዘኻ ፡ ፲፪ ፡ ይኾናል ፡ (፭ነገ ፡ ፬ ፡ ፭፪ ። ኢ ሳቯ ፡ ፲ ። ሆሴዮ ፡ ፱) ።

ጫነ ፡ በል ፤ ከርሣም ፡ ሆዳም ።

ጭን ፡ (ኖች) ፤ ከጕልበት ፡ በላይ ፡ ከታፋ ፡ በታች ፡ ያለ ፡ አንደኛ ፡ የእግር ፡ ክፍል ፡ ሕፃን ፡ በላዩ ፡ የሚጫንበት ፡ የሚቀመጥበት ፡ (ዘፀ፲፪ ፡ ፱ ። ዮሐ፲፱ ፡ ፴፭ ፡ ፴፪ ፡ ፴፫) ። በትግሪኛ ፡ ግን ፡ ጭን ፡ አጥግቢኝ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ውፍረቷን ፡ ሥጋ ማነቷን ፡ ያስረዳል ። ዘርፍ ፡ ኹኖ ፡ ሲነገር ፤ የጭን ፡ በቅሎ ፡ የጭን ፡ ፈረስ ፡ ይላል ፤ ይኸውም ፡ መቀ መጫነትን ፡ ያሳያል ።

ጭን ፡ ገረድ ፤ (የጭን ፡ ገረድ) ፤ ጌታ ዋን ፡ በጭናጅ ፡ ውስጥ ፡ የምታቅፍ ፡ ወይም ፡ ርሱ ፡ ጭኑን ፡ የሚጭንባት ፡ የመንገድ ፡ የዘመቻ ፡ ጊዜ ፡ ገረድ ፡ ማዕርጓ ፡ ከሚስት ፡ ከቁባት ፡ የሚያንስ ። ገረድን ፡ እይ ።

ጭነ ፡ ጥብቅ ፤ ብርቱ ፡ ፈረሰኛ ።

ጭንና ፡ ጭን ፤ ኹለት ፡ ጭናች ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ያሉ ፡ (ማሕፄ ፡ ፲፭) ።

መጫን ፤ በራስ ፡ በትከሻ ፡ በወገብ ፡ ላይ ፡ ማድረግ ፡ ማስቀመጥ ፡ ማሸከም ፡ (፭ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፱) ። ማሰር ፡ መጨፈቅ ።

መጫኛ ፡ (ኞች) ፤ በክብት ፡ ዠርባ ፡ ላይ ፡ ጭነት ፡ ማሰሪያ ፡ ዕጥፍ ፡ ጠፍር ፤ ወይም ፡ ገመድ ። መጫኛና ፡ ስልቻ ፡ እንዲሉ ። (ውርድ) ፤ ዳኛ ፡ ቢያገድል ፡ በዳኛ ፤ አህያ ፡ ቢያጋድል ፡ በመ ጫኛ ። መዘራዝርን ፡ ሌበቻን ፡ ተመልከት ።

አስጫነ ፤ ጫኑ ፡ አለ ፤ ጫኞችን ፡ አዘዘ ።

አስጫነ ፤ አስጨቈነ ፡ አስጨፈቀ ፡ አስለ ሰቀ ።

አስጫኝ ፤ ያስጫነ ፡ የሚያስጭን ፤ የጫ ኞች ፡ አለቃ ።

ማስጫን ፤ በደንጊያ ፡ ማስጨቈን ፡ ማስ ጨፈቅ ።

ማስጫኛ ፤ የጭነት ፡ ዕቃ ፡ ጊዜ ፡ ስፍራ ።

ተጫነ ፤ (ተጽዕነ) ፤ ጭነትን ፡ ኮርቻን ፡ ተሸከመ ።

ተጫነ ፤ በክብት ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ ተቀ መጠ ። (ሽለላ) ፤ ግፉ ፡ በዛ ፡ ግፉ ፡ በዛ ፤ በመርከብ ፡ ተጭኖ ፡ ሐበሻ ፡ ሊገዛ ።

ተጫነ ፤ በሸክምነት ፡ በላይ ፡ በተሸካሚነት ፡ በታች ፡ ኾነ ፤ ተከመረ ፡ ጨቈነ ፡ ከበደ ። እከሌን ፡ እርጅና ፡ እንቅልፍ ፡ ተጭኖታል ፡ እንዲሉ ። (ተረት) ሰው ፡ ይውደድኽ ፤ ድንጋይ ፡ ይጫንኽ ።

ተጫነ ፤ ባጋሰሰ ፡ ዠርባ ፡ መጣ ፡ ኼደ ፡ እኽሉ ፡ ዕቃው ። (ተረት) ፤ ነገር ፡ ቢበዛ ፡ ባህያ ፡ አይጫንም ።

ተጫኝ ፤ የተጫነ ፡ የሚጫን ፤ ጎይለኛ ።

ተጫን ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ጠላትን ፡ ጨቊን ፡ ከበድ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ተጫኔ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ።

መጫን ፤ መሸከም ፤ ወደ ፡ ታች ፡ ማለት ፡ መጨቈን ፡ መከበድ ።

(ጥሣ) መጫኛ ፤ መጨቈኛ ፡ መጨፈቂያ ፡ ባለ ባላ ፡ በትር ፡ ደንጊያ ፤ መግጠሚያ ፡ ያለው ፡ የማ ተሚያ ፡ ቤት ፡ ባለመዘውር ፡ ብረት ፡ ድኾስን ፡ ለጥ ፡ ቀጥ ፡ የሚያደርግ ፡ መርገጫ ። ፈረንጆች ፡ ፕ ሬስ ፡ ይሉታል ።

ተጫጫነ ፤ ተሸካከመ ፤ ተካበደ ። ከረምቱ ፡ ተጫጭኗል ፤ እኽሌን ፡ እንቅልፍ ፡ ተጫጭኖታል ፡ እንዲሉ ።

መጫጫን ፤ መሸካከም ፤ መካበድ ፡ አለ መቅለል ።

አጫጫነ ፤ ጭነትን ፡ እክብት ፡ ዠርባ ፡ ላይ ፡ አዋጣ ፡ አስተሳሰረ ፤ የሚጫነውን ፡ ክብት ፡ አያያዘ ፡ (ያዘ) ።

አጫጫኝ ፤ ያጫጫነ ፡ የሚያጫጭን ፤ የ ጫኝ ፡ ረዳት ።

ማጫጫን ፤ ማስተሳሰር ።

ጭነት ፤ (ጽዕነት) ፤ የክብት ፡ ሸክም ፡ ሲ ራራ ፡ ቀርቃባ ፡ ወይም ፡ ሞላላ ፤ ሣር ፡ ዕንጨት ፡ ደንጊያ ፡ ዐፈር ፡ ውሃ ፡ እኽል ፡ ልብስ ፡ ዕቃ ፡ ማን ኛውም ፡ ለሰው ፡ ጥቅም ፡ የሚኾን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ።

ጫን ፤ (ተጽዕኖ) ፤ መጫን ።

ጫን ፡ አለ ፤ ዐየል ፡ ከበድ ፡ አለ ።

ጫን ፡ ያለው ፤ የወንድ ፡ መጠሪያ ፡ ስም ።

አጫጫን ፤ አስተሳሰር ፤ መጫን ።

ቄኖ ፤ የንጪት ፡ ስም ፤ እሾኹ ፡ ቀንጠፋ ፡ የሚመስል ፡ ዛፍ ።

ቈንብላ ፤ (ዕንብል) ፤ የራስ ፡ ማሰሪያ ፡ ወይም ፡ ጌጥ ።

(ጥል) ቄንቡል ፤ (ጸቢል) ፤ ጥፍት ፡ ዕልም ።

ቄንቡል፡ አለ ፤ (ኮነ ፡ ከመ፡ጸበል) ፤ ሼደ ፡ ነጐደ ፤ ካይን ፡ ተሰወረ ፤ በቶሎ ፡ ዐለፈ ።

ጨነበረ ፤ (ጨበረ) ፤ ሮጠ ፡ ፈጠነ ፤ ጠለቀ ፡ ዐረበ ።

ጨነበረ ፤ ሳተ ፤ ስሕተተኛ ፡ ኾነ ።

ቈንቡሬ ፤ ሯጭ ፡ ፈጣን ።

ቄንብር ፤ የሮጠ ፡ የፈጠነ ፡ የጠለቀ ።

ቄንብሬ ፤ የሚዳ ፡ ስም ፤ በታችኛው ፡ ወግዳ ፡ ያለ ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ መሮጫ ፡ መጋለቢያ ።

ቄንብር ፡ ቦቃ ፤ (ቄምር ፡ ቦቃ) ፤ በስተምዕራብ ፡ ብርሃን ፡ የተሣለባት ፡ የተጨመረባት ፡ በስተምሥራቅ ፡ ግን ፡ ጨለማ ፡ ያለባት ፡ ጨረቃ ። ጨረቃ ፡ ቄንብር ፡ ቦቃ ፡ ዐጤ ፡ ቤት ፡ ገባች ፡ ዐውቃ ፡ እንዲሉ ፡ ልጆች ። ቦቃ ፡ ጋልኛ ፡ ነው ፤ ንጣትን ፡ ነጭነትን ፡ ያሳያል ። ግንባረ ፡ ቦቃ ፡ እንዲሉ ።

ተጨናበረ ፤ ተሳሳተ ፡ ተደናገረ ።

መጨናበር ፤ መሳሳት ፡ መደናገር ።

ተጨነባበረ ፤ ተደነጋገረ ።

አጨናበረ ፤ አሳሳተ ፡ አደናገረ ፤ ኹለት ፡ ነገር ፡ አሳየ ።

አጨናባሪ ፤ ያጨናበረ ፡ የሚያጨናብር ፤ አሳሳች ፡ አደናጋሪ ።

ማጨናበር ፤ ማሳሳት ፡ ማደናገር ።

ማጨናበሪያ ፤ የሐሰት ፡ የተንኰል ፡ ነገር ፤ የሽንገላ ፡ ምላስ ።

አጨነባበረ ፤ አደነጋገረ ።

ማጨነባበር ፤ ማደነጋገር ።

ማጨነባበሪያ ፤ ማደነጋገሪያ ።

አጨነባበር ፤ አደነጋገር ፤ ማጨናበር ።

(ጨነበሰ) ፤ ጠነበዘ ። ትግ ፡ ጠንበሰ) ፤ ተጨናበሰ ፤ ታወከ ፤ አልድን ፡ ትክክል ፡ አላይ ፡ አልነድ ፡ አልበራ ፡ አለ ፤ ጨሰ ፤ ሲጠፋ ፡ ቀረበ ፤ ያይን ፡ የእሳት ፡ የመብራት ።

ጨነበሰ ፤ ጨንባሳ ፤ የተጨናበሰ ፡ የሚጨናበስ ፤ ጤና ፡ ቢስ ፡ ዐይን ።

መጨናበስ ፤ ቍልጭ ፡ አለማለት ፡ መጨስ ።

ተጨነባበሰ ፤ ተማማሰ ።

ቄንብስብስ ፤ የተጨነባበሰ ።

ቄንብስብስ ፡ አለ ፤ ተጨነባበሰ ።

አጨናበሰ ፤ አወከ ፤ አጨሰ ፤ እንዳያይ ፡ እንዳይነድ ፡ አደረገ ።

ማጨናበስ ፤ ማወክ ፡ ማጨስ ።

አጨነባበሰ ፤ አማማሰ ።

ማጨነባበስ ፤ ማማማስ ።

ማጨነባበሻ ፤ ማማማሻ ።

አጨነባበሰ ፤ አማማስ ፤ ማጨናበስ ።

ጨነገዘ ፤ ቈረጠ ፡ ቀደደ ።

ጨነጋገዘ ፤ ቈራረጠ ፡ ቀዳደደ ፡ (ፀነገ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ። ሕዝ፲፫ ፡ ፲፭) ።

ጨነጐለ ፤ (ጨገለ) ፤ አጐለ ፡ ሰነከለ ፤ በኾምር ፡ አስቀረ ። (ጠነወተ)ን ፡ ጨነፈን ፡ እይ ።

ተጨናጐለ ፤ ታጐለ ፡ ተሰናከለ ፤ ሳይዋጣ ፡ ባጓጐል ፡ ቀረ ።

መጨናጐል ፤ መሰናከል ።

መጨናጐያ ፤ መሰናኪያ ።

ተጨነጓጐለ ፤ ተጓጐለ ፡ ተሰነካከለ ።

መጨነጓጐል ፤ መተጓጐል ፡ መሰነካከል ።

መጨነጓጐያ ፤ መተጓጐያ ፡ መሰነካኪያ ።

አጨናጐለ ፤ አሰናከለ ።

አጨናጓይ ፤ ያጨናጐለ ፡ የሚያጨናጐል ፤ አሰናካይ ።

ማጨናጐል ፤ ማሰናከል ።

ማጨናጐያ ፤ ማሰናኪያ ።

አጨነጓጐለ ፤ አስተጓጐለ ፡ አሰነካከለ ።

ማጨነጓጐል ፤ ማስተጓጐል ፡ ማሰነካከል ።

ማጨነጓጐያ ፤ ማሰነካኪያ ።

አጨነጓጐል ፤ አሰነካከል ፤ ማጨናጐል ።

ጨነገፈ ፤ (ጸንገፈ ። ትግ ፡ ጨንገፈ) ፤ መለመለ ፡ ጣለ ፡ አረገፈ ፤ አወረደ ፡ አወጣ ፡ አጠናወተ ፡ (ገቢር) ።

ጨነገፈ ፤ ወረደ ፡ ወጣ ፡ ተጠናወተ ፡ ተጣለ ፡ (ተገብሮ) ።

ጨነገፈች ፤ አወረደች ፡ አወጣች ፡ ሽልን ፡ (ዘፀሮ፭ ፡ ፳፪) ።

ጨንጋፊ ፤ የጨነገፈ ፡ የሚጨነግፍ ፤ መልግይ ።

ቄንገፋ ፤ ምልመላ ፡ ውርጃ ፤ የማርገፍ ፡ የማጠናወት ፡ ሥራ ፡ (ፀነገ ፡ ፮ ፡ ፳፭) ።

መጨንገፍ ፤ ማርገፍ ፡ ማውረድ ፡ ማውጣት ፡ ማጠናወት ።

መጨንገፍ ፤ መርገፍ ፡ መውረድ ፡ መውጣት ፡ መጠናወት ።

መጨንገፊያ ፤ መመልመያ ፤ ማጭድ ፡ በትር ፡ ምች ፡ በሽታ ።

አስጨነገፈ ፤ አስመለመለ ፡ አስጣለ ።

አስጨነገፈ ፤ አስወረደ ፡ አስወጣ ፤ ባጓጕል ፡ አስቀረ ፡ (ፀነገ ፡ ፀ ፡ ፲፱) ።

አስጨንጋፊ ፤ ያስጨነገፈ ፡ የሚያስጨነግፍ ፡ የሚያስወርድ ፤ አጠናዋች ።

ማስጨንገፍ ፤ ማስመልመል ፡ ማስወረድ ፡ ማስወጣት ።

ተጨነገፈ ፤ ተመለመለ ፡ ረገፈ ።

ጭንግፍ ፤ (ጽንጉፍ) ፤ የተመለመለ ፤ ምልማይ ፡ ርጋፊ ።

ጨንጋፋ ፤ ጭንጋፊ ፤ የጨነገፈ ፤ የወረደ ፡ የወጣ ፤ ውርጃ ።

ጭንጋፍ ፡ (ፎች) ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ አለቀኑ ፡ የተወለደ ፡ አካለ ፡ ጕደሉ ፤ ሞኝ ፡ (ዘጕፀፀ ፡ ፲ፀ ። መክፀ ፡ ፫) ።

አጨናገፈ ፤ አሰናከለ ።

አጨነጋገፍ ፤ አጠነዋወት ፤ መጨንገፍ ።

ጨንገር ፤ ልምጭ ፡ አርጭሚ ፡ አሽንቋጠ ፡ (ፀሳሙ ፡ ፯ ፡ ፲ፀ ። ምሳ፲፫ ፡ ፭፬) ።

ጨንገሮች ፤ ልምጮች ፡ አርጭሚዎች ።

ጨንገር ፤ ክፍል ፡ ክፍል ፡ ያለው ፡ የሰንጠረዥ ፡ መሥመር ። ጨንገር ፡ ሰንጠረዥ ፡ እንዲሉ ።

ጨንገር ፤ ባለመሥመር ፡ የሐር ፡ ልብስ ፡ የሮንዜና ፡ የመጠብር ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ ሰንበር ፡ መሳይ ።

ጨንገር ፤ የዛር ፡ ስም ።

ጨንገር ፤ ሰርገኛ ፡ ጤፍ ፡ አገዳው ፡ እንደ ፡ መሥመር ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ የሚወጣ ።

ጨንገሬ ፤ የጨንገር ፡ ጨንገራዊ ፤ የኔ ፡ ጨንገር ።

ጭንጨ ፡ (ዎች) ፤ ከባዕድ ፡ ያልተደባለቀ ፡ ያልተዋለደ ፡ ያልተዳቀለ ፡ ያልተለወጠ ፡ ነገድ ፡ ወገን ፤ ሌላ ፡ ቋንቋ ፡ የማያውቅ ፡ የሰው ፡ ዘር ። ጭንጨ ፡ ዐማራ ፡ ጭንጩ ፡ ጋላ ፡ እንዲሉ ።

ጭንጫ ፡ (ፎች) ፤ ከ*ኮ*ሐ) ፤ ከደንጊያነት ፡ በቀር ፡ ዐፈር ፡ አሸዋ ፡ የሌለበት ፡ ስፍራ ፡ የማይታረስ ፡ የማይዘራ ፡ አለት ፡ ገጠር ፡ (ምሳ፭ ፡ ፲፯ ። ሰቈ፫ ፡ ፲፭) ። ሽከረን ፡ ተመልከት ።

ጭንጫ ፤ ባጤ ፡ ምኒልክ ፡ አዳራሽ ፡ ፌት ፡ ለፌት ፡ ያለ ፡ ወልወል ፡ አደባባይ ፡ ሸንጎ ።

ጭንጫማ ፤ ጭንጫም ፤ ጭንጫ ፡ ያለው ፡ ባለጭንጫ ፡ መሬት ።

ጭንጭራ ፤ (ት) ፤ መቋደሻ ፡ በውስጡ ፡ ጥቃቅን ፡ ጭንጫ ፡ የሚገኝበት ።

ጭንኰር ፤ የቍስል ፡ ስም ፤ ሽሐኝ ፡ (ዘፀፀ ፡ ፱ ፡ ፲ ። ፪ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፲፯) ። ጭንቍርን ፡ እይ ።

ጭንኰሮ ፤ ራሰ ፡ ብትን ፡ ዘንጋዳ ፤ እንጭ ብሌ ። ዘሩ ፡ ጠነከረ ፡ ነው ።

(ጨነፈረ) ፤ ጨፈረ ፡ ጠፈረ ። ቸነፈር) ፤ አጨናፈረ ፡ (አስተፃፈረ) ፤ ክፉኛ ፡ መታ ፤ አጮኸ ፡ አላመመ ፤ የምች ።

ማጨናፈር ፤ መምታት ፡ ማሳመም ።

ማጨናፈሪያ ፤ ጨረቃ ፡ ፀሓይ ፡ ላብ ፡ የወጥ ፡ ሽታ ።

ጨነቀ ፤ (ጸዐቀ) ፤ ጠበበ ፡ ቸገረ ፡ አወከ ፡ (ኢሳ፷፫ ፡ ፱) ። (ተረት) ፤ የጨነቀው ፡ እርጉዝ ፡ ያገባል ፤ የባሰበት ፡ እመጫት ። ጠነቀን ፡ ተመልከት ።

ጭንቅ ፤ (ጸዕቅ) ፤ የጠበበ ፡ ጥብ ፤ የቸገረ ፡ ችግር ። ጭንቅ ፡ አለመቃብር ፡ የለም ።

ጭንቅ ፡ አለው ፤ ጥብብ ፡ ችግር ፡ አለው ፤ የሚያደርገውን ፡ ዐጣ ።

መጭነቅ ፤ መጥበብ ፡ መቸገር ።

አስጨነቀ ፤ አስጠበበ ፡ አስቸገረ ፤ ጭንቅ ፡ አሳየ ፡ (ኢሳ፷፫ ፡ ፲ ። ኤር፲፱ ፡ ፱ ። ሕዝ፲፰ ፡ ፯ ። ዳን፭ ፡ ፭) ።

አስጨናቂ ፤ ያስጨነቀ ፡ የሚያስጨንቅ ፤ አስጠባቢ ፡ አስቸጋሪ ፡ (ኢሳ፲፱ ፡ ፩ ። ፳፱ ፡ ፳) ። ሲበዛ ፡ አስጨናቆች ፡ ይላል ፡ (ኢሳ፵፱ ፡ ፳፯) ።

አስጨናቂ ፤ የሰው ፡ ስም ።

ማስጨነቅ ፤ ማስጠበብ ፡ ማስቸገር ፡ (ምሳ ፳፪ ፡ ፲፯ ። ሕዝ፵፭ ፡ ፱) ።

ማስጨነቂያ ፤ ማስጠበቢያ ፡ ማስቸገሪያ ፡ ሥቃይ ፡ መከራ ።

ተጨነቀ ፤ (ተጽዕቀ) ፤ ተጠበበ ፡ ተቸገረ ፡ ታወከ ፤ ግራ ፡ ገባው ፡ (ዘፍ፮ ፡ ፯) ። (ግጥም) ፤ እግዜር ፡ ያውቃል ፤ ሰው ፡ በከንቱ ፡ ይጨነቃል ። ፲፪ ፡ ኾነን ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ወደን ፤ እሷ ፡ ትሥቃለች ፡ እኛ ፡ ተጨንቀን ።

ተጨናቂ ፡ (ቆች) ፤ የተጨነቀ ፡ የሚጨነቅ ፡ (መክ፬ ፡ ፩) ።

መጨነቅ ፤ መጠበብ ፡ መቸገር ፡ መውጣ ፡ ቀዳዳ ፡ ማጣት ፡ (ዘዳ፴፫ ፡ ፱፫ ፡ ፱፭ ። ኢሳ፷፭ ፡ ፲፯ ። ኤር፲፱ ፡ ፱ ። ሕዝ፬ ፡ ፲፯) ።

መጨነቂያ ፤ ምጥ ፡ ጣረ ፡ ሞት ።

ተጣነቀ ፤ (ተጸዐቀ) ፤ ተጣጋ ፡ ተጣበበ ፡ ተፋተገ ፡ ተጋፋ ።

ተጣናቂ ፤ (ተጸዓቂ) ፤ የሚጣነቅ ፤ ተጣባቢ ፡ ተጋሪ ።

መጣነቅ ፤ መጣበብ ።

ተጨናነቀ ፤ ተጠጋጋ ፡ ተቀራረበ ፡ ተነባበረ ፡ ተደራረበ ።

መጨናነቅ ፤ መጠጋጋት ፡ መቀራረብ ።

መጨናነቂያ ፤ ጠባብ ፡ ስፍራ ፡ ቤት ።

አጣነቀ ፤ (አስተጻዐቀ) ፤ አጣበበ ፡ አጋፋ ፡ መተናፈሻ ፡ አሳጣ ፡ (ዘዳኟ ፡ ፲፪ ። ኢሳ፲፩ ፡ ፲፫ ። ዮኤ፪ ፡ ፭ ። ማር፫ ፡ ፱) ።

አጣናቂ ፤ ያጣነቀ ፡ የሚያጣንቅ ፤ አጣባቢ ።

ማጣነቅ ፤ ማጣበብ ፡ ማጋፋት ።

አጠናነቀ ፤ አጠጋጋ ፡ አቀራረበ ፡ አደራረበ ።

ጭንቀት ፤ ጭንቅ ፡ ጥበት ፡ ችግር ፡ ጣር ፡ ጋር ፡ ሥቃይ ፡ መከራ ። ጭንቅ ፡ በጥሬነቱ ፡ ከጭንቀት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ መኾኑን ፡ አስተውል ፡ (ኢሳ ፴ ፡ ፮ ፡ ፷ ። ኤር፮ ፡ ፳፬) ።

ማንቃ ፤ በትከሻና ፡ በትከሻ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ገላ ፡ ደንደስ ፡ ማዥራት ፡ የዠርባ ፡ ማፍ ፡ (ኢሳ፵ ፡ ፮ ። ፴ ፡ ፮ ። ዘካ፯ ፡ ፲፩) ።

ማንቃ ፤ የትከሻ ፡ ስም ፤ ትከሻ ። ማንቃ ፡ ጠላ ፡ እንዲሉ ።

ማንቆች ፤ ማዥራቶች ፡ ትከሾች ፡ (ዘዘጽ፳፡ ፲፪) ።

አጠናነቅ ፤ አቸጋገር ፤ መጭነቅ ።

ጭንቀ-ላ ፤ ታናሽ ፡ ማሰሮ ፡ ዐይኑትን ፡ የምትበልጥ ፡ ያራስ ፡ ልጅ ፡ ጭንቅላት ፡ የምታኽል ። ልጆች ፡ ሲሞሉ ፡ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ ጭንቀ-ላ ፡ ያርገኝ ፡ እንዲሉ ።

ጭንቅላት ፤ (ጭንቅ ፡ አላት) ፤ የራስ ፡ ስም ፤ የተንቀሳቃሽ ፡ ኹሉ ፡ ራስ ። ቅልን ፡ እይ ።

ጭንቅላቶች ፤ ፪ና ፡ ከ፪ ፡ በላይ ፡ ያሉ ፡ ራስ ፡ ቅሎች ።

ጭንቅላታም ፤ ዘናና ፡ ገመሞ ፡ ራስ ።

ጭንቅሎ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ የቀ-ልምጫ ፡ ስም ፤ ራሳም ፡ ራሰ ፡ ትልቅ ።

ጠነቀረ ፤ ደፈጠ ።

አጠነቀረ ፤ አደፈጠ ።

አጠንቅራ ፤ በተነቀለ ፡ ማግስት ፡ የሚበቅል ፡ መጥፎ ፡ ዐረም ።

ጠነቈረ ፤ (ጠነቀረ) ፤ ዐይኑን ፡ ገደለ ፡ አደከመ ፤ አስተያየቱን ፡ ቈጠበ ፡ አሳነሰ ፤ ፩ ፡ ዐይኑን ፡ ጨፍኖ ፡ ባ፩ ፡ ዐይኑ ፡ አየ ።

ጠንቋራ ፤ የጠነቈረ ፤ አንድ ፡ ዐይኑን ፡ ያደከመ ።

አጠነቈረ ፤ አጠለገ ፡ አወለገ ።

ተጠነቈረ ፤ ደከመ ፡ አነሰ ፤ ሊከደን ፡ ሊገጠም ፡ ጥቂት ፡ ቀረው ፡ ሸፋሸፍቱ ።

ጭንቍር ፤ የተጠነቈረ ።

ጭንቍር ፤ ጭንኰር ፤ ሽሐኝ ፡ ዐይንን ፡ የሚጠነቍር ፡ አፍንማን ፡ የሚያበላሽ ፡ ቍስል ፤ ቍሞርን ፡ እይ ። በግእዝ ፡ ጥንቁር ፡ ይባላል ።

ተጠናቈረ ፤ ባንድ ፡ ዐይን ፡ ቱያየ ፤ በ፪ኛው ፡ አልተያየም ።

መጠናቈር ፤ መተያየት ፡ አለመተያየት ።

አጠናቈረ ፤ ጠንቋራ ፡ አኳኋን ፤ ዐይንን ፡ አጣፈነ ፤ ቅንድብን ፡ አጠጋጋ ።

ማጠናቈር ፤ ማጣፈን ።

ማጠናቈሪያ ፤ ይላማ ፡ አፈ ፡ ሙዝ ፡ ቀስት ።

አጠነቍቈር ፤ የግራ ፡ ዐይን ፡ አጠፋፈን ፤ የቀኝ ፡ ዐይን ፡ አስተያየት ።

ጠፋ ፤ ጠፈ፤ (ጋላ) ፤ የመስክ ፡ ስም ፤ መስክ ፤ ለምጠቅ ፡ ጠቆ ፡ (ማሕ፯ ፡ ፲፭) ።

ጠፈ ፤ ጠጉራም ፡ ጋቢ ፡ ቡልኮ ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ ሀብታም ፡ የሚለብሰው ። ጠፋዊ ፡ ማለትን ፡ ያሳያል ፤ ጠጉሩ ፡ የሚታጠድ ፡ ይመስላልና ።

ጩፋ ፤ (ጋላ) ፤ የብርና ፡ የወርቅ ፡ አንባር ፤ ንጉሥ ፡ ኹለት ፡ ጠላት ፡ ለገደለ ፡ የሚሸልመው ። ማልደያን ፡ ተመልከት ።

ጩፋ ፤ ግጥም ፡ ያለ ፡ የሽሩባ ፡ ሥራ ። ጩፋ ፡ በጋልኛ ፡ ኹሉ ፡ ዝጉ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ጫፍ ፤—መጠረሻ ፤—ጠፈጠፈ ።

ጠፈገ ፤ ጠፈቀ ፡ ቸፈገ ።

ተጠፈገ ፤ ተጠፈቀ ፡ ተቸፈገ ።

ጭፍግ ፤ ጭፍቅ ፡ ችፍግ ።

ጭፍግ ፡ አለ ፤ ችፍግ ፡ አለ ።

ጠፈገገ ፤ ግንባሩን ፡ ቋጠረ ፡ አጠቈረ ፤ ሳይጠዳው ፡ ቀረ ። ጠገገን ፡ እይ ።

መጠፍገግ ፤ ፊትን ፡ መቋጠር ።

ተጠፈገገ ፤ ተቋጠረ ፡ ጠቈረ ።

ጠፈገግ ፤ ጠፍጋጋ ፤ የተጠፈገገ ፡ ፊተ ፡ ቋጣራ ።

ጠፈጠፈ ፤ (ጠፈጠፈ) ፤ መታ ፡ ቈረጠ ፡ ቈራረጠ ፡ ተፈተፈ ፡ ጫፍን ፡ አውራን ፡ ክብትን ፡ ሳይወድቅ ፡ በቁሙ ።

ጠፈጠፈ ፤ ነባርን ፡ ዐለፈ ፡ ሻረ ፡ ዳኛው ።

ጠፈጠፈ ፤ ሰደበ ፡ ፀረፈ ፡ ወረፈ ።

ጠፍጣፊ ፤ የጠፈጠፈ ፡ የሚጠፈጥፍ ፤ ቈራጭ ፡ ተፍታፊ ።

ጭፍጠፋ ፤ ቈረጣ ፡ ትፍተፋ ።

ጠፈጠፍ ፤ (ጠፈጠፍ) ፤ የከረምት ፡ ጭቃና ፡ ውሃ ፡ የሰውን ፡ እግር ፡ የሚቈርጥ ፡ የሚያቈስል ።

ጫፍ ፤ ራስ ፡ መጠረሻ ፡ ውልብልቢት ፡ ቀንበጥ ፡ ዐናት ፡ (ዘፍጽ ፡ ፲፭ ። ኢሳ፶፱ ፡ ፲፱) ። የተራራ ፡ የዛፍ ፡ የነገር ፡ ጫፍ ፡ እንዲሉ ። ቅርንጫፍን ፡ ተመልከት ።

ማፎች ፤ ራሶች ፣ ዐናቶች ፣ (ዘፀጽፅ ፣ ፴፭ ። ሕዝ፴፪ ፣ ፭ ፣ ፮ ። ሮሜ፲፩ ፣ ፲፮ ፣ ፲፯ ፣ ፲፰ ፣ ፳፭) ።

ማራ ፣ ደረቅ ፤ ለዛ ፣ ሙጥጨ ።

ማፍና ፣ ማፍን ፣ ገጠመ ፤ ልብስን ፣ ከርን ፣ ገመድን ፣ ጠፍርን ፣ ሽቦን ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ዐጠፈ ።

መጠፍጠፍ ፤ መቈራረጥ ፣ መተፍተፍ ።

መጠፍጠፊያ ፣ ጐራዴ ፣ ማንኛውም ፣ ስለት ።

አስጠፈጠፈ ፤ አስመታ ፣ አስቈረጠ ።

አስጠፍማፊ ፤ ያስጠፈጠፈ ፣ የሚያስጠፈጭፍ ፤ አስቈራጭ ።

ማስጠፍጠፍ ፤ ማስመታት፣ ማስቈረጥ ።

ማስጠፍጠፊያ ፤ ጊዜና ፣ መሣሪያ ።

ተጠፈጠፈ ፤ ተቈራረጠ ፣ ተተፈተፈ ።

ተጠፈጠፈ ፤ ታለፈ ፣ ተሻረ ፣ ነገሩ ።

ተጠፍማፊ ፤ የሚጠፈጠፍ ፣ ቅጠል ።

ጭፍጭፍ ፤ የተጠፈጠፈ ፤ የማፍ ፣ ቅን ጥብጣቢ ፣ ቍርጥራጭ ።

ጭፍማፊ ፤ የነገር ፣ ትርፍራፊ ።

ተጠፋጠፈ ፤ በሰይፍ ፣ ተማታ ፣ ተቈራረጠ ።

አጠፋጠፈ ፤ አማታ ፣ አቈራረጠ ።

አንጠፈጠፈ ፤ (አንጠፈጠፈ) ፤ በአለት ፣ ላይ ፣ መናኛ ፣ ዕጥበት ፣ ዐጠበ ።

አንጠፈጠፈ ፤ አወዛ ፣ አቅለጠለጠ ።

አንጠፈጠፈ ፤ ወቀሠ ፣ ዘለፈ ።

አንጠፍማፊ ፤ ያንጠፈጠፈ ፣ የሚያንጠፈጭፍ ፤ ዐጣቢ ።

እንጭፍማፊ ፤ ዕጣቢ ፣ እድፍ ።

ማንጠፍጠፍ ፤ ማጠብ ፣ ማቅለጥለጥ ፣ ማውዛት ።

ማንጠፍጠፊያ ፤ ማጠቢያ ፣ ውሃ ፣ እንዶድ ፣ እጅ ፣ ቈርበት ፣ የለስ ፣ ጣቢያ ።

ተንጠፈጠፈ ፤ በማጠቢያ ፣ ላይ ፣ ተመታ ፣ ታጠበ ።

ተንጠፈጠፈ ፤ እዠ ፣ ወዛ ፤ የፈት ።

ጭፍጭፍ ፤ ማዠት ። ጀቱም ፣ ፍ ፣ ይጠብ ቃል ።

ጭፍጭፍ ፣ አደረገ ፤ አንጠፈጠፈ ።

ጭፍጭፍ ፣ አለ ፤ ችፍ ፣ ችፍ ፣ አለ ፤ ተቅለጠለጠ ፤ የወዝ ፣ የማውጌ ፣ እንጀራ ።

መንጠፍጠፍ ፤ መታጠብ ፣ መውዛት ።

አጠፋጠፍ ፤ አቈራረጥ ፤ መጠፍጠፍ ።

ጠፈለቀ ፤ (ጠፈቀ) ፤ ረገጠ ፣ ዳጠ ፣ ደፈጠጠ ፣ አጠማለቀ ።

ጠፈለቀ ፤ ዕዳሪ ፣ አወጣ ፣ ዐረሰ ፣ ተረ ተረ ፣ ሠነጠቀ ። ጠጋን ፣ እይ ።

ጠፈለቀ ፤ ዐዲስ ፣ ብረት ፣ ሠራ ፣ ቀጠ ቀጠ ። ጠፈለቀ ፣ ከጠፈቀና ፣ ከፈለቀ ፣ የተዴቀለ ፣ ነው ።

ጠፍላቂ ፣ (ቆች) ፤ የጠፈለቀ ፣ የሚጠፈልቅ ፤ ዳጭ ፣ ዐራሽ ፣ ቀጥቃጭ ።

መጠፍለቅ ፤ መዳጥ ፣ ማጠማለቅ ፣ ማረስ ፣ መቀጥቀጥ ፣ (ዓሞኜ ፣ ፲፩) ።

መጠፍለቂያ ፤ መደፍጠጫ ፣ ዕዳሪ ፣ ማውጫ ፣ መቀጥቀጫ ፣ ጊዜ ፣ እግር ፣ ደንጊያ ፣ ማረሻ ፣ መስፍ ፣ መዶሻ ።

ጠፈላለቀ ፤ አበለሻሸ ፣ እንዳለወገን ፣ አደረገ ፣ (ፀዜና ፣ ፴፬ ፣ ፺) ።

አስጠፈለቀ ፤ አስረገጠ ፣ አስዳጠ ፣ አስደፈጠጠ ።

አስጠፈለቀ ፤ ጠፍልቁ ፣ አለ ፤ አሳረሰ ፣ አስተረተረ ።

አስጠፈለቀ ፤ አሠራ ፣ አስቀጠቀጠ ።

አስጠፍላቂ ፤ ያስጠፈለቀ ፣ የሚያስጠፈልቅ ።

ማስጠፍለቅ ፤ ማስዳጥ ፣ ማሳረስ ፣ ማስቀጥቀጥ ።

ማስጠፍለቂያ ፤ ማሳረሻ ፣ ማስቀጥቀጫ ።

ተጠፈለቀ ፤ ተረገጠ ፣ ተዳጠ ፣ ተደፈጠጠ ።

ተጠፈለቀ ፤ ታረሰ ፣ ተተረተረ ፣ ተሠነጠቀ ፣ ዕዳሪው ።

ተጠፈለቀ ፤ ተሠራ ፣ ተቀጠቀጠ ፣ ጠገራው ።

ተጠፍላቂ ፤ የሚጠፈለቅ ፣ ዕዳሪ ፣ ብረት ።

ጠፍላቃ ፤ የተዳጠ ፣ የተደፈጠጠ ።

ጭፍልቅ ፣ (ቆች) ፤ የተጠፈለቀ ፣ የተሠራ ፣ የታረሰ ።

ጭፍልቅ ፤ ዐዲስ ፣ ዕርሻ ፣ ዐዲስ ፣ የብረት ፣ ዕቃ ።

ጭፍልቅ ፣ አደረገ ፤ ጠፈለቀ ።

ጭፍልቅ ፣ አለ ፤ ተጠፈለቀ ።

ተጠፋለቀ ፤ ተጠማለቀ ፤ ተቀጣቀጠ ።

ተጠፈላለቀ ፤ ተዳዳጠ ፣ ተደፋጠጠ ፣ ተጠመላለቀ ።

አጠፋለቀ ፤ አስተራረሰ ፣ ዕዳሪ ፣ አዋጣ ።

አጠፋለቀ ፤ ብረት ፣ አሣራ ፣ አባጅ ፣ አቀጣቀጠ ።

አጠፈላለቀ ፤ አዳዳጠ ፣ አደፋጠጠ ፣ አጠመላለቀ ።

አጠፈላለቅ ፤ አቀጣቀጥ ፤ መጠፍለቅ ።

ጠፈነ ፤ (ጸፈነ) ፤ ዐይኑን ፡ ከደነ ፤ ዐፈነ ፡ ደፈነ ፡ ወለሰ ፡ ሸፈነ ፡ ደመና ፡ ምድርን ።

ጠፋኝ ፡ (ሞች) ፤ የጠፈነ ፡ የሚጠፍን ፤ ሸፋኝ ።

ጥፈና ፤ ከደና ፡ ዐፈና ፡ ደፈና ፡ ሸፈና ።

መጠፈን ፤ መከደን ፡ መድፈን ፡ መሸፈን።

መጠፈኛ ፤ መከደኛ ፡ ሸፋኸፍት ።

ጠፋፈነ ፤ ከዳደነ ፡ ሸፋፈነ ።

መጠፋፈን ፤ መከዳደን ፡ መሸፋፈን ።

አስጠፈነ ፤ አስከደነ ፡ አሸፈነ ።

ማስጠፈን ፤ ማስከደን ፡ ማሸፈን ።

ተጠፈነ ፤ ተከደነ ፡ ተደፈነ ፡ ተሸፈነ ፡ (ኢ ሳኧ፱ ፡ ፱ ። ፴፪ ፡ ፫) ። ድመት ፡ ውሻ ፡ ዐይጥ ፡ አን በሳ ፡ ነብር ፡ ዥብ ፡ ተኩላ ፡ ቀበሮ ፡ ዋልጋ ፡ እነ ዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ኹሉ ፡ ዐይናቸው ፡ ተጠፍኖ ፡ ይወለዳሉ ፤ ምክንያቱም ፡ የጠለማ ፡ ጥፍሮች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ነው ።

ተጠፋኝ ፤ የሚጠፈን ።

ጠፋና ፤ ጥፍን ፤ የተጠፈነ ፡ ዐይን ፤ ወይም ፡ አሞራ ፡ ሰው ፡ (፪ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፱) ። ዐይንም ፡ የለኝ ፤ ጠፋና ፡ ነኝ ፡ እንዲሉ ፡ ልጆች ።

ጥፍን ፡ አደረገ ፤ ከድን ፡ ሸፍን ፡ አደረገ ።

ጥፍን ፡ አለ ፤ ድፍን ፡ አለ ፤ ተጠፈነ ።

ጥፍና ፤ ዐይን ፡ ጠፋና ።

ጥፍና ፤ የቀን ፡ ጠለማ ፡ የጉም ፡ ዐፈና ፡ ወሲስ ።

(ጥጠ) መጠፈን ፤ መከደን ፡ መሸፈን ።

ተጣፈነ ፤ ተካደነ ፡ ተሻፈነ ።

ተጠፋፈነ ፤ ዐይንን ፡ ተከዳደነ ፡ ተሸፋፈነ ።

አጣፈነ ፤ አካደነ ፡ አሻፈነ ።

አጠፋፈነ ፤ አከዳደነ ፡ አሸፋፈነ ።

አጥፈነፈነ ፤ አጥበሰበሰ ።

ማጥፈንፈን ፤ ማጥበሰበሰ ።

ተጥፈነፈነ ፤ ተጥበሰበሰ ።

ጥፍንፍን ፤ የተጥፈነፈነ ፤ ከድን ፡ ግልጥ ፡ ባይ ።

መጥፈንፈን ፤ መጥበሰበሰ ፤ ጥፍንፍን ፡ መኾን ።

አጠፋፈን ፤ አከዳደን ፤ መጠፈን ።

ጠፈንታ ፤ የቀድሞ ፡ ወታደር ፡ ስም ፤ ቡር ሳን ፡ ቤት ፡ አንሣን ፡ የመሰለ ፡ ጥፍራ ። (ጸፈናዊ ፡ ሰዓለ ፡ ጸፈን) ፡ ግለት ፡ ይመስላል ።

ጠፈቀ ፤ (ጸፈቀ) ፤ ደንጊያ ፡ ጫነ ፡ ረገጠ ፡ ለሰቀ ፡ ለጥ ፡ ቀጥ ፡ አደረገ ፡ ርጥብ ፡ ጠፈቃን ።

ጠፈቀ ፤ አጠጋጋ ፡ ጠቀጠቀ ፤ አበዛ ፡ ቸፈገ ፡ ጠፈገ ።

ጠፈቀ ፤ አከበበ ፡ አድበለበለ ። ጠበጠን ፡ እይ ።

ጠፋቂ ፡ (ቆች) ፤ የጠፈቀ ፡ የሚጠፍቅ ፤ ለሳቂ ።

ጥፈቃ ፤ ጥቅጠቃ ፡ ልሰቃ ።

ጠፈቃ ፡ (ቆች) ፤ ተጠፍቆ ፡ የደረቀ ፡ ባለጥራር ፡ ዕንጨት ፡ ያጥር ፡ የሚያዳ ፡ መሥሪያ ።

ጠፈቃ ፤ ቅንድብ ፡ ጥፋር ።

ጠፈቃ ፤ (ትግ) ፤ ጥቃ ።

መጠፈቅ ፤ መለሰቅ ፡ መለጠቅ ፡ መጠቅጠቅ ፡ ማድበልበል ።

መጠፈቂያ ፤ መለሰቂያ ፡ ሚዳ ፡ ደንጊያ ።

አስጠፈቀ ፤ ድንጋይ ፡ አስማነ ፤ አስለሰቀ ።

አስጠፈቀ ፤ አስጠቀጠቀ ።

አስጠፋቂ ፤ ያስጠፈቀ ፡ የሚያስጠፍቅ ፤ አስለሳቂ ።

ማስጠፈቅ ፤ ማስለሰቅ ፡ ማስጠቅጠቅ ።

ማስጠፈቂያ ፤ ጊዜና ፡ ስፍራ ።

ተጠፈቀ ፤ ደንጊያ ፡ ተማነበት ፤ ተለሰቀ ፡ ቀጥ ፡ አለ ።

ተጠፈቀ ፤ ተጠጋጋ ፡ ተጠቀጠቀ ፡ ተቸፈገ ፡ በዛ ።

ተጠፈቀ ፤ እንክብል ፡ ኾነ ፡ ተድበለበለ ።

ተጠፋቂ ፤ የሚጠፈቅ ።

(ጥፍ) ጥፍቅ ፤ (ጽፉቅ) ፤ የተጠፈቀ ፤ በከባድ ፡ ነገር ፡ የተረገጠ ፤ ልስቅ ፡ ችፍግ ፤ የተጠቀጠቀ ፡ (ኢዮ፴፰ ፡ ፵) ። ጥፍቅ ፡ ያለ ፡ ዳር ፡ እንዲሉ ።

(ላፍ) ጥፍቅ ፤ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ጽያ ፡ ዐርብ ፤ በ ርሱ ፡ የተሠራ ፡ ልብስ ። ጥፍቅ ፡ ኩታ ፡ ጥፍቅ ፡ ቀሚስ ፡ እንዲሉ ። ጥርሱ ፡ ቀጪንና ፡ የተቀራረበ ፡ ከኾነ ፡ ፀያውም ፡ ጥፍቅ ፡ ይባላል ። የአከሌ ፡ ዐርብ ፡ ጥፍቅ ፡ ነው ፡ እንዲሉ ።

ጥፍቅ ፤ በፂ ፡ በቅል ፡ የተሠራ ፡ ፲፪ ፡ ክንድ ፡ መቀነት ፤ በጣም ፡ ተመቶ ፡ የተጠቀጠቀ ፡ ሱሪ ፡ የሚኾን ፡ ልብስ ።

ጥፍቆ ፤ ባለቅመም ፡ ዳቦ ፡ ቄሎ ፡ እንደ ፡ ጥብጦ ፡ የተድበለበለ ፤ ኳስ ፡ መሳይ ፡ የኑግ ፡ ልጥ ልጥ ። ሽሚትን ፡ ተመልከት ።

ተጣፈቀ ፤ ተጣጋ ፡ ተጣቄነ ።

ተጠፋፈቀ ፤ ተጠጋጋ ፡ ተጠቋቄነ ።

አጣፈቀ ፤ በጠፈቃ ፡ ላይ ፡ ደንጊያ ፡ አጣጣነ ፤ አላሰቀ ።

አጠፋፈቀ ፤ አለሳሰቅ ፡ መጠፈቅ ።

ጠፈረ ፤ (ፀፈረ) ፤ ዘለለ ፡ አረገደ ፡ መር ፡ መር ፡ አለ ፤ ባንጎት ፡ ወረደ ። ደንከረን ፡ እይ ።

ጠፈረ ፤ ቀረበ ፡ ተጠጋ ።

ጠፋሪ ፡ (ዎች) ፤ የጠፈረ ፡ የሚጠፍር ፤ ዘላይ ፡ አርጋጅ ።

ጭፈራ ፤ ጭፋሮ ፤ ዝላይ ፡ ረገዳ ። ጮቤን ፡ አስተውል ።

ጭፍራ ፡ (ሮች) ፤ ወታደር ፡ የቊጥር ፡ ጦር ፡ እየጠፈረ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ የሚቀርብ ፡ ሰራዊት ፡ (ኢሳሳጅ ፡ ፲፪ ። ሉቃ፫ ፡ ፲፬) ።

ጭፋር ፡ (ሮች) ፤ የቅንድብ ፡ ጠጮር ፡ በሸፋሸፍት ፡ ጣፍና ፡ ጣፍ ፡ ተቀራርቦና ፡ ተደራርቦ ፡ የሚታይ ።

ጭፋር ፤ የዘንባባና ፡ የተምር ፡ ቅጠል ፡ ሰሌን ።

መጠፈር ፤ መዝለል ፡ ማርገድ ፡ መቅረብ ።

መጠፈሪያ ፤ መዝለያ ፡ ማርገጃ ፡ እግር ፡ ምድር ።

ጠፋፈረ ፤ ዘላለለ ።

መጠፋፈር ፤ መዘላለል ።

አስጠፈረ ፤ አዘለለ ፡ አስረገደ ፡ አስረገጠ ።

አስጠፋሪ ፤ ያስጠፈረ ፡ የሚያስጠፍር ፤ አዘላይ ፡ አስረጋጅ ፡ አስረጋጭ ።

ማስጠፈር ፤ ማዘለል ፡ ማስረገድ ።

ማስጠፈሪያ ፤ ማዘለያ ፡ ማስረገጃ ፡ ጊዜና ፡ ስፍራ ።

ተጠፈረ ፤ ተዘለለ ፡ ተረገደ ።

ተጣፈረ ፤ ተዛለለ ፤ ተቃረበ ፤ ተያያዘ ፡ ተቀናጀ ።

ተጣፋሪ ፤ የሚጣፈር ፤ ተያያዥ ፡ ንግግር ።

መጣፈር ፤ መዛለል ፡ መቃረብ ፡ መያያዝ ።

መጣፈሪያ ፤ መዛለያ ፡ መያያዣ ።

አጣፈረ ፤ አዛለለ ፤ አቃረበ ፤ አያያዘ ፡ አቀናጀ ።

አጣፋሪ ፡ (ዎች) ፤ ያጣፈረ ፡ የሚያጣፍር ፤ ፊት ፡ ለፊት ፡ በአንጻር ፡ ያለ ፡ የጭፈራ ፡ ጓድ ።

አጣፋሪ ፤ አያያዥ ፡ አቀናጂ ፤ ቃልን ፡ ከቃል ፡ (ነገርን ፡ ከነገር) ፡ የሚያያይዝ ፡ ራብዕ ፡ ፊደል ፡ እና ፤ ሲነገርም ፡ እ ፡ ተጕርዶ ፡ ይቀራል ። እከሌና ፡ እከሌ ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ እንዲሉ ። እናን ፡ በስፍራው ፡ ተመልከት ።

ማጣፈር ፤ ማዛለል ፡ ማያያዝ ።

ማጣፈሪያ ፤ ማያያዣ ፡ ማቀናጃ ።

አጠፋፈር ፤ አዘላለል ፤ መጠፈር ።

(ጠፈረረ) ፤ ጠረፈፈ) ፤ አንጠፈረረ ፤ አንጠረፈፈ ። ጠበረረን ፡ እይ ።

እንጭፍር ፤ እንጭርፍ ፡ ጠጮር ።

እንጭፍሬ ፤ የእንጭፍር ፡ ዐይነት ፤ እንጭብሌ ።

ማንጠፍረር ፤ ማንጠርፈፍ ።

ተንጠፈረረ ፤ ተንጠረፈፈ ።

ጠፈረር ፤ ጠፍራራ ፤ የተንጠፈረረ ፤ ጠረፈፍ ፡ ጠርፋፋ ።

ጭፍርር ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ።

ጭፍርር ፡ አለ ፤ ተንጠፈረረ ።

መንጠፍረር ፤ መንጠርፈፍ ።

ጠቆ ፤ (ጸቀወ) ፤ ጭቃ ፡ ለምጠቅ ። ጠቀየን ፡ ተመልከት ።

ጩቅ ፤—ንፉግ ፤—ጮቀ ።

ጣቅ ፤—ሙጫ ፤—ጠቀየ ።

ጭቃ ፤—በቁሙ ፤—ጠቀየ ።

ጮቀ ፤ (ጠፀ ፡ ፀወገ) ፤ ነፈገ ፡ ሠሠተ ፡ ቤሰ ።

ጩቅ ፡ (ቆች) ፤ ጠዋሚ) ፤ ንፉግ ፡ ሥሥታም ፡ ቢስ ፡ እጁን ፡ ቢሉት ፡ ጠብ ፡ የማይለው ።

ጮቄ ፤—ደጋ ፤—ጠቀየ ።

ጮቅ ፤—የእግር ፡ ጣት ፡ ቊስለ ፤—ጠቀየ ።

ጠቀጠቀ ፤ ጠቀጠቀ ፡ ደፈነ ።

ጠቀጠቀ ፤ ነዘነዘ ፡ አተከረ ፡ ነተረከ ።

ጠቀጠቀ ፤ ጠቆ ፡ አደረገ ፤ አጠቀየ ።

ጠቀጠቀ ፤ ርጥብ ፡ ጌሾ ፡ ወቀጠ ።

ጠቅጣቂ ፡ (ዎች) ፤ የጠቀጠቀ ፡ የሚጠቀጥቅ ፤ ደፋኝ ፡ ነዝናዥ ።

ጠቅጣቃ ፡ (ቆች) ፤ ነዝናዛ ፡ ነትራካ ።

ጭቅጠቃ ፤ ደፈና ፤ ንዝነዛ ፡ ንትረካ ።

ጠቀጠቀ ፤ ጭቃማ ፡ ስፍራ ፤ የውሃና ፡ የጭቃ ፡ አንድነት ፡ ድብልቅነት ፤ ጠቆ ፡ ለምጠቅ ።

መጠቅጠቅ ፤ መጠቅጠቅ ፡ መድፈን ፡ መነዝነዝ ፡ መውቀጥ ።

መጠቅጠቂያ ፤ መጠቅጠቂያ ፡ መነዝነዣ ፡ መውቀጫ ፡ ዘነዘና ።

መጠቅጠቂት ፤ በውሃ ፡ እየተነከረ ፡ በምጣድና ፡ ባክንባሎ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ቀዳዳ ፡ መድፈኛ ፡ የጠርቅ ፡ ትልታይ ፡ እንጀራ ፡ ነፋስ ፡ እንዳይነፍስበት ፡ መክልከያ ። ነገር ፡ መጠቅጠቂት ፡ የሚነገረው ፡ ለእንስት ፡ ነው ።

አስጠቀጠቀ ፤ አስጠቀጠቀ ፡ አስደፈነ ።

አስጠቀጠቀ ፤ አስነዘነዘ ፡ አስነተረከ ።

አስጠቀጠቀ ፤ አስወቀጠ ።

አስጠቅጣቂ ፤ ያስጠቀጠቀ ፡ የሚያስጠቀጥቅ ፤ አስደፋኝ ፡ አስነዝናዥ ፡ አስወቃጭ ።

ማስጨቅጨቅ ፤ ማስደፈን ፡ ማስነዝነዝ ፡ ማስወቀጥ ።

ተጨቀጨቀ ፤ ተጠቀጠቀ ፡ ተደፈነ ።

ተጨቀጨቀ ፤ ተነዘነዘ ፡ ተነተረከ ።

ተጨቀጨቀ ፤ ተወቀጠ ።

ጭቅጭቅ ፤ የተጨቀጨቀ ፡ በመጨቅጨቂት ፡ የተደፈነ ፡ እንጀራ ።

ጭቅጭቅ ፤ የተወቀጠ ፡ የጌሾ ፡ ቅጠል ።

ጭቅጭቅ ፡ አለ ፤ ፍንጥቅ ፡ ፍንጥቅ ፡ አለ ፡ ውሃው ፡ ጭቃው ፤ ተነዛ ፡ ተበተነ ። ፪ቱንም ፡ ቅ ፡ አጥብቅ ።

ተጨቃጨቀ ፤ ተነዛነዘ ፡ ተነታረከ ።

ተጨቃጫቂ ፡ (ቆች) ፤ የተጨቃጨቀ ፡ የሚጨቃጨቅ ፤ ተነዛናዥ ።

ተጨቃጫቂነት ፤ ተጨቃጫቂ ፡ መኾን ።

ጭቅጭቅ ፡ (ቆች) ፤ ንዝንዝ ፡ ንትርክ ፡ ውዝግብ ። ፪ኛውን ፡ ጭ ፡ አጥብቅ ።

ጭቅጭቃም ፤ ባለጭቅጭቅ ፤ ንዝንዛም ።

ጭቅጭቀኛ ፡ (ኞች) ፤ ጨቅጫቃ ፡ ጭቅ ጭቅ ፡ ወዳድ ፡ ነገር ፡ ቢያልቅበት ፡ የማይፈቅድ ።

መጨቃጨቅ ፤ መነዛነዝ ፡ መነታረክ ።

መጨቃጨቂያ ፤ መነዛነዣ ፡ ጊዜ ፡ ስፍራ ፡ ርስት ፡ ገንዘብ ።

አጨቃጨቀ ፤ አጠቃጠቀ ፡ አዳፈነ ።

አጨቃጨቀ ፤ አነዛነዘ ፡ አነታረከ ።

አጨቃጨቀ ፤ አዋቀጠ ።

አጨቃጫቂ ፤ ያጨቃጨቀ ፡ የሚያጨቃጭቅ ፤ አነዛናዥ ፡ የጭቅጭቅ ፡ ዳኛ ።

ማጨቃጨቅ ፤ ማጠቃጠቅ ፡ ማነዛነዝ ፤ ማዋቀጥ ።

ማጨቃጨቂያ ፤ ማነዛነዣ ፡ ማነታረኪያ ።

አጨቃጨቅ ፤ አደፋፈን ፡ አነዛነዝ ፤ መጨቅጨቅ ።

ጨቀየ ፤ (ሰቀየ ፡ ጸቀመ) ፤ ረካ ፡ ራሰ ፡ ጭቃ ፡ ኾነ ።

ጫቅ ፤ እንደ ፡ ጭቃ ፡ እየኾነ ፡ ከንጫት ፡ የሚወጣ ፤ የሙጫ ፡ ዐይነት ።

ጭቃ ፤ የራሰ ፡ የረሰረሰ ፡ ዐፈር ፤ የመሬት ፡ ሊጥ ፡ ያልበካና ፡ የበካ ። (ተረት) ፤ ማር ፡ ሲበዛ ፡ ጭቃ ፡ ነው ። አፍን ፡ ወንበርን ፡ ተመልከት ።

ጭቃ ፤ ወልቅ ፡ አረንቋ ፡ ማጥ ፡ ረግረግ ።

ጭቃ ፤ የሰው ፡ አካል ፡ ሥጋ ። አከሌ ፡ ከ ወደ ፡ ጭቃው ፡ በዛ ፡ ብሷል ፡ (ዘፍ፪ ፡ ፯) ።

ጭቃ ፤ ገባር ፡ በጭቃው ፡ በመሬቱ ፡ በር ሻው ፡ የሚገብር ። ፩ ፡ ጭቃ ፡ ፪ ፡ ጭቃ ፡ እንዲሉ ።

ጭቃ ፤ ዝናም ፡ ከጣለ ፡ የታረሰ ፡ የርሻ ፡ ይዘታ ። ጭቃዬን ፡ አለቅም ፡ እንዲል ፡ ባላገር ።

ጭቃማ ፤ ጭቃም ፤ ባለጭቃ ፡ ስፍራ ፡ ጭቃ ፡ ያለበት ፡ የበዛበት ።

ጭቃማ ፤ ሥጋማ ፡ አካለ ፡ ወፍራም ፡ ሰው ።

ጭቃ ፡ ኾነ ፤ ላቈጠ ።

ጭቃ ፡ ረጋጭ ፤ ጭቃን ፡ የሚረግጥ ፡ የሚ ያበካ ።

ጭቃ ፡ ሹም ፡ (ሞች) ፤ የጭቃ ፡ ሹም ፡ ባለምድርን ፡ የሚያዝ ። ሾመን ፡ እይ ።

ጭቃ ፡ ሱሪ ፤ በከረምት ፡ የሚጠለቅ ፡ የ ጭቃ ፡ ሱሪ ።

ጮቅ ፤ የከረምት ፡ ጭቃ ፡ ጨቀጨቅ ።

ጮቅ ፤ የእግር ፡ ጣት ፡ ውስጥ ፡ ቍስል ፤ በጭቃ ፡ ምክንያት ፡ መካከል ፡ መካከሉ ፡ ይቈስ ላል ፤ (ይከረከራል) ።

ጮቂ ፤ የጮቅ ፡ ባለጮቅ ፡ ደጋን ጮቅማ ፡ ስፍራ ። ጋላም ፡ ቄን ፡ አጥብቆ ፡ ጭቃን ፡ ጮቂ ፡ ይላል ። ጨቆን ፡ ተመልከት ።

ጭቅይት ፤ መጨቅየት ።

ጭቅይት ፡ አለ ፤ ጨቀየ ።

መጨቅየት ፤ ጭቃ ፡ ጮቂ ፡ ጨቀጨቅ ፡ መኾን ።

መጨቅያ ፤ መራሻ ፡ ክረምት ፡ ዝናም ፡ ውሃ ፡ ጭቃ ፡ መኾኛ ።

አጨቀየ ፤ ውሃ ፡ አጠገበ ፡ አራሰ ፡ አረካ ፡ ጭቃ ፡ አደረገ ፡ አላቈጠ ።


ማጨቅየት ፤ ማራስ ፡ ማላቈጥ ።

ማጨቅያ ፤ ማራሻ ፡ ጊዜ ፡ ስፍራ ።

ጨቀለ ፤ ወለደ ።

መጨቀል ፤ መውለድ ።

ጨቅላ ፡ (ሎች) ፤ ዐራስ ፡ ሊጋ ፡ ልጅ ፡ ሰውነቱ ፡ ያልጠና ፡ ያልጠነከረ ፡ ራሱን ፡ ያልቻለ ፡ ርጥብ ፡ ሕፃን ፡ (ዘፍ፭፫ ፡ ፲፫) ።



ጨቅላ ፡

ጫቅማ ፤ ጉሎ ፤ የጉሎ ፡ ዐይነት ፡ ዛፍ ።

ጨቈነ ፤ (ጸቈነ) ፤ ተጣነ ፡ ዐመቀ ፡ ረጠጠ ፤ በታች ፡ አደረገ ፤ ቀንበር ፡ ጣነ ፡ አገዛዝ ፡ አጸና ፡ አስጨነቀ ፡ አስቸገረ ፡ (ዓሞ፪ ፡ ፲፫) ።

ጨቈነ ፡ ጨረቀ ፡ ለሰቀ ።

ጨቋኝ ፡ (ኞች) ፤ የጨቈነ ፡ የሚጨቍን ፤ ተጣኝ ፡ ምቀኛ ።

ጨቋኝነት ፤ ጨቋኝ ፡ መኾን ፡ ተጣኝነት ።

ጨቈን ፤ (ጸቈን) ፤ ዐጪር ፡ የፍል ፡ የች ግኝ ፡ ዳስ ፡ ጀጉል ። የጨቈን ፡ ምስጢር ፡ ሽም ጥን ፡ ያያል ።

ጨቈን ፤ ከባድ ፡ ሸክም ።

ጭቈና ፤ ጫና ፤ የመጨቈን ፡ ሥራ ።

መጨቈን ፤ መጫን ፡ መጨፈቅ ።

መጨቈኛ ፤ መጫኛ ፡ መጨፈቂያ ።

ጨቋቈነ ፤ ጫን ፡ ጫን ፡ አደረገ ፤ ጨፋ ፈቀ ፡ አጠጋጋ ።

አስጨቈነ ፤ አስጫነ ፡ አስጨፈቀ ።

አስጨቋኝ ፤ ያስጨቈነ ፡ የሚያስጨቍን ።

ማስጨቈን ፤ ማስጫን ፡ ማስጨፈቅ ።

ማስጨቈኛ ፤ የሚከብድ ፡ ነገር ።

ተጨቈነ ፤ ተረጠጠ ፡ ታመቀ ፤ በታች ፡ ኾነ ፡ ተቸገረ ፡ ተጨነቀ ፡ (ሉቃ፮ ፡ ፴፰ ። ዓሞ፪ ፡ ፲፫) ።

ተጨቈን ፤ ተጨፈቀ ፡ ተለሰቀ ።

ተጨቋኝ ፤ የሚጨቈን ፤ ተጨፋቂ ፡ ተለሳቂ ።

ጭቍን ፤ (ጽቈን) ፤ የተጨቈነ ፤ ሌላ ፡ የተ ጫነው ፡ ሽምጥ ።

ጭቍኝ ፡ (ኛች) ፤ ችግኝ) ፤ ታላቅ ፡ ሽታ ፡ ያለው ፡ ቅጠል ፡ ባረንዛ ፡ መካከል ፡ ተጨቍኖ ፡ የሚ በቅል ፡ በመዐዛው ፡ ክፉ ፡ ሽታን ፡ የሚጨቍን ፡ ቅጠሉ ፡ ባፍንጫ ፡ ተወትፎ ፡ የሚጨቈን ።

ተጫቈነ ፤ ተጫጫነ ፤ ተጫፈቀ ።

ተጨቋቈነ ፤ ተጠጋጋ ፡ ተጨፋፈቀ ።

አጫቈነ ፤ አጫጫነ ፤ ወደ ፡ ታች ፡ አባባለ ፤ አጫፈቀ ።

አጨቋቈነ ፤ አጨናነቀ ፡ አጠጋጋ ፡ አጣ በበ ።

ተጭቈነቈነ ፤ እንደ ፡ ጭቍኝ ፡ ቅጠል ፡ ኾነ ፤ ተጣበበ ።

ጭቍንቍን ፤ (ጽቍንቍን) ፤ የተጭቈ ነቈነ ፤ ቅርብርብ ።

አጨቋቈነ ፤ አጫጫነ ፤ መጨቈን ።

ጭቅና ፡ (ኖች) ፤ የሥጋ ፡ ስም ፤ ካ፤፱ቱ ፡ የበሬ ፡ ብልት ፡ ፩ዱ ። ቀጪን ፡ ሠጥርና ፡ ሁላሊት ፡ ሥብ ፡ ያለበት ፡ ለመረቅ ፡ የሚፈለግ ፡ የሰብራዳ ፡ ክፍል ።

ጭቅቅት ፤ (ጸንቀቀ ፤ ጽንቅቅት) ፤ የመጨቅጨቂት ፡ ዐይነት ፡ ጥቅር ፡ እድፍ ፡ ቢያ ጥቡ ፡ አይጠራ ።

ጭቅቅታም ፤ ጭቅቅት ፡ ያለበት ፡ የበዛ በት ፡ ታጥቦ ፡ የማያውቅ ፡ ሰው ።

ጫቀታ ፤ በወለቃ ፡ አጠገብ ፡ ያለ ፡ አገር ።

ጫረ ፤ (ትግ ፡ ጸሐረ) ፤ መሬትን ፡ ሻጨረ ፡ በጥቂቱ ፡ (ላመል) ፡ ቈፈረ ፡ ኳተ ፡ ፋረ ፤ ወይም ፡ ጐደፈረ ፤ መነጨረ ፡ በተነ ፡ በሬው ፡ ሰዉ ።

ጫረ ፤ ክብሪትን ፡ በሣጥኑ ፡ ላይ ፡ መታ ። ክብሪት ፡ ጫረ ፡ እንዲሉ ።

ጫረ ፤ ፍምን ፡ ከምድጃ ፡ ዛቀ ፡ ወሰደ ። እሳት ፡ ጫረ ፡ እንዲሉ ።

ጫረ ፤ መናኛ ፡ ጽፈት ፡ ጻፈ ፡ ከተበ ።

ጫሪ ፡ (ዎች) ፤ ጸሐሪ) ፤ የጫረ ፡ የሚ ጭር ፤ ፋሪ ፡ ቈፋሪ ፡ ሻጫሪ ፡ ጐድፋሪ ፡ ጸፊ ። ፋመ ፡ ብለኽ ፡ ፍምን ፡ አስተውል ።

ጫሪ ፤ መንጫሪ ፡ በታኝ ።

ጫራ ፤ ያገር ፡ ስም ።

(ጥሬ) ጫሬ ፤ (ትግ ፡ ጽሒራ) ፤ መቃብር ፡ አፍ ራሽ ፡ ሬሳ ፡ አውጥ ፤ በግእዝ ፡ ጽዕብ ፡ ይባላል ።

ጫሬ ፤—አይጨስ ፡ ነዶድ ፤—ጨረረ ።

(ጥሬ) ጭሪ ፤ ጭሬ ፤ አፈ ፡ ቀይ ፡ አረጥ ፡ የከ ብትን ፡ ገላ ፡ የምትጭር ፡ ቍስልና ፡ መሸገር ፡ በል ፡ ወፍ ።

ጭሪዎች ፤ አረጮች ።

ጭሬ ፤ እኔ ፡ ለሚል ፡ ቦዝ ፡ አንቀጽ ፤ መን ጭሬ ፡ በትኜ ። (ተረት) ፤ ባልበላ ፡ ጭሬ ፡ አላፈ ስም ፡ ወይ ፡ አለች ፡ ዶሮ ።

(ላሬ) ጭሬ ፡ (ዎች) ፤ የጦር ፡ ስም ፤ ከአበታና ፡ ካፎቄ ፡ የሚያንስ ፡ ቅጠለ ፡ ጠባብ ፡ ጦር ፡ (ፎሳሙ ፡ ፲፯ ፡ ፵፩) ።

ጭር ፡ አለ ፤—ርጭ ፡ አለ ፤ ድምጥ ፡ ሰጠ ፤—ጨረረ ።

መጫር ፤ መቈፈር ፡ መሻጨር ፡ መፋር ፡ መዛቅ ፡ መጻፍ ።

መጫሪያ ፤ መቈፈሪያ ፡ መሻጨሪያ ፡ መው ሰጃ ፡ ዶማ ፡ ወንካሴ ፡ ጥፍር ፡ ገል ፡ (ዘኍ፬ ፡ ፲፬ ። ዘዳ፳፫ ፡ ፲፫) ።

መጫሪያዎች ፤ የእሳት ፡ ማንኮች ፡ (፩ነገ ፡ ፯ ፡ ፵ ፡ ፵፩) ።



መጫሪያዎች ፡

ጫጫረ ፤ ቈፋፈረ ፡ ሞጫጨረ ፤ ጻጻፈ ።

መጫጫር ፤ መቈፋፈር ፡ መሞጫጨር ።

መጫጫሪያ ፤ የዶሮ ፡ እግር ።

ጫር ፤ መጫር ።

ጫር ፡ አደረገ ፤ ጫረ ።

ጭር ፡ ጭር ፡ አደረገ ፤ ቈፈር ፡ ቈፈር ፡ ፋር ፡ ፋር ፡ ጸፍ ፡ ጸፍ ፡ አደረገ ።

አጫረ ፤ (አጽሐረ ፤ አፅረረ) ፤ ጦር ፡

ዠመረ፡ ፈለመ ፡ ፈተነ፡ ቈሰቈሰ፡ ቈረቈሰ፡ ቀነቀነ ።

አጣረ ፤ አሾተለ ፡ አደባ ፡ ሸመቀ ። ምነው ፡ ቢቀርብኽ ፡ መንግሥትና ፡ ድባብ ፤ እንዲህ ፡ ሰው ፡ ለመግደል ፡ አጭረኽ ፡ እንደባብ ፡ (አልቃሽ ፡ አቶ ፡ በዛብኽን) ።

አጣሪ ፡ (ዎች) ፤ ያጣረ ፡ የሚያጭር ፡ የጦር ፡ ቀንቃኝ ፡ ተቈራጽሽ ፡ (ፈሳሙ ፡ ፲፯ ፡ ፬) ።

አጣሪ ፡ ኾነ ፤ ነገር ፡ ፈለገ ፡ አነፈነፈ ፡ በቀንዱ ፡ ዐፈር ፡ ያዘ ፤ በእግሩ ፡ መሬት ፡ የሚጕ ደፍር ፡ በሬን ፡ መሰለ ።

ማጣር ፤ ጦር ፡ መቀንቀን ፡ ነገር ፡ መፈለግ ።

ማጣሪያ ፤ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ስፍራ ፡ ጊዜ ።

አስጣረ ፤ (አጽሐረ) ፤ አስኾጨረ ፡ አስ ቈፈረ ፡ አስኳተ ፡ አስፋረ ፡ አስጕደደረ ።

አስጣረ ፤ አሳትን ፡ አስወሰደ ፡ አስመጣ ።

አስጣሪ ፤ ያስጣረ ፡ የሚያስጭር ።

ማስጣር ፤ ማስኾጨር ፤ ማስቈፈር ፡ ማስ ፋር ።

ተጣረ ፤ (ተጽሕረ) ፤ ተኾጨረ ፡ ተቈ ፈረ ፡ ተኳተ ፡ ተፋረ ፡ ተጕደደረ ፡ ተበተነ ።

ተጣረ ፤ ተዛቀ ፡ ተወሰደ ፡ ፍሙ ።

ተጣጣረ ፤ ጦርነት ፡ ተጕመረ ፡ ተፋተነ ፡ ተቈራቈሰ ፤ ነገር ፡ ተፈላለገ ።

ተጣጣረ ፤ አሳትን ፡ ተበዳደረ ።

መጣጣር ፤ መጕመር ፡ መፋተን ።

ጭሮሽ ፤ ተጭሮ ፡ የወጣ ፡ የሠረገላ ፡ ውሃ ።

ጭረት ፤ (ጽሕረት) ፤ መጣር ፡ የመ ጣር ፡ ሥራ ።

ጭረት ፤ ሙጭር ፤ ጣር ፡ ተደርጎ ፡ የተ ጻፈ ፡ የዜማ ፡ የተመለስ ፡ ምልክት ።

ጭረት ፤—የቃጣ ፡ ባዘቶ ፤—ጨረተ ።

ጭረት ፤—የንጨት ፡ ሥር ፤—ጨ ረተ ።

ጭራ ፤ (ጽሕራ) ፤ ቈፍራ ። (ተረት) ፤ ዶሮ ፡ ጭራ ፡ መታረጃዋን ፡ አወጣች ። ዶሮ ፡ ጭራ ፡ የምታወጣው ፡ ምስጢር ። (የዝንጀሮ ፡ ግጥም) ፤ ልጂ ፡ ጭራም ፡ አትበላ ፤ እናይ ፡ ኋላ ።

ጭራ ፤—የኾራት ፡ ጣፍ ፤—ጨረረ ።

አጣጣረ ፤ አጕመረ ፡ ጠብን ።

አጣጣረ ፤ አዋሰደ ፡ ፍምን ።

አጣጣር ፤ አቈፋፈር ፤ መጣር ።

ጭራ ፤—የጨረር ፡ ብርሃን ፤—ጨ ረረ ።

ጭሬ ፤ (ጋላ) ፤ መጠጣጥ ።

ጭሬ ፤ ካዋሽ ፡ ወንዝ ፡ በስተግራ ፡ ያለ ፡ አገር ።

ጨረባ ፡ (ቦች) ፤ የወፍ ፡ ስም ፤ ብዙ ፡ ዅኖ ፡ የሚታይ ፡ ወፍ ፤ በቋል ፡ ጥሬ ፡ ፈጅ ። የጨ ረባ ፡ ተዝካር ፡ እንዲሉ ።

ጨረባ ፡



(ጨረገገ) ፤ ዠረገገ) ፤ አንጨረገገ ፤ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ አፈራ ፡ አንዠረገገ ፡ አንጠለጠለ ።

አንጨረገገ ፤ አጠቈረ ፤ የፊት ። በተደራ ጊነትም ፡ ይፈታል ።

እንጭርግ ፤ ያንጨረገገ ፡ የተንጨረገገ ፤ እ ንዠርግ ፡ እንጥልጥል ።

ማንጨርገግ ፤ ማንዠርገግ ፡ ማንጠል ጠል ፡ ማጥቈር ።

ተንጨረገገ ፤ ተንዠረገገ ፡ ተንጠለጠለ ።

ተንጨረገገ ፤ ጠቈረ ።

መንጨርገግ ፤ መንዠርገግ ፡ መጥቈር ።

መንጨርገጊያ ፤ ብዙ ፡ ማፍሪያ ፡ የፍሬ ፡ ወራት ።

ጨረገደ ፤ (ጠረገ ፡ ረገደ) ፤ ባንድነት ፡ ዐጨደ ፡ ቈረጠ ፡ ማርን ፡ ቅጠልን ።

ጨረገደ ፤ የተጠቀለለ ፡ እንጀራን ፡ ባፉ ፡ ቈረሰ ፡ ገመጠ ፡ በላ ።

ጨረገደ ፤ መታ ፡ ደበደበ ። እከሌ ፡ እከ ሌን ፡ በዱላ ፡ ጨረገደው ።

መጨርገድ ፤ ማጨድ ፡ መቍረጥ ፡ መግ መጥ ።

አስጨረገደ ፤ አሳጨደ ፡ አስቈረጠ ።

ተጨረገደ ፤ ታጨደ ፡ ተቈረጠ ።

ተጨረገደ ፤ ተቈረሰ ፡ ተገመጠ ፡ ተበላ ።

ጭርግድ ፤ የተጨረገደ ፤ ዕጭድ ።

ተጨራገደ ፤ ተጣጨደ ፡ ተቋረጠ ።

ተጨራገደ ፤ ተማታ ፡ ተደባደበ ፡ በበሎታ ።

መጨራገድ ፤ መተጣጨድ ፡ መማታት ።

አጨረጋገድ ፤ አስተጣጨድ ፤ መጨር ገድ ።

ጨርጨቤ ፤ ጠንቋይ ፡ በሰው ፡ ቁመት ፡ ልክ ፡ የሚጽፈው ፡ ከታብ ፡ አስማት ።

(ጨረጨረ) ፤ ጨረረ) ፤ አንጨረጨረ ፤ ያለሽክላ ፡ በፍም ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ ቈላ ፡ ጠበሰ ። በተገብሮነትም ፡ ይፈታል ።

አንጨረጨረ ፤ አስጮኽ ።

እንጭርጭር ፤ የተንጨረጨረ ፡ የጥሬ ፡ ባቄላ ፡ ቈሎ ፤ ጥብስ ፡ ሥጋ ።

ማንጨርጨር ፤ መቍላት ፡ መጥበስ ።

ማንጨርጨሪያ ፤ መጥበሻ ፤ ባንከርት ፣ ላይ ፣ ያለ ፣ ፍም ፣ መቊሊያ ።

ተንጨረጨረ ፤ እጅግ ፣ ተቈላ ፣ ተጠበሰ ።

ተንጨረጨረ ፤ መልሶ ፣ መላልሶ ፣ እንደ ፣ እንጥራር ፣ ጮኸ ።

መንጨርጨር ፤ መቈላት ፣ መጠበስ ፣ መ ጮኽ ።

መንጨርጨሪያ ፤ እሳት ፣ ጉረሮ ።

ጨርጨር ፤ በሐረርጌ ፣ ክፍል ፣ ያለ ፣ ሞ ቃት ፣ አገር ።

ጨረጨሰ ፤ (ጨረሰ ፣ ጠረሰ) ፤ አፈጀ ፣ ጨርሶ ፣ አረጀ ፤ ጥርሱ ፣ ረገፈ ። ጠረጠሰን ፣ እይ ፤ ከዚህ ፣ ጋራ ፣ አንድ ፣ ነው ።

ጭርጭስ ፤ የጨረጨሰ ፣ ያረጀ ፣ ያፈጀ ፣ ሽማግሌ ።

ጭርጭስ ፣ አለ ፤ ጨረጨሰ ፤ እርጅት ፣ አለ ።

መጨርጨስ ፤ ማፍጀት ፣ ፈጽሞ ፣ ማር ጀት ፣ ጥርስ ፣ ማጣት ።

ጨረመደ ፤ (ጨረመተ) ፤ ብዙ ፣ እን ጀራ ፣ በላ ። ጨረገደን ፣ እይ ።

ተጨረመደ ፤ ተበላ ።

ተጨራመደ ፤ ተወጣመደ ።

ጨርማዳ ፤ የተጨራመደ ፣ ወጥማዳ ። ጨ ረመተን ፣ ተመልከት ፤ ጸና ፣ ተ ፣ ተወራራሾች ፣ ስለ ፣ ኾኑ ፣ ጨረመተ ፣ በማለት ፣ ፈንታ ፣ ጨረ መደ ፣ ይላል ።

ጨረመመ ፤ (ጸረመ) ፤ ዘነበለ ፣ እንቅልፍ ፣ የገረዘዘው ፣ ሰው ፣ መሰለ ፤ ጠማማ ፣ ኾነ ፣ ቤቱ ፣ በክብደት ፣ ብዛት ።

ጨረመም ፤ ጨርማማ ፤ (ጸራሞ) ፤ የተጨረመመ ፣ ሊወድቅ ፣ የቀረበ ። ጸረመ ፣ ጸራሞ ፣ ጥንታዊ ፣ ዐማርኛ ፣ ነው ።

ተጨራመመ ፤ ተጣመመ ።

መጨራመም ፤ መጣመም ።

መጨራመሚያ ፤ መጣመሚያ ።

አጨራመመ ፤ አጣመመ ።

ማጨራመም ፤ ማጣመም ።

ማጨራመሚያ ፤ ማጣመሚያ ።

ጨረመተ ፤ ጨመተረ ፣ ጨመደደ ።

ተጨራመተ ፤ ተጨማተረ ፣ ተጨማደደ ።

መጨራመት ፤ መጨማተር ፣ መጨማ ደድ ።

መጨራመቻ ፤ መጨማተሪያ ።

ተጨረማመተ ፤ ተጨመዳደደ ።

ጭርምትምት ፤ የተጨረማመተ ፤ ጭም ትርትር ።

ጭርምትምት ፣ አለ ፤ ጭምትርትር ፣ አለ ፤ ተጨረማመተ ።

መጨረማመት ፤ መጨመታተር ፣ መጨ መዳደድ ።

አጨራመተ ፤ አጨማተረ ፣ አጨማደደ ።

ማጨራመት ፤ ማጨማተር ፣ ማጨማደድ ።

አጨረማመተ ፤ አጨመታተረ ፣ አጨመ ዳደደ ።

ማጨረማመት ፤ ማጨመታተር ፣ ማጨ መዳደድ ።

አጨረማመት ፤ አጨመታተር ፤ ማጨራ መት ።

ጨረንፌ ፤ ከአስታ ፣ ጋራ ፣ የሚበቅል ፣ ዕን ጨት ።

ጭራንፎ ፣ (ዎች) ፤ የጭራሮ ፣ ማፍ ፣ (ሚልፀ ፣ ፩ ። ሆሲፕፀ ፣ ፯) ።

ጨረንቀ ፤ (ደረንቀ) ፤ አሳነሰ ፣ ዐጪር ፣ አደረገ ፤ ጨቈነ ። ይህ ፣ ሽክም ፣ ወንጥፍን ፣ ጨረ ነቀው ።

ጨርናቂ ፤ የጨረነቀ ፣ የሚጨረንቅ ፤ ከ ባድ ፣ ነገር ።

መጨርነቅ ፤ ማሳነስ ፣ ማሳጠር ፣ መጨ ቈን ።

አስጨረነቀ ፤ አሳጠረ ፣ ዐጪር ፣ አስደ ረገ ፤ አስጨቈነ ።

ተጨረነቀ ፤ አነሰ ፣ ዐጠረ ፤ ተጨቈነ ።

ጨርናቃ ፤ የተጨረነቀ ፤ ወንጥ ፣ ዐጪር ፣ ሰው ።

ጭርንቅ ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ።

አጨረናነቅ ፤ አጨቃቈን ፤ መጨርነቅ ።

ጭርንቁስ ፤ ጨርቅ ፣ ቊረንጮ ፣ ባንድ ነት ፣ የተሰፋ ። ቅርንጥስን ፣ እይ ።

ጭርንቁሳም ፤ ጨርቃም ፣ ቊረንጪም ።

ጨረፈ ፤ (ፀረፈ ፤ ሰደበ) ፤ በቀላል ፣ መታ ፣ ቈረጠ ። የፀረፈ ፣ ምስጢር ፣ ስድቡ ፣ እንዳይጐዳ ፣ በትሩ ፣ አለመጉዳቱን ፣ ያሳያል ። (ጨነፈረ)ንና ፣ ስ ሙፈን ፣ ቈረፈን ፣ ተመልከት ።

ጨራፌ ፤ የጨረፈ ፣ የሚጨርፍ ።

መጨረፍ ፤ ጥቂት ፣ መምታት ፣ መቊረጥ ።

መጨረፊያ ፤ በትርና ፣ ስለት ።

አስጨረፈ ፤ ላመል ፣ አስመታ ፣ አስቈረጠ ።

አስጨራፌ ፤ ያስጨረፈ ፣ የሚያስጨርፍ ።

ማስጨረፍ ፤ ማስመታት ፣ ማስቈረጥ ።

ተጨረፈ ፤ በቀላል ፣ በጥቂት ፣ ሻጥለጥ ፣ ተመታ ፣ ተቈረጠ ።

ጭርፍ ፤ የተጨረፈ ።

ጠረፍታ ፤ ትከከል ፡ ያልኾነ ፡ የጐን ፡ ምት ፤ ወይም ፡ የማየት ፡ እኩሌታ ።

ቈርፋት ፤ (ጥጠ) የመጠረፍ ፡ ኹናቴ ።

አጠራረፍ ፤ ቀላል ፡ አመታት ፤ መጠረፍ ።

ቈራፍ ፤ ቡቃያ ፡ (ጐንደር) ።

(ጠረፈፈ) ፤ ጠፈረረ ፡ ጠበረረ) ፤ አንጠረፈፈ ፤ አንጠፈረረ ፡ አሳደገ ፡ አረመመ ፡ አቆመ ፡ አደረቀ ፤ ቈራንፎ ፡ አስመሰለ ፡ ጠጕርን ። በተደራጊነትም ፡ ይፈታል ። (ጠረፈፈ) ፡ ለጠጕር ፡ ብቻ ፤ (ጠፈረረ) ፡ ለሞራሮም ፡ ይነገራል ።

አንጠርፋፊ ፤ ያንጠረፈፈ ፡ የሚያንጠረፍፍ ፤ ጠጕር ፡ አሳዳጊ ።

እንቈርፍ ፤ የተንጠረፈፈ ፡ ያደገ ፡ የረዘመ ፡ የሸፍታ ፡ የናዝራዊ ፡ ጕፈሬ ።

ማንጠርፈፍ ፤ ማስረዘም ፡ ማቆም ፡ ማድረቅ ።

ማንጠርፈፈያ ፤ ራስና ፡ ጊዜ ።

ተንጠረፈፈ ፤ አደገ ፡ ረዘመ ፡ ቆመ ፡ ደረቀ ፡ ተንጠፈረረ ።

ጠረፈፍ ፤ ጠርፋፋ ፤ ጠፈረር ፡ ጠፍራራ ፤ እንቈርፍ ።

መንጠርፈፍ ፤ መንጠፍረር ፡ መርዘም ፡ መቆም ፡ የማርት ፡ ወስፌ ፡ መምሰል ።

መንጠርፈፈያ ፤ መንጠፍረሪያ ፡ መርዘሚያ ።

ጠረቀ ፤ (ጠሪቅ ፡ ጠረቀ ፤ ቀዘነ) ፤ ተከፈለ ፡ ጠብ ፡ ጠብ ፡ አለ ።

ጠረቀ ፤ (ሠረቀ) ፤ ወጣ ፡ ነጣ ።

ጠረቀ ፤ (ጸረቀ) ፤ ዐለቀ ፡ ሣሣ ።

ጠራቃ ፤ ሽንታም ፡ ፈሪ ።

(ጥር) ቈርቅ ፤ ጥቂት ፡ ሽንት ።

ቈርቂያም ፤ ቈርቅ ፡ የሚያደርግ ።

ቈርቅ ፡ አደረገ ፤ በጥቂቱ ፡ ሸነ ፡ ቀዘነ ፤ ሸንቱን ፡ ቈረጠ ።

ቈርቅ ፡ አለ ፤ ጠረቀ ።

ጮረቃ ፤ የከብት ፡ ሽንትና ፡ የዝናም ፡ ውሃ ፡ ካዛባ ፡ ጋራ ።

ጩርቅርቅ ፡ አለ ፤ (አንያረረ) ፤ ፈራ ፤ ሸንቱን ፡ ለቀቀ ፤ በሽንት ፡ ተበከለ ።

አጠረቀ ፤ (አሥረቀ) ፤ ሸንቱን ፡ ወረወረ ፡ ረጨ ፡ ፈነጠቀ ፡ እንደ ፡ ጮራ ።

አጠረቀ ፤ አወጣ ፤ አነጣ ።

አጠረቀ ፤ አሳለቀ ፡ አሣሣ ።

ማቈረቅ ፤ ጠብ ፡ ማድረግ ።

ጠረቃ ፤ (ሠርቅ) ፤ የሰማይ ፡ መብራት ፡ ስም ፤ የፀሓይ ፡ ታናሽ ፡ ወንድም ፤ ከፀሓይ ፡ የምትነሣው ፡ ብርሃኗ ፡ ከመላ ፡ በኋላ ፡ እያለቀ ፡ የሚኼድ ፡ ጠፍ ፡ የሚኾን ። ጠፍ ፡ ጠረቃ ፡ ሊጋ ፡ ጠረቃ ፡ ሙሉ ፡ ጠረቃ ፡ እንዲሉ ።



ጠረቃ ፡

ጠረቃ ፡ ዳቦ ፡ ጣይልኝ ፤ የልጆች ፡ ጨዋታ ።

ጠረቃ ፡ ምድር ፡ ያዘች ፤ ማታ ፡ ሳት ወጣ ፡ ጧት ፡ ወጣች ፤ ታየች ።

ጠረቃ ፡ ተወለደች ፤ ብቅ ፡ አለች ፡ በቀለች ፡ ተገለጠች ።

ጠረቂት ፤ (ጠረቃዊት) ፤ የማሽላ ፡ ስም ፤ ነጭ ፡ ማሽላ ። ፪ኛ ፡ ስኳ ፡ ወገሬ ፡ ይባላል ።

ጠርቅ ፡ (ቆች) ፤ ጸርቅ) ፤ የልብስ ፡ የሸማ ፡ ዕላቂ ፡ (ሕዝ፲፫ ፡ ፳ ፡ ፳፩) ።

ጠርቃም ፤ ባለጠርቅ ፡ ቅርንጥሳም ፡ ዘባተኛም ።

ጠርቂ ፤ ያ ፡ ጠርቅ ፤ የርሱ ፡ ጠርቅ ።

ጠርቂ ፤ የርኒ ፡ ጠርቅ ። ጠረቂ ፡ ብለኽ ፡ ጠርቂን ፡ አስተውል ።

ጠርቃጠርቅ ፤ የጠርቅ ፡ ጠርቅ ፤ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ጠርቅ ፡ የዕላቂ ፡ ዕላቂ ። በዘመናችን ፡ ግን ፡ ከባሕር ፡ የመጣውን ፡ ዐዲስ ፡ ልብስና ፡ ሐር ፡ ኹሉ ፡ ጠርቅ ፡ ይሉታል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። የባሕር ፡ ጠርቅ ፡ እንዲሉ ።

ጠርቅ ፡ ኾነ ፤ ለፋ ፡ ለተተ ፡ ለሰለሰ ፤ የቈርበት ፡ የሰው ፡ ገላ ።

ጠርቀ ፡ ለባሽ ፤ ቍርጩ ፡ መናጢ ፡ ድኻ ፡ ጠርቅ ፡ የሚለብስ ፡ (ማቴ፭ ፡ ፳፪) ።

ጩራቅ ፤ (ሚራክ) ፤ ዐዋቂ ፡ ብልኅ ፡ አራት ፡ ዐይና ። አከሌ ፡ ጩራቅ ፡ ነው ፡ እንዲሉ ። ፈረንጆች ፡ ዲፕሎማቲክ ፡ (ዕጥፍ ፡ ዐይን) ፡ ይሉታል ። ሲበዛ ፡ ጩራቆች ፡ ያሠኛል ። አራት ፡ ዐይና ፡ ማለትም ፡ ፍጹም ፡ ዕውቀትን ፡ እንጂ ፡ ዐይንን ፡ አያሳይም ። አራትን ፡ ተመልከት ።

ጩራቅ ፤ የሰው ፡ ዥብ ፡ ሰው ፡ በሌ ፤ ሰውን ፡ እያረደ ፡ የሚበላ ፡ ባላራት ፡ ዐይን ። በማዥራቱ ፡ ያለውን ፡ ፪ ፡ ዐይን ፡ በጠርቅ ፡ ይሸፍነዋል ፤ የሰው ፡ ሥጋ ፡ የሚቀቅልበት ፡ የብረት ፡ ጋን ፡ አለው ፡ ይባላል ። ምንም ፡ የሰው ፡ ሥጋ ፡ መብላቱ ፡ ርግጥ ፡ ቢኾን ፡ አራት ፡ ዐይን ፡ አለው ፡ ማለት ፡ ተረት ፡ ነው ። ኛምኛምን ፡ አይ ።

ጠረቋ ፤ (ትግ ፡ ጠልቅዐ) ፤ ፍሬ ፡ ዝመረ ፡ ጠርቋ ፡ ኾነ ።

ጨርቋ ፤ (ቀውዕ) ፤ እንጭጭ ፤ ለጋ ፣ ፍሬ ። ጨርቅና ፣ ጨርቋ ፣ ባማርኛ ፣ ይተባበራሉ ። (ግጥም) ፤ እንዲያ ፣ ስናከብራት ፣ እመቤት ፣ ብለን ፣ በጨርቋ ፣ ቀበሯት ፣ ምን ፣ ትዋብ ፣ ወሌን ።

ጨርቋዎች ፤ ለጋዎች ፣ ቃሪያዎች ።

ጨርቋ ፣ በርበሬ ፤ ቃሪያ ፣ ያልበሰለ ።

መጨርቋት ፤ ጨርቋ ፣ እንጭጭ ፣ መኾን ።

መጨርቀኣያ ፤ ጊዜ ፣ ወር ።

ጮረቃ ፤—ሽንትና ፣ ዐዛባ ፤—ጨረቀ ።

ጨርቆስ ፤ (ቂርቆስ) ፤ የሰው ፣ ስም ፤ በግ እዝ ፣ ቂርቆስ ፣ የተባለው ፣ በሕዝብ ፣ አነጋገር ፣ ጨርቆስ ፣ ይባላል ።

ጨርቆሴ ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ፤ የኔ ፣ ጨርቆስ ፤ ወይም ፣ ጨርቆሳዊ ። የወልደ ፣ ቂርቆስ ፣ ከፊል ፣ ነው ።

ጨረረ ፤ (ጠረረ ። ፀረረ) ፤ ነዛ ፣ ፈነጠቀ ፣ ላከ ፣ ሰደደ ፣ ብርሃንን ፤ ዘረጋ ፣ ጮራን ።

ጨረረ ፤ ወጋ ፣ አሳመመ ፣ ራስን ፣ ዐይንን ።

ጨረረ ፤ ነሰነሰ ፣ ወዘወዘ ፣ ጭራን ።

ጨረረ ፤ መታ ፣ ከለከለ ፣ ዕሽ ፣ አለ ፣ አበ ረረ ፣ ዝንብን ፣ ትንኝን ።

ጨረር ፤ ክብ ፣ የፀሐይ ፣ ሰሌዳ ፣ ጢትና ፣ ማታ ፣ የሚታይ ። ጨረሯ ፣ ወጋችኝ ፣ እንዲል ፣ ባሳገር ።

ጨረር ፤ ሰባት ፣ ያራባ ፣ ከፍል ። አራባን ፣ እይ ።

ጭራ ፣ (ምች) ፤ የኾራት ፣ የጋማ ፣ ማፍ ፣ ቅማ ። ቄንጎን ፣ ተመልከት ።



ጭራ ፣


ጭራ ፤ ባንድነት ፣ የታሰረ ፣ የናስ ፣ ሽቦ ። ናስን ፣ አስተውል ።

ጭራው ፤ አይያዝም ፤ ሲፈልጉት ፣ አይ ገኝም ፣ ሰውየው ።

ጭራው ፣ ጮሌ ፤ ብልጥ ፣ ሰው ።

ጭራውን ፣ ለበሰ ፤ ጭራውን ፣ አቅንቶ ፣ ሮጠ ፣ ፈረጠጠ ፣ ጋለበ ።

ጮራ ፤ (ጸር) ፤ የጨረር ፣ ብርሃን ፣ በመ ስኮት ፣ የሚገባ ፣ ጦር ፣ ምርቅና ፣ ጭራ ፣ ቅንድብ ፣ መስሎ ፣ የሚታይ ። ጀንበሯ ፣ ጮራ ፣ ሰደደች ፣ እን ዲሉ ።



ጮራ ፣

ጭር ፤ ርጭ ፣ ጸጥ ።

ጭር ፣ አለ ፤ (ጸርሐ) ፤ ጮኸ ፣ ድምጥ ፣ ሰጠ ፣ አሰማ ፣ አውራ ፣ ዶሮ ።

ጭር ፣ አለ ፤ ርጭ ፣ ጸጥ ፣ አለ ፤ ድምጥ ፣ ታጣ ። ፈትን ፣ ተመልከት ።

ጭር ፣ አለች ፤ ጮኸች ፤ ማጨቶጅን ፣ አስ ጠነቀቀች ፣ ዶርዋ ።

ጭር ፣ አለች ፤ ምድር ፣ ያዘች ፤ ተቀመ ጠች ፤ ዝም ፣ አለች ።

ጭርታ ፤ ጭር ፣ ማለት ፤ ዝምታ ፣ ጸጥታ ፣ ማታ ።

አንጫረረ ፤ አሳረረ ፣ አንጠበረረ ፣ አገ መነ ፣ አኰማተረ ፤ ገረፈ ፣ አጮኸ ።

እንጭራር ፣ (ሮች) ፤ ማታ ፣ ማታ ፣ የ ሚጮኽ ፣ ድምጠ ፣ ብዙ ፣ ጥቁር ፣ ተንቀሳቃሽ ፣ በክንፍ ፣ በራሪ ፤ እግሮቹ ፣ ፮ ፣ ሲኾኑ ፣ በራሱ ፣ ላይ ፣ ጭራ ፣ የሚመስል ፤ ፪ ፣ ቀንድ ፣ አለው ፤ ፪ኛ ፣ ስሙ ፣ ቢያርዱ ፣ አይሞት ፣ ነው ።



እንጭራር ፣

ማንጫረር ፤ ማቃጠል ፣ ማንጠብረር ፣ ማ ሳረር ፣ መግረፍ ፣ ማጮኽ ።

ተንጫረረ ፤ ተቃጠለ ፣ ተንጠበረረ ፣ ዐ ረረ ፣ ገመነ ፣ ተኰማተረ ፤ ጮኸ ።

ጫሬ ፤ ጪኺ ፣ ነጫሬ ።

ጫሬ ፤ አይጪስ ፣ ነደድ ፤ ቅጠሉ ፣ ምስር ፣ የሚመስል ፣ ዕንጨት ። እሳት ፣ ሲጠምሩት ፣ የሚ ንጫረር ። ጪሰን ፣ እይ ።

መንጫረር ፤ መቃጠል ፣ መንጠብረር ፣ ማረር ፣ መጮኽ ።

ጭርር ፣ አለ ፤ ዕርር ፣ አለ ፤ እንደ ፣ እን ጭራር ፣ ጮኸ ።

ጭራሮ ፣ (ምች) ፤ ደረቅ ፣ ዕንጨት ፣ ቀማ ጪን ፤ ሳይቈረጥ ፣ ፀሐይ ፣ አቃጥሎ ፣ ያደረቀው ።

ጭራሮ ፤ ቅንድብ ፡ ጭፋር ። ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ መዝጊያው ፡ ጭራሮ ፡ (እንቆቅልሽ) ።

ጭራሮ ፡ ደብር ፤ የቀበሌ ፡ ስም ፤ በታች ፡ ወግዳና ፡ በተጕለት ፡ ያለ ፡ የጭራሮ ፡ ደብር ፡ (ቤተ ፡ ክሲያን) ፤ ወይም ፡ ተራራ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ጮረረ ፤ (ያረረ ። ትግ ፡ ፀረረ) ፤ ወረደ ፡ ፈሰሰ ፡ ተንቈረቈረ ።

መንጮረር ፤ መውረጃ ፡ መፍሰሻ ፡ የጣራ ፡ አሸንዳ ።

ጭርጭር ፡ አለ ፤ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ ወ ረደ ፤ ጭልጭል ፡ አለ ።

ጨረሰ ፤ (ጠርሰ ፡ ፀርሰ) ፤ ፈጀ ፡ ገደለ ፡ ፈጸመ ፡ ከወነ ፡ ደመደመ ፡ አበቃ ፡ አከተመ ፡ በጥ ርስ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ መሣሪያ ።

ጨራሽ ፡ (ሾች) ፤ የጨረሰ ፡ የሚጨርስ ፤ ፈጻሚ ። ነገር ፡ ጨራሽ ፡ እንዲሉ ።

ጭረሳ ፤ ፍጸማ ፤ የመጨረም ፡ ሥራ ።

መጨረስ ፤ መፈጸም ፡ መከወን ።

መጨረሻ ፤ መፈጸሚያ ፡ ጊዜ ፡ (መከፔ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ። ራእ፭ ፡ ፳) ። (የሰው ፡ መጨረሻ) ፤ ፍ ጹም ፡ ደግ ፡ ሰው ።

ጨራረሰ ፤ ፈጸጸመ ።

አስጨረሰ ፤ አስፈጸመ ፡ አሳለቀ ፡ አስከ ወነ ።

አስጨራሽ ፤ ያስጨረሰ ፡ የሚያስጨርስ ፤ አስፈጻሚ ።

ማስጨረስ ፤ ማስፈጸም ፡ ማሳለቅ ።

ማስጨረሻ ፤ ማስፈጸሚያ ።

ተጨረሰ ፤ ተፈጀ ፡ ተገደለ ፡ ተፈጸመ ፡ ፀ ለቀ ፤ ተከወነ ፡ ተደመደመ ፡ (ኢዮ፴፪ ፡ ፲፭) ።

ጭርስ ፤ የተጨረሰ ፡ ያለቀ ።

ጭርስ ፡ አለ ፤ ፍጽም ፡ ዕልቅ ፡ አለ ።

ጭራሽ ፤ ንኡስ ፡ አገባብ ፤ ፈጽሞ ።

ጭራሽ ፤ ፍጻሜ ፡ መጨረሻ ። ጭራሹን ፡ አሳየ ።

ተጮረሰ ፤ ተጋደለ ፡ ተላለቀ ።

መጮረስ ፤ መጋደል ።

ተጨራረሰ ፤ ተገዳደለ ።

አጮረሰ ፤ አጋደለ ፡ አፋጸመ ፤ አደማደመ ።

አጮራሽ ፤ ያጮረሰ ፡ የሚያጮርስ ፤ አፋ ጻሚ ።

ማጮረስ ፤ ማጋደል ፡ ማፋጸም ።

ማጮረሻ ፤ ማፋጸሚያ ።

አጨራረሰ ፤ አፈጻጸመ ፡ አስተላለቀ ፡ አከ ነዋወን ።

ማጨራረስ ፤ ማፈጻጸም ።

ጨርሶ ፤ ፈጽሞ ፡ ደምድሞ ።

አጨራረስ ፤ አፈጻጸም ፤ መጨረስ ።

ጨረተ ፤ ተበተነ ፡ ባዘተ ፤ አሸዋ ፡ ጭራ ፡ መሰለ ፤ ነጣ ፡ ጭረት ፡ ጭርት ፡ ኾነ ።

ጨረተ ፤ ሰለለ ፡ ቀጠነ ።

ጨረተ ፤ ተጨመረ ፡ ታከለ ፡ በዛ ፡ ፈደ ፈደ ፤ የዋጋ ።

ጭረት ፤ የናጫ ፡ የሳማ ፡ የቃጫ ፡ የንሰት ፡ የጉናጉና ፡ የክሥዳ ፡ ባዘቶ ።

ጭረት ፤ የጣርና ፡ የንጨት ፡ ቀጪን ፡ ሥር ፡ የጭራ ፡ ዐይነት ።

ጭረት ፤—ሙጭር ፤—ጫረ ።

ጭርት ፤ ደቃቅ ፡ አሸዋ ፡ የሚመስል ፡ ነ ጭና ፡ ደረቅ ፡ ዕከክ ።

ጭርታም ፤ ጭርት ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ባለ ጭርት ።

አጨረተ ፤ ፋቀ ፡ ፈገፈገ ።

አጨረተ ፤ ቀጠቀጠ ፡ በተነ ፡ አባዘተ ፤ አ ነጣ ፡ ጭርት ፡ አደረገ ፤ ጭራ ፡ አስመሰለ ፤ አንድ ፡ የነበረውን ፡ ለያየ ፡ አበዛ ።

ማጭረት ፤ መፋቅ ፡ መቀጥቀጥ ፡ መበ ተን ፡ ማባዘት ፡ ማንጣት ።

ማጭረቻ ፤ ዕንጨት ፡ ጕድን ፡ ድንጋይ ፡ ውሃ ።

አስጨረተ ፤ አስፋቀ ፤ ጭረት ፡ ጭርት ፡ አስደረገ ።

ማስጨረት ፤ ቀላድ ፡ ቃጫ ፡ ማስመሰል ።

ተጫረተ ፤ ተፈካከረ ፡ ተበላለጠ ፤ ባ፤ ፩ ፡ በ፪ ፡ ፬ ፡ እሰጥ ፡ አክል ፡ እጨምር ፡ ተባባለ ፤ በግዥ ፡ ዋጋ ፡ ተለያየ ።

ተጫራች ፡ (ኞች) ፤ የተጫረተ ፡ የሚጫ ረት ፤ ተበላላጭ ፡ ተፈካካሪ ።

ጫረታ ፤ የዋጋ ፡ ብልጫ ፡ ፍክክር ።

መጫረት ፤ መበላለጥ ፡ መፈካከር ።

መጫረቻ ፤ የጎራጅ ፡ ቍን ፤ የሚሸጥ ፡ ዕቃ ።

አጫረተ ፤ አፋፈቀ ፡ አቀጣቀጠ ፡ አባተነ ፡ አለያየ ።

አጫረተ ፤ ዋጋ ፡ አሳረረ ፡ አባዛ ፡ አበላ ለጠ ፡ አፈካከረ ።

አጫራች ፡ (ኞች) ፤ ያጫረተ ፡ የሚያጫ ርት ፤ አፈካካሪ ፡ አበላላጭ ፡ ጎራጅ ፡ ባይ ።

ማጫረት ፤ ማበላለጥ ፡ ማፈካከር ።

ማጫረቻ ፤ ጊዜ ፡ ገበያ ፡ አደባባይ ።

ጭርቲ ፤ ድምጠ ፡ ሰላላ ፡ ዕድሜው ፡ የበዛ ፡ ጠጉሩ ፡ የነጣ ፡ አፍ ፡ ቂጡ ፡ የሸበተ ፡ ሽማግሌ ፡ ዥገፍ ። ነጨሬን ፡ ናጭርትን ፡ አስተውል ።

አጨራረት ፤ አበዛዘት ፤ ማጭረት ።

ጨረቻ ፤ (ጋላ) ፤ ያሸዋ ፡ ስም ፤ አሸዋ ።

ጨረች ፤ የሰው ፡ ስም ። (ተረት) ፤ ጭቅ ጭቅ ፡ ነው ፤ አቶ ፡ ጨረች ፡ ገዝተኹ ፡ ልበሱ ።

ጨሰ ፤ (ጠይስ ፡ ጤሰ) ፤ ተትጐለጐለ ፤ ቡልቅ ፡ ቡልቅ ፡ አለ ፤ በነነ ፡ ተነነ ፤ ታጠነ ።

ጨሰ ፤ ዐዘነ ፡ ነደደ ፡ ተከነ ፡ ገመነ ፤ የልብ ።

ጨስ ፤ (ጢስ) ፤ የጉም ፡ ዐይነት ፡ ብናኝ ፡ የእሳት ፡ እንፋሎት ፡ የማገዶ ፡ ውጥ ። የወገርት ፡ የቡክቡካ ፡ የዕጣን ፡ የልባንጃ ፡ የጽጌ ፡ ረዳ ፡ የማንኛውም ፡ የጨስ ፡ ዕንጨት ፡ መዐዛ ፡ መልካም ፡ ሽታ ። (ተረት) ፤ እንባ ፡ ሲኻኝ ፡ ዐይኔን ፡ ጨስ ፡ ወጋኝ ። ሥራ ፡ ጠፍቶ ፡ ጨስ ፡ ይሞቃል ።



ጨስ ፡

ጨሳም ፤ ጨስ ፡ የበዛበት ፡ ቤት ፡ ዋሻ ።

ጨሰኛ ፡ (ኞች) ፤ ጨስ ፡ የሚያጨስ ፡ ባለጨስ ፤ በሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ቤት ፡ ሠርቶ ፡ የሚኖር ። ጨስ ፡ ለጊዜው ፡ ታይቶ ፡ በኋላ ፡ እንዲታጣ ፡ ጨሰኛም ፡ መሬትን ፡ ለቆ ፡ ይኼዳልና ፤ በዚህ ፡ ስም ፡ ተጠራ ። (ተረት) ፤ ያተር ፡ ከምር ፡ የጨሰኛ ፡ ክብር ።

ጨሰኛ(ኝ)ነት ፤ ጨሰኛ ፡ መኾን ።

ጨስ ፡ አባይ ፤ የጥቊር ፡ አባይ ፡ ጭጭቱ ፡ ብናኝ ።

ጨስ ፡ ጨስ ፡ አለ ፤ ለበላተኛ ፡ አፍ ፡ የጨስ ፡ ጣዕም ፡ ሰጠ ፡ ምግቡ ።

መጨስ ፤ መትጐልጐል ፡ መብነን ፡ መትነን ።

መጨሻ ፤ የንጀራ ፡ የወጥ ፡ የንፍሮ ፡ ቤት ፡ ምድጃ ።

አጨሰ ፤ አበነነ ፡ አተነነ ፤ ዕጣንን ፡ የጨስ ፡ ዕንጨትን ፡ ዐጠነ ።

አጨሰ ፤ ጨሰኛ ፡ ኾነ ፤ በሰው ፡ ምድር ፡ ተቀመጠ ።

አጨሰ ፤ ትንባኾ ፡ (ስጃራ) ፡ ጠጣ ።

አጨሰ ፤ አሳዘነ ፡ አናደደ ፡ አቃጠለ ፡ አገመነ ።

አጫሽ ፡ (ሾች) ፤ ያጨሰ ፡ የሚያጨስ ፤ ጨሰኛ ።

አጫሽነት ፤ አጫሽ ፡ መኾን ፤ ጨሰኛነት ።

ማጨስ ፤ ግብነን ፡ ማትነን ፤ ማሳዘን ፡ ማናደድ ።

ማጨሻ ፤ ገል ፡ ግርግራት ፡ ዐይነ ፡ ተኵላ ፡ ጥና ።

አስጨሰ ፤ ጨስ ፡ አስደረገ ፤ አሳጠነ ።

አስጨሰ ፤ አስኖረ ። (አያስጨስም) ፤ አያስኖርም ።

ማስጨስ ፤ ማሳጠን ፤ ማስኖር ።

ተጫጫሰ ፤ ተፋፋመ ፡ ተያያዘ ፡ በዛ ፡ ጨሱ ፤ በረታ ፡ ጠቡ ።

መጫጫስ ፤ መያያዝ ፡ መፋፋም ።

መጫጫሻ ፤ ጊዜና ፡ ስፍራ ።

አጫጫሰ ፤ አያያዘ ፡ አፋፋመ ።

አጫጫሽ ፤ ያጫጫሰ ፡ የሚያጫጭስ ።

ማጫጫስ ፤ ማያያዝ ፡ ማፋፋም ።

ማጫጫሻ ፤ ዙበትና ፡ ዕንጨት ፡ ግብስ ብስ ፡ ፋንድያ ።

አይጨስ ፤ የማይጨስ ።

አይጨስ ፡ ነደድ ፤ የንጨት ፡ ስም ፤ ርጥቡን ፡ ከእሳት ፡ ሲጠምሩት ፡ ሳይጨስ ፡ የሚነድ ፡ ታናሽና ፡ ቀጪን ፡ ዕንጨት ። ኹለተኛ ፡ ስሙ ፡ ጫሬ ፡ ይባላል ። ጠረረን ፡ ተመልከት ።

አጫጫስ ፤ አበናነን ፤ መጨስ ።

ጫታ ፤—ዝምታ ፤—(ጫጫ) ።

ጫት ፤ (ወዕአ ፤ ፃት) ፤ ርጥብ ፡ ዐራስ ፡ ልጅ ። አመጣት ፡ እንዲሉ ።

ጫት ፡ (ቶች) ፤ የተክል ፡ ስም ፤ ለጋውን ፡ ቅንበጡን ፡ እስላሞች ፡ የሚያኝኩት ፡ ዕንጨት ። ጫትና ፡ ቡና ፡ እንዲሉ ። ባረብኛ ፡ ቃት ፡ ይባላል ።



ጫት ፡

ጫት ፤ ጭሪ ፡ ገጣባ ፡ ለመብላት ፡ በከበት ፡ ዝርባ ፡ የምትታዘል ፡ ወፍ ፡ (ጉጉም) ።

ጫት ፡ አሞራ ፤ ሳቢላ ፡ በበሬ ፡ ዝርባ ፡ ላይ ፡ ቁሞ ፡ ዝጣ ፡ የሚሻገር ።

ጫተረ ፤ (ትግ ፡ ጸሕተረ) ፤ መሬትን ፡ ቈፈረ ፡ ጉደፈረ ፤ ለውጢያ ፡ አጫረ ። ጫረን ፡ እይ ፤ ሥሩ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ጫተረ ፤ ለፋ ፡ ደከመ ፡ በሥራ ። ዛሬ ፡ ስጫትር ፡ ውዬ ፡ መጣኹ ።

ጫታሪ ፤ ጫታራ ፤ የጫተረ ፡ የሚጫ
ትር ፤ የለፋ ፡ የደከመ ።
መጫተር ፤ መልፋት ፡ መድከም ።
መጫተሪያ ፤ መልፊያ ፡ መድከሚያ ።
አጫተረ ፤ አለፋ ፡ አደከመ ።

አጫተረ ፤ (ጫተረ) ፤ አሾተለ ፡ አደባ ።
አጫታሪ ፤ ያጫተረ ፡ የሚያጫትር ፤ አልፊ ፡
አድካሚ ።
ማጫተር ፤ ማልፋት ፡ ማድከም ።
ማጫተሪያ ፤ ማልፊያ ፡ ማድከሚያ ፡ ሥራ ፡
ስፍራ ።

የ

የ ፤ ፲ኛ ፡ ፊደል ፡ በአበገደ ፡ በጥንታዊው ፡
ተራ ፡ ቊጥር ፤ በፊደልነት ፡ ስሙ ፡ የማን ፤ በአጋዝ
ነት ፡ የ—፲ ፡ ይባላል ።
የ ፤ (ዘ) ፤ በጎላፊ ፡ አንቀጽ ፡ መነሻ ፡ ዅሉ ፡
እየገባ ፡ ባለቤት ፡ ሳይኖር ፡ በቂ ፤ ይኾናል ። የበላ ፡
በለጠኝ ፤ የሮጠ ፡ አመለጠኝ ። ያረገዘች ፡ ታስታ
ውቅ ፤ ከደረቷ ፡ ትታጠቅ ። የፈሩት ፡ ይደርሳል ፤
የጠሉት ፡ ይወርሳል ። አባት ፡ ያበጀው ፡ ለልጅ ፡
ይበጀው ። ዘመን ፡ የወለደው ፡ ንጉሥ ፡ የወደደው ።
፩ኛውን ፡ ይ ፡ ተመልከት ።
የ ፤ (ዘ) ፤ ባለቤት ፡ ሲኖር ፡ ቅጽል ፡ ይኾ
ናል ። ያልሰማ ፡ ጕሮ ፡ ከጎረቤት ፡ ያጣላል ። የሞተ ፡
ልጅ ፡ ወንጌ ፡ ረኽሮ ፡ ነው ። ዘመን ፡ የሰጠው ፡
ቅል ፡ ደንጊያ ፡ ይሰብራል ። ለና ፡ የ ፡ ሲቀድሙት ፡
ተውጦ ፡ ይቀራል ። (ግጥም) ፤ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡
ለወደደው ፡ ከሳት ፡ ያወጣል ፡ ከነደደው ። ለየወደ
ደው ፡ ከየነደደው ፡ ማለት ፡ ነው ።
የ ፤ (ዘ) ፤ የዘርፍ ፡ ደፊ ፤ ወይም ፡ አያያዥ ።
የሰማይ ፡ አምላክ ፤ የአቤል ፡ መሥዋዕት ፤ የሙሴ ፡
ጽላት ፤ የሰሎሞን ፡ መቅደስ ። የልጅ ፡ ጥፉ ፡ በስም ፡
ይደግፉ ፡ ቢል ፤ ጥፉ ፡ የኾነን ፡ ልጅ ፡ ያሠኛል ።
ቅጽልን ፡ ከነተሳቢው ፡ ሲደፋ ፤ ያህያ ፡ ውሃ ፡ ጠጪ ፡
ይላል ። ፩ኛውን ፡ ያ ፡ እይ ።
የ ፤ (ዚአ) ፤ ባለገንዘብነትን ፡ የሚገልጥ ፡
ጠቃሽ ፤ ይኸውም ፡ አያያዥ ፡ ካለው ፡ ይገባል ።
ይህ ፡ ቤት ፡ የሱ ፡ የሷ ፡ የኔ ፡ የኛ ፡ የነኛ ፡ የናንተ ፡
ያንተ ፡ ያንቺ ፡ ነው ።
የ ፤ (ኢ) ፤ አሉታ ። (ጥለ) አለ ፡ የለ ። ፪ኛ
ውን ፡ የለ ፡ ተመልከት ።
ዩ ፤ የዘማ ፡ ምልክት ። ሥረይን ፡ አስተ
ውል ።
ዪ ፤ (ኢ) ፤ የሣልስ ፡ ፊደል ፡ መሠረት ።
አዩ—ኢ ፤ በዩ—ቢ ። መዝገበ ፡ ፊደል ፡ አስተውል ።
ያ ፤ (ውእቱ) ፤ የሩቅ ፡ ወንድ ፡ ደቂቅ ፡
ቅጽል ፡ ይኾናል ፤ ትርጓሜው ፡ እሱ ፡ ርሱ ። ያ ፡
ሰው ። ያ ፡ ሲበዛ ፡ እኒያ ፡ እሊያ ፡ ይላል ፤ በስፍ
ራው ፡ ተመልከት ፤ ያችን ፡ እይ ።

ያ ፤ (ውእቱ) ፤ የሩቅ ፡ ወንድ ፡ በቂና ፡
ወጸፋ ። ያ ፡ ይምጣ ፤ ያ ፡ ይቅር ። ያ ፡ ሌላ ፤ ይኸ ፡
ሌላ ። ያ ፡ ይሙት ፤ ያ ፡ ይዳን ። ከደቂቅ ፡ አገባብም ፡
ጋራ ፡ በስቲያ ፡ ወዲያ ፡ እንዲያ ፡ እያለ ፡ ይነገራል ፤
በገቢርም ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ይላል ።
ያ ፤ (የማ) ፤ የትንቢት ፡ አሉታ ፡ በቂና ፡
ቅጽል ፡ መነሻ ። ያይወድ ፡ ያይለያይ ፡ ያይጠላ ፡
(ግር ፡ ይሥ ፡ ገጽ ፡ ፱) ።
ያ ፤ ምእላድ ፡ እየኽነ ፡ በቃል ፡ መጨረሻ ፡
ይገባል ። ጠደፈ ፡ ጥድፊያ ፤ ጻፈ ፡ መጻፊያ ፤ ጠረገ ፡
መጥረጊያ ፤ እንግድ ፡ እንግዲያ ፤ እንከ ፡ እንኪያ ፤
ቀረበ ፡ አቀረበ ፡ አቅራቢያ ፤ ዘመመ ፡ አዘመመ ፡
አዝማሚያ ።
ያ ፤ (አ) ፤ ለሩቅ ፡ ቤት ፡ ለሩቆች ፡ ለቅርቦች ፡
ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ የአንቀጽና ፡ የዝርዝር ፡ አያ
ያዥ ፤ ፍቺው ፡ ርሱ ። ይኸውም ፡ ወወቀ ፡ ያት ፡
ያቸው ፡ ያችኹ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፤ ራሱን ፡ ጕርዶ ፤
ዐወቃት ፡ ዐወቃቸው ፡ ዐወቃችኹ ፡ እያለ ፡ በርባታ ፡
ጊዜ ፡ የአንቀጹን ፡ መድረሻ ፡ ራብዕ ፡ ማድረጉን ፡
ያሳያል ። ያ ፡ ስምን ፡ አ ፡ አካልን ፡ ይተረጕማል ። ስም
ንም ፡ ከዝርዝር ፡ ሲያያይዝ ፤ እጃችን ፡ እግራችን ፡
ቀበሌ ፡ ቀበሌያችን ፡ ዕድሜ ፡ ዕድሜያችን ፡ ይላል ።
አንድ ፡ ዐይነት ፡ ቅጽልንና ፡ ስምን ፡ ሲያናብብ ፤
ገራገር ፡ ወንዛወንዝ ፡ ያሠኛል ።
ያ ፤ ኛ ። መቅኒያ ፡ መቅኛ ።
ያ ፤ (ዊ) ፤ ወገን ፡ ቅጽል ። ቅጠል ፡ ቅጠ
ልያ ፤ አባት ፡ አባትያ ፤ እናት ፡ እናትያ ፤ ሥስትያ ፡
አራትያ ፡ ዐምስትያ ። ማን ፡ አስተውል ። ያገርን ፡
ባለቤት ፡ ሲገልጽ ፤ ኢትዮጵ ፡ ኢትዮጵያ ፤ አርመን ፡
አርማንያ ፤ እስክንድር ፡ እስክንድርያ ፤ ሮም ፡ ሮምያ ፡
ይላል ።
ያ ፤ የግስ ፡ ጣልቃ ። ሠጠ ፡ ተንሢያጠጠ ፡
እንሢያጠጠ ።
ያ ፡ ሌላ ፤ ይኸ ፡ ሌላ ፤ ያ ፡ ቊጥታ ፤
ይኸ ፡ ሚዋጥታ ፤ ምን ፡ ገጥሞት ።
ዬ ፤ (ኤ) ፤ የኃምስ ፡ ፊደል ፡ ዅሉ ፡ መሠ
ረት ። አዬ—ኤ ፤ በዬ—ቤ ። መዝገበ ፡ ፊደል ፡ እይ ።

ዬ ፤ ዕሠይ ፡ ወሰው ፡ እኮ ። አበባዬ ፡ መስ ከረም ፡ ጠባዬ ።

ዬ ፤ (ኢ) ፤ የግድንቅ ፡ ቃል ። ዬ ፡ ወን ድሜ ፡ አንተ ፡ ታግሠሽኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ እኔስ ፡ የበደልኩሽ ፡ በደል ፡ ብዙ ፡ ነበር ።

ዬ ፤ ጊዜ ። አንደዬ ፡ ዐሥረዬ ። አንድና ፡ ዐሥር ፡ ለዬ ፡ ቅጽሎች ፡ ናቸው ።

ዬ ፤ (ዊ) ፤ ባገር ፡ ስም ፡ መጨረሻ ፡ እየ ገባ ፡ ለተወላጅ ፡ በቂ ፡ ይኾናል ። የጁ ፡ የጁዬ ፤ ወሎ ፡ ወሎዬ ።

ዬ ፤ ወገን ፡ ቅጽል ። ድንክ ፡ ድንክዬ ።

ዬ ፤ (ወዮ) ፤ የሐዘንና ፡ የጸጸት ፡ ቃል ። ዬ ፡ ቤቴን ፡ በጊዜው ፡ ሳልከድን ፡ ዝናም ፡ ቢጥል ፡ እን ዴት ፡ እኾናለኹ ። (ግጥም) ፤ ማሽላዬ ፡ ወማይ ፡ በላሽ ፡ ወዬ ። ዬዬንና ፡ እዬዬን ፡ ተመልከት ።

ዬ ፤ (የ) ፤ በራብዕና ፡ በኃምስ ፡ በሳብዕ ፡ ፊደል ፡ በሚጠርስ ፡ ስም ፡ እኔ ፡ ለሚል ፡ ዝርዝር ። ሥራ ፡ ሥራዬ ፤ ዕጣ ፡ ዕጣዬ ፤ ጌታ ፡ ጌታዬ ፤ ፍሬ ፡ ፍሬዬ ፤ ከበሮ ፡ ከበሮዬ ፡ ማሲንቆ ፡ ማሲንቆዬ ።

ይ ፤ ለሩቅ ፡ ወንድ ፡ ለሩቆች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ የትንቢት ፡ የዘንድ ፡ የትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ መነሻ ። ገደለ ፡ ይገድል ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ ይግ ደል ። አንቀጹ ፡ በአዐ ፡ ሲነሣ ፡ ከትእዛዝ ፡ በቀር ፡ ያ ፡ ይኾናል ። አመነ ፡ ያምን ፡ ያምን ፡ ዘንድ ። ዐረፈ ፡ ያርፍ ፡ ያርፍ ፡ ዘንድ ። ባስደራጊም ፡ አስቀደሰ ፡ ያስ ቀድስ ፡ ያስቀድስ ፡ ዘንድ ፡ ያስቀድስ ፡ ይላል ።

ይ ፤ በለ ፡ የሚጠርስ ፡ ግስ ፡ የሚልስ ፡ ቅጽል ፡ መድረሻ ። ከፈለ ፡ ከፋይ ፤ ከለለ ፡ ከላይ ፤ ፈነገለ ፡ ፈንጋይ ፤ ሰቀለ ፡ ሰቃይ ። ይኸውም ፡ የና ፡ ለ ፡ ተወ ራራሽ ፡ መኾናቸውን ፡ ያስረዳል ።

ይ ፤ (ዊ) ፤ ወገን ፡ ቅጽል ። ድንግል ፡ ድን ግላይ ፤ ጎምር ፡ ጎምራይ ፤ ሾተል ፡ ሾተላይ ።

ይ ፤ በትንቢት ፡ መነሻ ፡ እየገባ ፡ በቂ ፡ ይኾ ናል ። ድኻ ፡ ይበላው ፡ እንጂ ፡ ይከፍለው ፡ አያጣም ። ይኸውም ፡ በየሚ ፡ ፈንታ ፡ የተነገረ ፡ ነው ።

ዮ ፤ (ሆይ) ፤ ንኡስ ፡ አገባብ ፤ የአንከሮና ፡ የአጋኖ ፡ የአክብሮ ፡ ቃል ። ሰውዮ ፡ ሴትዮ ።

የቦ ፤ (ጋላ) ፤ የጦር ፡ ስም ፤ ታናሽ ፡ ጦር ፡ ጭሬ ።

ይባዝ ፤ በይፋት ፡ ከፍል ፡ ያለ ፡ ቀበሌ ። (ግጥም) ፤ የማሀለ ፡ ሥላሴ ፡ ጠላቱ ፡ ከበዛ ፡ ይጣ ፡ ይኼድ ፡ እንጂ ፤ ይባዝን ፡ አይግዛ ።

የባጕስ ፤—ገሮ ፡ ቄራጭ ፤—ባጕሰ ።

ያቤሎ ፤ በሲዳሞ ፡ ከፍል ፡ ያለ ፡ አገር ።

ይበል ፤—ይናገር ፤—ባለ ።

ይብላኝ ፤—በቁሙ ፤—በላ ።

ይብራ ፤ የውሃ ፡ ዶሮ ፡ እውሃ ፡ ውስጥ ፡ ጠ ልቃ ፡ የምትወጣ ፡ እግሯ ፡ ቀይ ፡ መልክ ፡ ብዙ ፡ (ዘሌ ፲፩ ፡ ፲፮) ። ዝዙን ፡ ተመልከት ። ትእዛዝ ፡ እን ቀጽ ፡ ሲኾን ፤ በራ ፡ ይበራል ፤ ይብራ ፡ ይላል ።



ይብራ ፡

የብስ ፤ (የብሰ) ፤ ደረቅ ፡ ምድር ፡ ባሕር ፡ የሌለባት ።

ይብሽ ፤ ቅጥራን ፤ የቅጥራን ፡ ዐይነት ።

የገቦ ፤ (ዘገቦ) ፤ የጐን ፤ በጐን ፡ የሚወጣ ፡ የሚያፈጠፍጥ ፡ የሚያቈጠቍጥ ፡ የማሽላ ፡ ቅጥይ ፤ የበቈሎ ፡ ፍሬ ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ገቦ ፡ ይላል ፡ (ዘሌጽ፭ ፡ ፭) ። ገቦ ፡ በግእዝ ፡ ጐን ፡ ማለት ፡ ነው ።

የገቦ ፤ ሳይዘሩት ፡ የሚበቅል ፡ እሸል ፤ ወፍ ፡ ዐራሽ ፡ (ዘሌጽ፭ ፡ ፲፩) ። የገቦ ፡ ማለት ፡ በመ ከር ፡ ጊዜ ፡ ረግፎ ፡ እመሬት ፡ የገባ ፡ መኾኑን ፡ ያስ ረዳል ። ገባን ፡ እይ ፤ አንቀጹ ፡ ርሱ ፡ ነው ።

ይግባኝ ፤—ይሰማልኝ ፤—ገባ ።

የጕድፍ ፤—በቁሙ ፤—ጕያፈ ።

የጁ ፤ (የእጁ) ፤ ያገር ፡ ስም ፤ የቀድሞ ፡ ስሙ ፡ ገነቴ ፡ ነው ። አለቃ ፡ ታየ ፡ የጻፉትን ፡ የኢ ትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ታሪክ ፡ ተመልከት ።

ይዲ ፤ ይበል ፡ ዲያቆን ፡ (ቅዳሴ) ።

የዲያ ፤ የዚያ ፡ የሞ ። ዲያ ፡ የዳያብሎስ ፡ ከፈል ፡ ነው ።

ይድኖ ፤ ከሸማ ፡ በስተግራ ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ስም ።

ይህ ፤ (ዝ) ፤ የቅርብ ፡ ዐጸፋና ፡ ጭብጥ ፡ ቅጽል ። ባይን ፡ የሚታይ ፡ በእጅ ፡ ሊጨበጥ ፡ የሚ ቻል ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ይባላል ። ይህ ፡ ሲበዛ ፡ እኒህ ፡ እሊህ ፡ ያሠኛል ። ይሽን ፡ እይ ፤ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሰው ፡ ቅጽል ፤ ይህ ፡ ነው ፡ ዐጸፋ ። ከደቂቅ ፡ ጋራ ፡ ሲናበብ ፡ እን ዲህ ፡ ወዲህ ፡ ይላል ።

ይህን ፤ የገቢር ፡ ቅጽል ። ይህን ፡ ብትሰጥ ፡ ምን ፡ ትውጥ ።

ይህን ፡ ያልመታ ፡ የማሪያም ፡ ጠላት ፤ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ ዛፍን ፡ በድንጋይ ፡ ይመግራሉ ፤ (ይደበድባሉ) ።

ይህንን ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ይሽንን ፡ ተመል ከት ።

ይሁዳ ፤ (የሀደ) ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ካ፤፪ቱ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ አንዱ ። ትርጓሜው ፡ አማኒ ፡ (አማን) ፡ ማለት ፡ ነው ። ሌሎችም ፡ በዚህ ፡ ስም ፡

የሚጠሩ ፣ ሰዎች ፣ አሉ ። ይሁዳ ፣ የጌታችን ፣ ወንድም ፤ ይሁዳ ፣ አስቆሮታዊ ፣ እንዲሉ ።

ይሁዲ ፤ (ዐረ) ፤ ይሁዳዊ ፤ የይሁዳ ፣ ወገን ፣ ወይም ፣ ነገድ ፤ ነገደ ፣ እስራኤል ፤ ፈላሻ ፣ ግዙር ።

ይሁዲነት ፤ (ይሁድና) ፤ ይሁዲ ፣ መኾን ፣ ፈላሻነት ፣ (ግብ ፣ ሐዋ፮ ፣ ፭) ።

ይሁዲዎች ፤ አይሁድ ፣ አይሁዶች ።

አይሁድ ፤ የይሁዳ ፣ ነገዶች ፤ እስራኤሎች ። ፤ሩ ፣ ነገድ ፣ በያዕቆብ ፣ እስራኤል ፣ እንደ ፣ ተባሉ ፣ በይሁዳም ፣ አይሁድ ፣ ተብለዋል ፣ (አስቴ፫ ፣ ፮ ። ዮሐ፮ ፣ ፲፱) ።

አይሁዶች ፤ ዝኒ ፣ ከማሁ ፤ አይሁድ ፣ የግ እዝ ፤ አይሁዶች ፣ ያግርኖ ፣ ነው ።

ይሀታ ፤ (ይሀችታ) ፤ ታን ፣ ተመልከት ።

ይሀች ፤ (ይሀ) ፤ ለቅርብ ፣ ሴት ፣ ዐጸፋና ፣ ቅጽል ። ይሀች ፣ ሴት ፣ ይሀች ፣ ናት ።

ያው ፤ (ያ) ፤ እሱ ፣ ነው ፤ አለ ። ው ፣ ከነው ፣ መጥቶ ፣ ከያ ፣ ተደርጎል ። ሲዘረዝር ፣ ያውልሽ ፣ ያውልሽ ፣ ያውላችኹ ፣ ያውልኽ ፤ ሲደጋገም ፣ ያው ፣ ያው ፣ ይላል ። ያውልኹ ፣ እማገሩ ፤ ክፉ ፣ አትናገሩ ።

ያውልሽ ፤ ዕንካ ፣ ውሰደው ። (ግጥም) ፤ ጣዩ ፣ የልሽ ፣ የልሽ ፤ ዝናቡ ፣ የልሽ ፣ የልሽ ፤ ትዘራውም ፣ እንደኹ ፣ ቅብቅቡ ፣ ያውልሽ ።

ያውና ፤ ያ ፣ እሱ ፤ ው ፣ ነው ፤ ና ፣ እንሆ ። በተገናኝ ፣ እንሆ ፣ እሱ ፣ ነው ፤ (በሩቅ) ፣ አለ ። ና ፣ ከናሁ ፣ መጥቷል ። (የባለጊ ፣ ግጥም) ፤ ያውና ፣ እዚያ ፣ ማዶ ፣ ዘፍ ፣ ይወዛወዛል ፤ ያንቺ ፣ ልብ ፣ እንዴት ፣ ነው ፤ የኔስ ፣ ይናውዛል ። ያውና ፣ እዚያ ፣ ማዶ ፣ ፍሪዳ ፣ ተጥሏል ፤ ቢላዋው ፣ ደንዘ ፣ ልብ ፣ አልቄርጥ ፣ ብሏል ። ፈሪዳ ፣ የተባለው ፣ ጌታችን ፣ ኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ ነው ።

የዋሀ ፤ (የውሀ) ፤ ኀር ፣ ቅን ፣ ሞኝ ፤ እንስሳ ፣ ደንሴ ። ሠረየን ፣ ርግብን ፣ ረባ ፣ ብለኽ ፣ ርባታን ፣ ተመልከት ።

የዋህ ፣ ኾነ ፤ (ተየውሀ) ፤ ለዘበ ፣ ኀራ ፤ ወደ ፣ ወሰዱት ፣ ኼደ ።

የዋህነት ፤ ኀርነት ፣ ሞኝነት ።

የዋሆች ፤ ኀሮች ፣ ሞኞች ፣ እከይ ፣ አልቦች ።

የወል ፤—የተራራ ፣ ስም ፤—ወለለ ።

ያዘ ፤ (አኀዘ) ፤ አፈፍ ፣ ለቀም ፣ አደረገ ፤ ከእጅ ፣ አኀባ ፣ ጨበጠ ፤ ተሸከመ ፣ ቻለ ፣ አኀመረ ፣ ወሰነ ። (እፍንጣውን ፣ ያዘ) ፤ ዐፈነ ፣ ደፈነ ። (በወጦመድ ፣ ያዘ) ፤ ዐነቀ ። (በልብስ ፣ ያዘ) ፤ ታቀፈ ። (ባፍ ፣ ያዘ) ፤ ጐረሠ ። (ልጓም ፣ ያዘ) ፤ ገታ ። (መግል ፣ ያዘ) ፤ ዐቈረ ፣ ጸጠረ ። (ሥጋ ፣ ያዘ) ፤ ወፈረ ። (ሥራ ፣ ያዘ) ፤ ረባ ፣ ጠቀመ ፣ አገለገለ ። (ሥር ፣ ያዘ) ፤ አሥር ፣ ኀባ ፣ ተመለሰ ። (ዐይን ፣ ያዘ) ፤ ጨለመ ፤ ማየት ፣ ከለከለ ። (ቀለም ፣ ያዘ) ፤ አጠና ፣ ዐወቀ ፤ ልብ ፣ አደረገ ። (ቂም ፣ ያዘ) ፤ በልቡ ፣ አሳደረ ። (ስፍራ ፣ ያዘ) ፤ ቆመ ፣ ተደገፈ ። ያዘ ፣ በነገር ፣ ኹሉ ፣ እየ ኀባ ፣ እንዳመጣጡ ፣ መፈታቱን ፣ አስተውል ። (ተረት) ፤ ከበሮ ፣ በሰው ፣ እጅ ፣ ያምር ፤ ሲይዙት ፣ ያደናግር ። አፍን ፣ እይ ።

ያዢ ፣ ዥ ፣ (ገሮች) ፤ የያዘ ፣ የሚይዝ ፤ ተሸካሚ ፣ ጨባጭ ፣ ገቺ ፣ ጐበዝ ። ያዢ ፣ ሲይዘው ፣ ብረት ፣ ያራል ። ጠመንዣ ፣ ያዥ ፣ ሰናድር ፣ ያዥ ፣ እንዲሉ ።

ያዝ ፤ (እኂዝ) ፤ መያዝ ።

ያዝ ፣ አደረገ ፤ በፍጥነት ፣ ያዘ ።

ያዝ ፣ ለቀቅ ፤ መያዝ ፣ መልቀቅ ።

መያዝ ፤ መጨበጥ ፣ መግታት ፣ (ሕዝ፴ ፣ ፵፩) ።

መያዣ ፤ መጨበጫ ፣ መቋጠሪያ ፣ መሸከሚያ ፤ እጅ ፣ ከረጢት ፣ ስልቻ ፣ ቃሬዛ ፣ መረብ ፣ መግለቦ ፤ የመሰለው ፣ ኹሉ ። ሥንቅ ፣-መያዣ ፣ ሬሳ ፣ መያዣ ፣ ዕቃ ፣ መያዣ ፣ ዓሣ ፣ መያዣ ፣ እንዲሉ ።

መያዣ ፤ የድንኳን ፣ መግጠሚያ ፣ ሜንጦ ፣ (ዘፀ ፳፮ ፤ ፮ ፣ ፲፩) ። ሲበዛ ፣ መያገሮች ፣ ይላል ፣ (ዘፀ ፴፭ ፣ ፲፩) ።

መያጋ ፤ እጀታ ፣ ቀለበት ፣ ገሮ ።

መያዣ ፤ የጥቍር ፣ ጤፍ ፣ እንጀራ ፤ ወይም ፣ ከስንዴ ፣ ጋራ ፣ የተቀየጠ ፣ ዘኬ ፣ ነጭ ፣ በላዩ ፣ ኹኖ ፣ የሚያዝበት ፣ በላተኛን ፣ መግቻ ፤ የማለፊያና ፣ የጋሬ ፣ መካከለኛ ።

መያዣ ፤ ተበዳሪ ፣ ላበዳሪ ፣ የሚሰጠው ፣ ተመላሽ ፣ ነገር ፣ (ዘፍ፴፰ ፤ ፲፰ ፣ ፳) ።

መያዣ ፤ ዕጉቻ ፣ (ዘዳ፳፬ ፤ ፮ ፣ ፲ ፣ ፲፯ ። ኢዮ፳፬ ፣ ፫ ። ዓሞ፪ ፣ ፰) ።

ማዝ ፤ ያይን ፣ በሽታ ፣ ሸፋሸፍትን ፣ ይዞ ፣ የሚበላ ፣ የሚመልጥ ።

አሲያዘ ፤ (አእኀዘ) ፤ አስጨበጠ ፣ እጅ ፣ አስደረገ ። (በሽታ ፣ አሲያዘ) ፤ አጋባ ። (የውሻ ፣ በትር ፣ አሲያዘ) ፤ ቢያክ ፣ ቢያክ ፣ አለ ፤ አረከሰ ።

አሲያዘ ፤ መያዣ ፣ ሰጠ ፣ አደረገ ፣ (ነሐ ፭ ፣ ፬) ። እከሌ ፣ ርስቱን ፣ አሲዞ ፣ ገንዘብ ፣ ተበደረ ።

አሲያዘ ፤ የባለዳን ፣ ቤት ፣ ንብረት ፣ በዘበኛ ፣ አስጠበቀ ። ከበረ ፣ ብለኽ ፣ አስከበረን ፣ ተመልከት ።

አሲያዥ ፣ (ገሮች) ፤ ያሲያዘ ፣ የሚያሲዝ ። ወንድና ፣ ሴትን ፣ ለመለየት ፣

አሲያዦ ፤ ያ ፣ አሲያዥ ።

አሲያዢ ፤ ያሲያዘች ፣ የምታሲዝ ፤ ያች ፣ አሲያዥ ።

ማሲያዝ ፤ ማስጨበጥ ፣ ማስገታት ።

ማሲያዣ ፤ ማስጨበጫ ፣ ጊዜ ፣ ስፍራ ፣ መሣሪያ ።

ተያዘ ፤ (ተኣኀዘ) ፤ ተጨበጠ ፡ ተገታ ። ሠለጠ ፡ ብለኸ ፡ ሥልጣንን ፡ እይ ።

ተያዘ ፤ እወጥመድ ፡ ገባ ።

ተያዘ ፤ ተዋሰ ፤ በጉዶለ ፡ እመላለኹ ፡ በጠፋ ፡ እተካለኹ ፡ አለ ። (ቤቱ ፡ ተያዘ) ፤ በዳኛ ፡ እጅ ፡ ኾነ ።

ተያዢ ፡ ዥ ፡ (ጕሾች) ፤ የሚያዝ ፡ የሚጨበጥ ፤ ዋስ ፡ መድን ፡ ጎላፊ ፡ ተጠያቂ ።

ተያዥ ፤ የሚያዘው ፤ የርሱ ፡ ተያዥ ፤ ያ ፡ ተያዥ ።

ተያኒ ፤ የርሷ ፡ ተያዥ ፤ ያች ፡ ተያዥ ።

ተያዥ ፡ ኾነ ፤ መድን ፡ ኾነ ፤ ተዳነ ።

ተያዥነት ፤ ተያዥ ፡ መኾን ፡ ዋስትና ።

ተይዟል ፤ ለሰው ፡ ተረክቧል ፡ ዕቃው ፡ ገንዘቡ ፡ ቤቱ ፤ ተያዥ ፡ ኾኗል ፡ ዋሱ ።

ተይዟል ፤ በጠና ፡ ታሟል ።

መያዝ ፤ መጨበጥ ፡ እሰው ፡ እጅ ፡ መግባት ፡ መገታት ፤ መዋስ ።

መያዣ ፤ ጊዜ ፡ ስፍራ ፡ ወጥመድ ፡ ጠፍር ፡ ገመድ ፡ ጕድጓድ ።

ተያያዘ ፤ (ተኣኀዘ) ፤ ተጣመረ ፡ ተቈላለፈ ፡ ተጣበቀ ፤ ተቀጣጠለ ፡ ነደደ ፤ ተጣላ ፤ ግብ ግብ ፡ አለ ፤ ታገለ ፡ ተናነቀ ፡ (ማቴ፲፭ ፡ ፲፬) ።

ተያያዥ ፤ የሚያያዝ ፡ የሚታገል ።

መያያዝ ፤ መጣመር ፡ መቀጣጠል ።

መያያዣ ፤ ሰንሰለት ፡ ቁራሮ ፡ ጥቂት ፡ ገንዘብ ።

አያያዘ ፤ (አስተኣኀዘ) ፤ አገናኘ ፡ አጣመረ ፡ አቈላለፈ ፡ አዋሰበ ፡ አጣበቀ ፤ አቀጣጠለ ፡ አነደደ ፤ አጣላ ፡ አስተናነቀ ።

አያያዥ ፤ ያያያዘ ፡ የሚያያይዝ ፤ አቈላላፊ ፡ አቀጣጣይ ። ዘረፈ ፡ ብለኸ ፡ ዘርፍን ፡ ተመልከት ።

ማያያዝ ፤ ማገናኘት ፡ ማቈላለፍ ፡ ማቀጣጠል ፡ ማጣላት ፡ ማስተናነቅ ።

ማያያዣ ፤ ማቀጣጠያ ፡ ማንደጃ ፤ ቁራንፎ ፡ ግባስ ።

ይዘት ፡ (ቶች) ፤ እኀዘት) ፤ መያዝ ። የዜማ ፡ ምልክት ፡ አንዲት ፡ ነጥብ(.) ፤ የንባብ ፡ ማጥበቂያም ፡ ትኽናለች ። መዝገበ ፡ ፊደል ፡ እይ ።

ይዘታ ፡ (ዎች) ፤ የተያዘ ፤ በጅ ፡ ወደር ፡ ነገር ።

አይዞኽ ፤ (ኢ.ይእኀዘከ) ፤ ንኡስ ፡ አገባብ ፤ የማጽናትና ፡ የማበርታት ፡ ቃል ። አይዝኽም ፤ አይ ነካኽም ፤ ቢነካኽም ፡ አይጐዳኽም ፤ በርታ ፡ ጽና ፡ ማለትን ፡ ያሳያል ። አይዞኽ ፡ ወንድሜ ፤ ተሠራው ፡ ጋሜ ፡ እንዲል ፡ ሐርበኛ ፡ የጥምቀት ፡ ለት ። አይ ዞኽ ፡ አይዟችኹ ፡ እያለ ፡ በቅርብ ፡ በቅርቦቹ ፡ ብቻ ፡ ይነገራል ።

አይዞኽ ፡ ባይ ፤ ረዳት ፡ ደጋፊ ፤ የሚያጽናና ።

ያዝ ፤ (አኀዝ) ፤ አንሣ ፡ ጨብጥ ፡ አንግብ ፡ (መዝ፹፰ ፡ ፪) ።

ያዝ ፤ ቶሎ ፡ በል ፤ ንከስ ። ባላገር ፡ ግን ፡ ጃስ ፡ ዙቲ ፡ ይላል ።

አያያዝ ፤ አጨባበጥ ፤ መያዝ ። (ተረት) ፤ ካያያዝ ፡ ይቀደዳል ፤ ካነጋገር ፡ ይፈረዳል ።

የዚያ ፤—የሱ ፤—ዚያ ።

ይሕ ፤ ይበሉ ፡ ሕዝብ ፡ (ቅዳሴ) ።

ዮሐንስ ፤ (ጽርእ) ፤ የለው ፡ ስም ፤ በዕብራይስጥ ፡ ዮሐናን ፡ ይባላል ። ትርጓሜውም ፡ እግዜር ፡ ምሕረቱን ፡ ሰጠ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዳግመኛም ፡ ደስታ ፡ ተብሎ ፡ ይተረጐማል ፡ (ሉቃ፩ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬) ። ሌሎችም ፡ በዚህ ፡ ስም ፡ የሚጠሩ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። የሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ የሐንስ ፡ ወልደ ፡ ነጐድጓድ ፡ የሐንስ ፡ መደብር ፡ የሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ እንዲሉ ።

የዊ ፤—ወዲያ ፤—ዕዊ ።

ይጣ ፤—ቀበሌ ፤—ዐጣ ።

የየ ፤ (ዘዘ) ፤ የደጊመ ፡ ቃል ፡ በቂ ። በነገር ፡ መነሻ ፡ እየገባ ፡ የስሙን ፡ መጠረሻ ፡ ፊደል ፡ ካዕብ ፡ አድርጎ ፡ ይነገራል ። የያገሩ ፡ የያንዳንዱ ፡ የየሰዉ ፡ ብሎ ፡ ደንብን ፡ ጠባይን ፡ ጕዳይን ፡ ማን ኛውንም ፡ ነገር ፡ ያሳያል ።

የዬ ፤ (ጋላ) ፤ የተዙላ ፡ ስም ፤ ተዙላ ።

ዬዬ ፤ ወየ ፡ ወየ ። ዬን ፡ ተመልከት ፤ ይህ ፡ የሱ ፡ ደጊመ ፡ ቃል ፡ ነውና ።

እዬዬ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ የሐዘንና ፡ የለቅሶ ፡ ቃል ። ዬ ፡ ዬዬ ፡ የማእዝ ፤ እዬዬ ፡ ያማርኛ ፡ ነው ።

እዬዬ ፡ ቢ.ዩላ ፡ ነው ፤ እዬዬ ፡ ብሎ ፡ ማልቀስ ፡ ባገር ፡ አማን ፡ ነው ። ደላ ፡ ብለኸ ፡ ተዳላን ፡ አስተውል ።

የካ ፤ (ጋላ ፡ ኤካ ፤ እውነት ፡ ነው) ፤ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ በስተምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ያለ ፡ ቀበሌ ። የካ ፡ ሚካኤል ፡ እንዲሉ ።

ይካ ፤ ይበል ፡ ካህን ፡ (ቅዳሴ) ።

ይኸ ፤ (ይህ) ፤ የይህን ፡ አፈታት ፡ ተመልከት ፤ ለማናበብና ፡ ሌላ ፡ ፊደል ፡ ለመጨመር ፡ ይህ ፡ ይኸ ፡ ተብሏል ።

ይኸው ፤ ው ፡ የነው ፡ ከፊል ፡ ነው ፤ ይኸ ፡ ነው ፡ አለ ፡ ያሠኛል ። ሲዘረዝርም ፡

ይኸውልዎ ፤ ይኸው ፡ አለልዎ ።

ይኸውለት ፤ ይኸው ፡ አለለት ።

ይኸውልኽ ፤ ይኸው ፡ አለልኽ ።

ይኸውልሽ ፤ ይኸው ፡ አለልሽ ።

ይኸውላቸው ፤ ይኸው ፡ አለላቸው ።

ይኸውላችኹ ፤ ይኸው ፡ አለላችኹ ።
ይኸውላት ፤ ይኸው ፡ አለላት ፡ ይላል ።
ይኸውና ፤ እንሆ ፡ ይኸ ፡ አለ ፤ እንሆ ፡ የተ ባለው ፡ ና ፡ ከግእዛዊ ፡ ቃል ፡ ከናሁ ፡ የተከፈለ ፡ ነው ።
ይኸን ፤ (ዘንተ) ፤ የገቢር ፡ ቅጽል ። ይኸን ፡ ጊዜ ፤ ይኸን ፡ ነገር ፡ ተው ። ይህን ፡ እይ ።
ይኸንን ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ይህንን ፡ አስተ ውል ።
ያኸል ፤—የሚያኸል ፤—አከለ ።
የከሰ ፤ (ትግ ፡ ወከሰ) ፤ ጠየቀ ፤ ጥያቄ ፡ አቀረበ ።
የካሸ ፡ (ሾች) ፤ የየከሰ ፡ የሚየከስ ፤ ጠያቂ ።
ተየከሰ ፤ ተጠየቀ ። ልማዱ ፡ ግን ፡ ጠየቀ ፡ ነው ።
ተየካሸ ፤ የተየከሰ ፤ ተጠያቂ ። ለጉባኤ ውም ፡ ለተየካሹ ፡ ምነው ፡ ቢገቡ ፡ ኾነ ፡ ምላሹ ፡ (ኪ ፡ ወ ፡ ክ) ።
የየካሸ ፡ የተየካሸ ፤ የጠያቂ ፡ የተጠያቂ ፤ ወይም ፡ ራሱን ፡ እሱ ፡ ጠይቆ ፡ እሱው ፡ መልስ ፡ የሚሰጥ ፤ ሌላ ፡ መልስ ፡ ሰጪ ፡ የሌለው ። መም ሀራን ፡ ግን ፡ የተየካሸ ፡ ተየካሸ ፡ ይሉታል ፡ (ትር ጓሜ ፡ ትምህርተ ፡ ኅቡኣት) ።
የካቲት ፤ (ከተተ) ፤ የወር ፡ ስም ፤ ፯ኛ ፡ ወር ፡ ከመስከረም ። የመከር ፡ መከተቻ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ከተተን ፡ እይ ።
(ላለ) የለ ፤ ባለ ፡ (ሐማሴን) ።
የለ ፤ የል ፤ (ኢሀለወ) ፤ አለ ፡ ያለውን ፡ የለ ፡ በማለት ፡ የሚነገር ፡ አፍራሽ ፡ አሉታ ፡ አ ንቀጽ ። ሌለን ፡ ተመልከት ። በ፰ ፡ ሰራዊት ፡ በዋ ዌና ፡ አለዋዊ ፡ ሲነገር ፤ ዋዊውም ፡ ም ፡ ነው ።
የለ ፤ የለም ፤ (ኢሀለወ ፤ ወኢሀለወ) ፤ እሱ ፡ የለ ።
የለኽ ፤ የለኽም ፤ (ኢሀሎከ ፤ ወኢሀ ሎከ) ፤ አንተ ፡ የለኽ ።
የሉ ፤ የሉም ፤ (ኢሀለዉ ፤ ወኢሀለዉ) ፤ እነዚያ ፡ የሉ ።
የላችኹ ፤ የላችኹም ፤ (ኢሀሎክሙ ፤ ወኢሀሎክሙ) ፤ እናንተ ፡ የላችኹ ።
የለች ፤ የለችም ፤ (ኢሀለወት ፤ ወኢ ሀለወት) ፤ እሷ ፡ የለች ።
የለሽ ፤ የለሽም ፤ (ኢሀሎኪ ፤ ወኢሀ ሎኪ) ፤ አንቺ ፡ የለሽ ።
የለኹ ፤ የለኹም ፤ (ኢሀሎኩ ፤ ወኢ ሀሎኩ) ፤ እኔ ፡ የለኹ ።
የለን ፤ የለንም ፤ (ኢሀሎነ ፤ ወኢሀ ሎን) ፤ እኛ ፡ የለን ፡ ይላል ። ሲዘረዝርም ፡

የለው ፤ የለውም ፤ (ኢሀለዎ ፤ ወኢሀ ለዎ) ፤ ዕውቀት ፡ የለው ።
የለኽ ፤ የለኽም ፤ (ኢሀለወከ ፤ ወኢ ሀለወከ) ፤ ኀንዘብ ፡ የለኽ ።
የላቸው ፤ የላቸውም ፤ (ኢሀለዎሙ ፡ ን ፤ ወኢሀለዎሙ ፡ ን) ፤ ትጋት ፡ የላቸው ።
የላችኹ ፤ የላችኹም ፤ (ኢሀለወክሙ ፡ ን ፤ ወኢሀለወክሙ ፡ ን) ፤ ዕውቀት ፡ የላችኹ ።
የላት ፤ የላትም ፤ (ኢሀለዋ ፤ ወኢሀ ለዋ) ፤ አላንድ ፡ የላት ፤ እንቅልፍ ፡ የላት ። ነቀሰ ንና ፡ (ቀለፋ) ፡ ብለኽ ፡ እንቅልፍን ፡ ተመልከት ።
የለሽ ፤ የለሽም ፤ (ኢሀለወኪ ፤ ወኢ ሀለወኪ) ፤ ምንም ፡ የለሽ ።
የለሽ ፤ የሌለው ። ዋስ ፡ የለሽ ፡ እንዲሉ ።
የለኝ ፤ የለኝም ፤ (ኢሀለወኒ ፤ ወኢሀ ለወኒ) ፤ ኀንዘብ ፡ የለኝ ።
የለን ፤ የለንም ፤ (ኢሀለወነ ፤ ወኢሀ ለወነ) ፤ ዕውቀት ፡ የለን ፡ ይላል ። ግእዝ ፡ መጪ መሩ ፡ ያማርኛውን ፡ ሞክሼ ፡ ለመለየት ፡ ነው ።
የሊ ፤ (ዔሊ) ፤ ድንጋይ ፡ ልብሱ ። አዐና ፡ የ ፡ ተወራራሽ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ባላገር ፡ በዔሊ ፡ ፈንታ ፡ የሊ ፡ ይላል ፤ በእተጌ ፡ ፈንታ ፡ ይተጌ ፡ እንዲል ። ዔሊን ፡ እይ ።
(ጥለ) ያለ ፤—የነበረ ፤—አለ ፤ (ሀለወ) ።
ያለ ፡ የሌለ ፤—የነበረ ፤ ያልነበረ ፤—አለ ፤ (ሀለወ) ።
(ላለ) ያለ ፤—የተናገረ ፤—አለ ፤ (ብሀለ) ።
ያለ ፤ (አለ) ፤ እንበለ) ፤ አለ ፡ በገባበት ፡ እየገባ ፡ ሲነገር ፤ ያላገባብ ፡ ያለደንብ ፡ ያለውድ ፡ በግድ ፡ ያለልክ ፡ ያለመጠን ፡ ያላቅም ፡ ያለፈቃድ ፡ ማለቱን ፡ ያሳያል ። ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ በአለ ፡ ተራ ፡ ተመልከት ። ዚህና ፡ ዚያ ፡ ዘርፍ ፡ ሲኾኑት ፤ ያለ ዚህ ፡ ያለዚያ ፡ ይላል ። ፍችውም ፡ በአለ ፡ ተጽ ፏል ።
ያል ፤—በቂና ፡ ቅጽል ፤—አል ።
ያለኽ ፤—የያዝኽ ፤—አለ ፤ (ሀለወ) ።
የሎሂ ፤ ኤሎሄ ።
የሎሄ ፡ የሎሄ ፡ አሉ ፤ የጭንቅ ፡ ጩ ኽት ፡ ፖኽ ፤ ኢዮሄ ፡ ኢዮሄ ፡ አለ ። ኤሎሄና ፡ ኢ ዮሄ ፡ የሎሄ ፡ ይቱ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ናቸው ።
የሌለ ፤—ያልነበረ ፤—ሌለ ።
ያላለ ፤—ያልተናገረ ፤—አል ።
ይሎ ፤ የጣራ ፡ ማዋቀሪያ ፡ ረዥም ፡ አጣና ፤ ተለብልቦ ፡ የተላጠ ፡ ተራዳ ።

የልካ ፤ (ጋላ ፡ ኢልካን) ፤ የዝናን ፡ ጥርስ ፡ አንባር ።

ይላማ ፤ (ዐላማ) ፤ ምልክት ፤ ወርውረው ፡ የሚወጉት ፡ ተኩሰው ፡ የሚመቱት ፡ ነገር ። ጊጤን ፡ እይ ።



ይላማ ፡

(ጥማ) **ይልማ ፤** በመንዝ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ቀበሌ ፡ የጠይቦች ፡ ገዳም ፡ የሚገኝበት ።

ይልማና ፤ በጐጃም ፡ ክፍል ፡ ያለ ፡ አገር ።

ይሉኝ ፤—በቁሙ ፤—አለ ፤ (ብሀለ) ።

ይሉኝታ ፤—በቁሙ ፤—አለ ፤ (ብሀለ) ።

ይልቅ ፤—ይበልጥ ፤—ላቀ ።

የሎስ ፡ (ሶች) ፤ ያሞራ ፡ ስም ፤ ንስር ፡ ግልገል ፡ እንሣ ፡ መቀነትማ ። የሎስ ፡ ያንሣኸ ፡ እንዲሉ ። መልኩ ፡ በስተገርባው ፡ ጥቁር ፡ አረን ጓዴ ፡ በስተፊቱ ፡ ከላድማ ፡ ነው ፤ ባፉና ፡ በክንፉ ፡ በእግሮቹ ፡ ላይ ፡ ንጣት ፡ አለው ። ከክንፍ ፡ እስከ ፡ ክንፉ ፡ ጅ ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ።

የሚ ፤ (ዘይ) ፤ በትንቢት ፡ መነሻ ፡ እየ ገባ ፡ ለሩቅ ፡ ወንድ ፡ ለሩቆች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ቅጽልና ፡ በቂ ፡ ይኾናል ። የሚሞት ፡ ሽማግሌ ፡ አይርገምሽ ። የሚያድግ ፡ ልጅ ፡ አይጥላሽ ። የሚማሩ ፡ ልጆች ። የሚመጣ ፡ ይምጣ ። አመነ ፡ አሳየ ፡ ዐወቀ ፡ ብሎ ፡ የትንቢቱን ፡ ቅጽል ፤ የሚያምን ፡ የሚያሳይ ፡ የሚያውቅ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፤ የሚአምን ፡ የሚአሳይ ፡ የሚዐውቅ ፡ ማለት ፡ የስሕተት ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

የማ ፤ (ዘኢይ) ፤ የትንቢት ፡ አሉታ ፡ በቂ ፡ ቅጽል ፡ መነሻ ። የማይሠራ ፡ አይብላ ። የማይማር ፡ የማይማሩ ። አይን ፡ ተመልከት ።

የም ፤ (ዘ) ፤ ለቅርቦቹ ፡ ለርቱ ፡ ሰራዊትና ፡ እኔ ፡ እኛ ፡ ለሚሉ ፡ በትንቢት ፡ መነሻ ፡ እየገባ ፡ ቅጽልና ፡ በቂ ፡ ይኾናል ። የምትማር ፡ (አንተ ፡ እሷ) ፡ የምትማሩ ፡ የምትማሪ ፡ የምማር ፡ የምን ማር ። ተመልሰሽ ፡ የሚን ፡ እይ ።

ያም ፤ (ውእቱኒ) ፤ ም ፡ ዋዌ ፡ ነው ። ያም ፡ ኾነ ፡ ያም ፡ ኾነ ፡ ሞት ፡ አይቀርም ። ያን ፡ አስተውል ።

ያም ፡ ያም ፤ አንዱም ፡ አንዱም ።

የምቡት ፡ የምቡት ፤ የልጆች ፡ ፈሊጥ ። የምቡት ፡ የምቡት ፤ ይሽን ፡ ያልመታ ፡ ይሞት ።

ይማም ፤ (አመመ ፤ ቀደመ ። ዐረ ፡ ዐመመ ፤ ጠመጠመ) ፤ የስላም ፡ ስም ፤ ግን ባር ፡ ቀደም ፡ ካህን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ባላባትነት ንም ፡ ያሳያል ።

ይማሞች ፤ ግንባር ፡ ቀደሞች ፡ ዋኖች ፡ የወሎ ፡ ባላባቶች ።

ይማማ ፤ (ዐረ ፡ ሚማማ) ፤ የይማሞች ፡ ጥምጥም ። አመመን ፡ እይ ።

የማን ፤ የፈደል ፡ ስም ፡ የ ፤ ቀኝ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ይማና ፤—ያደራ ፡ ገንዘብ ፤— አመነ ።

ይመናሹ ፤—ይዋጉ ፤—መንሽ ።

የምሥራች ፤—የደስታ ፡ ወሬ ፤—ምሥራች ።

የምር ፤—የውነት ፤—መረረ ።

የምሩ ፤—የውነቱ ፤—መረረ ።

የኔ ፤ (የእኔ) ፤ መዝመሪያውን ፡ የ ፡ ባጩኛ ፡ ተራ ፡ ተመልከት ።

የኔታ ፤ የኔ ፡ (የእኔ) ፡ ጌታ ፡ ጌታዬ ፤ አስተማሪዬ ፡ መምሬ ።

ያን ፤ (ያ) ፤ ውእተ) ፤ ለሩቅ ፡ የነገር ፡ ስም ፡ የሚነገር ፡ ገቢር ፡ ቅጽልና ፡ ዐጸፋ ፤ ወይም ፡ በቂ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ለት ፡ ያን ፡ ነገር ፤ ቅጽል ። ያን ፡ ጥለሽ ፤ ያን ፡ ያሸላል ፤ ያን ፡ ውደድ ፤ ያን ፡ ጥላ ፤ በቂ ።

ዮናኤል ፤ የመልአክ ፡ ስም ፤ ርግበ ፡ አምላክ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ገድ ፡ ኪሮ) ።

ይንበርበሩ ፤—የሰው ፡ ስም ፤—በረ በረ ።

የነጂ ፤—የረኛ ፡ አበል ፤—ነዳ ።

ያኛው ፤ ኛው ፡ ዝርዝር ፡ ምእላድ ፡ ነው ፤ ጀኛውን ፡ ኛ ፡ እይ ።

ይፋ ፤ (ጋላ ፡ ኢፋ ፤ ብርሃን) ፤ ግልጥ ፡ ስውር ፡ ያይዶለ ፡ ነገር ። እከሌ ፡ በይፋ ፡ ተናገረ ፡ እንዲሉ ።

ይፋግ ፤ በበጌምድር ፡ ከቃሮዳ ፡ በታች ፡ ያለ ፡ አገር ።

የፊጥኝ ፤—የኋሊት ፤—ፈጠነ ።

ይፋት ፤ በሸዋ ፡ አውራጃ ፡ ያለ ፡ አገር ። በግእዝ ፡ ዊፋት ፡ ይባላል ፤ ባረብኛም ፡ (ወፋት) ፡ ሞት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

ይፋቶች ፤ የይፋት ፡ ሰዎች ፡ የይፋት ፡ ተወላጆች ።

ይፋቶ ፤ የገብስ ፡ ስም ፤ ይፋታዊ ፡ የይፋት ፡ ማለት ፡ ነው ።

የቅ ፤ የጭ ፡ ወዲያ ። ቀና ፡ ጨ ፡ ተወራራ ፑች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ የጭ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ የቅ ፡ ይላል ። ቂርቆስ ፡ ጨርቆስ ።

ዮቅጣን ፤ የሰው ፡ ስም ፤ የዔቦር ፡ ልጅ ። ዘሩ ፡ ቀጠነ ፡ ነው ። (፱፫፤ ፳፭—፳፱) ።

ይቆን ፤ የጋኔን ፡ ስም ፤ ደቂቀ ፡ ሴትን ፡ ያሳት ፡ ሰይጣን ፡ (ሔኖ፤፮ ፡ ፲፯) ።

(ጥተ) ይቅር ፤—ይተው ፤—ቀረ ።

ዮር ፤—ከፊለ ፡ ስም ፤—ዮርዳኖስ ።

የርቦራ ፤ የዝናን ፡ ጥርስ ፡ አንባር ፡ ጠላቱን ፡ ለገደለ ፡ የሚሰጥ ።

ያሬድ ፤ የሰው ፡ ስም ፤ ትርጓሜው ፡ መውረድ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ያሬድ ፤ ከዕለት ፡ እስካመት ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ድጓ ፡ የደረሰ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቅ ፡ ቅዱስ ፡ ካህን ።

ዮርዳኖስ ፤ የወንዝ ፡ ስም ፤ ከላይ ፡ ፫ ፡ ከታች ፤ ፮ ፡ የሸነ ፡ ዝማ ፡ ጌታችን ፡ የተጠመቀበት ፤ ትርጓሜው ፡ የዳን ፡ ወንዝ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

ዮር ፤ የዮርዳኖስ ፡ ከፊል ። በዮር ፡ በታቦር ፡ እንዲሉ ፡ መተርጉማን ።

የረር ፤ ካዲስ ፡ አበባ ፡ በስተደቡብ ፡ ያለ ፡ ተራራ ፤ በሐረርጌም ፡ የሚገኝ ፡ ቀበሌ ። ኤረርን ፡ እይ ።

የርሱ ፤ የሱ ፤—የዚያ ፤—ርስ ፡ እስ ።

የሺ ፤ የሴት ፡ ስም ፤ የሺመቤት ፡ ከፊል ። ሺን ፡ ተመልከት ።

ዮሽ ፤ የነገር ፡ ትራስ ። ብርቅዮሽ ፡ ሦስት ዮሽ ።

የሻላ ፤ የቀድሞ ፡ ማዕርግ ፡ ስም ፡ የሻለቃ ፡ ከፊል ፤ ባለግምጃ ፡ ሹሪ ።

የሻላ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፤ የጠራ ፡ ገሊላ ፡ ባላባት ።

የሻላ ፡ ጥሬ ፡ ወርቅ ፤ ዝኒ ፡ ከማሁ ፤ ፭ኛው ፡ ልጅ ፤ ፪ኛው ፡ አባት ።

የት ፤ (አይቴ) ፤ ንኡስ ፡ አገባብ ፤ የጥያቄ ፡ ቃል ፤ የቦታ ፡ በቂ ። ከአንቀጽ ፡ በፊት ፡ እየገባ ፡ ይነገራል ። የት ፡ አለኸ ፤ የት ፡ ባጅቭ ፤ የት ፡ ዋልኸ ፤ የት ፡ ከረምኸ ፤ የት ፡ ኼድኸ ፤ የት ፡ ዐደርኸ ፤ የት ፡ ሰንበትኸ ። መምህራንም ፡ በየት ፡ ፈንታ ፡ ሔት ፡ ይላሉ ። ደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ እንደ ፡ ከ ፡ ወደ፡ እስከ ፡ መነሻ ፡ ሲኾኑት ፤ እንዴት ፡ ከየት ፡ ወዴት ፡ እስከ ፡ የት ፡ ይላል ። በዝርዝርነት ፡ የስም ፡ ምትክ ፡ ሲኾን ፤ የቱ ፡ የትኛው ፡ ነው ፤ የትኞች ፡ ቹ ፡ የትኛዎች ፡ ቹ ፡ ናቸው ፤ የትኛዋ ፡ ይቱ ፡ ናት ፡ ይላል ። የየት ፡ ነኽ ፡ ቢል ፤ የየት ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ያሠኛል ፤ ቅጽል ነትንም ፡ ያሳያል ። (ተረት) ፤ አገርኽ ፡ የት ፡ ነው ፤ ማሪያም ፡ ውሃ ፤ እንግዲያውማ ፡ ዘመዴ ፡ ነኽ ።

የት ፡ እየለሌ ፤ እጅግ ፡ መራራትን ፡ ያስረዳል ። (ለሌ)ን ፡ ተመልከት ።

የት ፡ ውዬ ፡ የት ፡ ዐድር ፡ ብዬ ፤ የወፍ ፡ ጭኽትና ፡ ስም ። አዛፍ ፡ ላይ ፡ ብሠራ ፡ አሞራው ፡ መከራ ፤ አካብ ፡ ላይ ፡ ብሠራ ፡ እባቡ ፡ መከራ ፤ አምድር ፡ ላይ ፡ ብሠራ ፡ አረኛው ፡ መከራ ፡ የት ፡ ውዬ ፡ የት ፡ ዐድር ፡ ብዬ ፡ ትላለች ፡ ይላሉ ።

የትም ፤ ም ፡ ዋፄ ፡ ነው ። ፈጠን ፡ አይ ።

የትም ፡ የት ፤ የትም ፡ የት ፡ ቢኼዱ ፡ ከማ ዜር ፡ አያመልጡ ፡ (መዝ፸፬ ፡ ፯—፲ ። ዮና፩ ፡ ፩—፲፯ ። ፪ ፡ ፩) ።

ዬቱ ፤ (ዬት ፡ ዊት) ፤ የእንስት ፡ የሴት ፡ መለዮ ። ውን ፡ ዋን ፡ እይ ። አንደኛዬቱ ፡ ኹለተኛዬቱ ፤ ጠረቃዬቱ ፡ አህያዬቱ ፡ ጥጃዬቱ ፡ ፍሬዬቱ ፡ ዶርዬቱ ። በራብዕ ፡ በታምስ ፡ በሳብዕ ፡ በማይጠርስ ፡ ስም ፡ ግን ፡ ዬ ፡ ትጕረዳለች ። ላሚቱ ፡ በጊቱ ፡ እንዲሉ ። ዬ ፡ ፊደልን ፡ ኹሉ ፡ ግልስ ፡ ማድረጉን ፡ አስተውል ።

ያች ፤ (ይእቲ) ፤ የሩቅ ፡ ሴት ፡ ዐጸፋና ፡ ቅጽል ፡ ወይም ፡ በቂ ፤ እሷ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዋን ፡ እይ ። ያች ፡ ትምጣ ፡ ያች ፡ ትቅር ፤ ዐጸፋ ። ያች ፡ ሴት ፡ ያች ፡ ልጅ ፤ ቅጽል ። ው ፡ ሲጨመርበት ፡ መኖርን ፡ ያሳያል ።

ያችው ፤ ያቻት ። ው ፡ ቦታን ፡ ያስረዳል ።

ያችውና ፤ ው ፡ እንዳለፈው ፤ ና ፡ ናት ፤ አለች ። ማዶ ፡ ለማዶ ፡ በሩቅ ፡ ለምትታይ ፡ ሴት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ማመልከቻ ፡ ቃል ፡ ነው ።

ያችኛዋ ፤ ኛዋ ፡ ዝርዝር ፡ ምእላድ ፡ ነው ፤ ፪ኛውን ፡ ኛ ፡ እይ ።

ያቻት ፤ ያች ፡ ናት ፤ አለች ።

ያቻትና ፤ ያች ፡ እሷ ፤ ት ፡ ናት ፤ ና ፡ (ና ው) ፡ እንሆ ። በተገናኘ ፡ እንሆ ፡ እሷ ፡ ናት ፤ በሩቅ ፡ አለች ፡ ያሠኛል ።

ይች ፡ ቺ ፤ ይህችን ፡ ተመልከት ።

ይችው ፤ በቅርቡ ፡ አለች ።

ይችውና ፤ እንሆ ፡ እዚሁ ፡ አለች ።

ይተጌ ፤ (እኅተ ፡ ሐዌጌ) ፤ እተጌ ፤ ንጉሥ ፡ እቴ ፡ የሚላት ፡ ሚስቱ ፡ ጣምራው ፤ የንጉሥ ፡ ባልተ ፡ ቤት ። ይተጌ ፡ ጣይቱ ፡ ይተጌ ፡ መነን ፡ ይተጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ እንዲሉ ። ሲበዛ ፡ ይተጌዎች ፡ ይላል ።

ይቶት ፤ (እኅት) ፤ ሴት ፡ ስትመነኩስ ፡ የምትጠራበት ፡ ስም ፤ የፍቅር ፡ የሃይማኖት ፡ የማ



ይቶት ፡

ኅበር ፡ እት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዳግመኛም ፡ እመ ፡ እማሆይ ፡ ትባላለች ። በግእዝ ፡ ቋንቋም ፡ መነኩ

ሲቷ ፡ (እጎት) ፡ እት ፡ መነሡሲው ፡ (እጎው) ፡ ወን ድም ፡ ይባላሉ ። በብዙም ፡ ለመናገር ፡ (እጎው ፡ እጋት) ፡ ወንድሞች ፡ እቶች ፡ ያሠኛል ። ይቶት ፡ አለስም ፡ ብቻውን ፡ ሲነገር ፡ እንዳለፈው ፡ በቂ ፤ ከስም ፡ ጋራ ፡ ሲጸፍ ፡ ቅጽል ፡ ይኾናል ። (የታቦት ፡ ዘፈን) ፤ ያባ ፡ ጠጋባብ ፡ ልጅ ፡ የይቶት ፡ እዝጊያራ ፡ ትምሩኝ ፡ እንደኾን ፡ ልምጣ ፡ ወደ ፡ ኮራ ።

ከ

ከ ፤ ፲፩ኛ ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ አልፍ ፡ ቤት ፡ በአበገደ ፤ ይኸውም ፡ በተራ ፡ ቍጥር ፡ ነው ። በፊደልነት ፡ ስሙ ፡ ካፍ ፤ በአኃዝነት ፡ ከ—፳ ፡ (ካያ ፡ ኻያ) ፡ ይባላል ።

ከ ፤ የኀ ፡ ወራሽ ፤ ወይም ፡ ተለዋጭ ። ኀ ረደፈ ፤ ከረተፈ ። ቸን ፡ እይ ።

ከ ፤ የጐ ፡ ወራሽ ፡ ከግእዝ ፡ ወጻማርኛ ። በጉበጐ ፤ ቦከቦከ ።

ከ ፤ የቀ ፡ ወራሽ ። ቀላድ ፤ ከላድ ።

ከ ፤ ወቢይ ፡ አኀባብ ። ከበላ ፡ ብላ ፤ ከሰው ፡ አትጣላ ። ይህ ፡ ጋራን ፡ ይዞ ፡ ሲነገር ፡ ነው ። ኋላን ፡ ይዞ ፡ ሲፈታ ፤ ውሃ ፡ ከፈሰሰ ፡ አልታፈሠ ። ኽብ ፡ ካኰተኰተ ፡ ሰው ፡ ከተከተተ ። ከመነኰሰች ። ባሰች ፤ ከቈረበች ፡ አፈረሰች ።

ከ ፤ (ተ) ፤ ደቂቅ ፡ አኀባብ ። በስምና ፡ በግብር ፡ በነገርም ፡ ኹሉ ፡ በቦታም ፡ መነሻ ፡ ኹኖ ፡ አየኀባ ፡ በቁም ፡ ቀሪ ፡ ይኾናል ። (ማስረጃ) ፡ ከሰ ማይ ፡ ወረደ ። ከምድር ፡ ወጣ ። ነገር ፡ ከሥሩ ፤ ውሃ ፡ ከጥሩ ። ከከፉ ፡ ተወልጄ ፡ ስፈጭ ፡ ዐደርኩ ። ፍየል ፡ ከመድረሷ ፡ ቅጠል ፡ መበጠሷ ። ከቃጫ ፡ ወዲያ ፡ ገመድ ፤ ከናት ፡ ወዲያ ፡ ዘመድ ፡ (የለም) ።

ከ ፤ በ ፡ ይኾናል ። ከታዘዝኸበት ፡ አው ለኻቸው ፡ ጠላት ፡ በወሰዳቸው ። በቁም ፡ ቀሪና ፡ በ ፡ ሲኾን ፤ ከሞት ፡ የተረፉ ፡ ከጥላ ፡ ያረፉ ። ጋራን ፡ ይዞ ፡ ሲፈታ ፤ እንቅልፍ ፡ ታበዝ ፤ ከነብር ፡ ትፋ ዘዝ ። ወደ ፡ ሲኾን ፤ የተጠማ ፡ ከፈሳሽ ፤ የተበደለ ፡ ከነጋሽ ። ይልቅን ፡ ይዞ ፡ ሲፈታ ፤ ከመጠምጠም ፡ መማር ፡ ይቅደም ። ከተሻጋች ፡ ታራቂ ፤ ካጣቢ ፡ አድራቂ ። ከጂ ፡ በጉንጨ ። ካጨደ ፡ የሰበሰበ ፡ (ይሻላል) ። እስከ ፡ ድረስን ፡ ይዞ ፡ እንዲፈታ ፡ ከ ፡ በግልጥ ፡ ጋራን ፡ ይዞ ፡ ይፈታል ። ሔኖክ ፡ ከኤል ያስ ፡ ጋራ ፡ ይኖራል ። ሙሴ ፡ ከአሮን ፡ ጋራ ፡ ነበር ። ቂርቆስ ፡ ከናቱ ፡ ጋራ ፡ ሞተ ። በግእዝ ፡ መሠረቶቹ ፡ «እም ፡ እስከ ፡ ምስለ» ፡ ናቸው ። ኻያው ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ ነው ።

ኩ ፤ እኔ ፡ ለሚል ፡ የአንቀጽ ፡ ዝርዝር ። ግእዝ ፡ ጸሐፍኩ ፡ ያለውን ፡ ጻፍኹ ፡ በግለት ፡ ፈ ንታ ፡ ጻፍኩ ፡ ይባላል ። ኹን ፡ ተመልከት ።

ኪ ፤—ቸልታ ፤—ሲ ።

ክ ፤—ቸልታ ፤—ስ ።

ክ ፤ ለቅርብ ፡ ወንድ ፡ የአንቀጽ ፡ ዝርዝር ። ግእዝ ፡ ገደልከ ፡ ያለው ፡ ገደልኽ ፡ በመባል ፡ ፈ ንታ ፡ ገደልክ ፡ ተብሎ ፡ ይጻፋል ። ኽን ፡ እይ ።

ኳ ፡ አለ ፤—ድምጥ ፡ ሰጠ ፤—(ኳኳ) ።

ኩቤ ፤—ክንፍ ፡ አልባ ፡ ፌንጣ ፤ (ኰበኰበ) ።

ኩብ ፤—የፈትል ፡ ጥቅል ፤—ኮበ ።

ኳበ ፤ (ከዐበ) ፤ ደንጊያን ፡ በደንጊያ ፡ ጡብን ፡ በጡብ ፡ ዕንጨትን ፡ በንጨት ፡ ጓልን ፡ በጓል ፡ አሞሌን ፡ ባሞሌ ፡ ላይ ፡ ደረበ ፡ አስቀመጠ ፡ ቀጠለ ፡ አነባበረ ።

ኳበ ፤ አመሰገነ ፤ ብዙ ፡ ምስጋና ፡ ሰጠ ፡ ኰ ፈሰ ። እወደድ ፡ ባይ ፡ አሽከር ፡ ጌታውን ፡ ይክባል ።

ኳቢ ፡ (ዎች) ፤ ከዓቢ) ፤ የኳበ ፡ የሚ ክብ ፤ ኳብ ፡ ወዋቂ ።

ኳቢ ፤ ያገር ፡ ስም ፤ በዜጋመል ፡ ባሻገር ፡ ያለ ፡ ቀበሌ ።

ኳቢ ፤ (ከዐቢ) ፤ የቅርብ ፡ ሴት ፡ ትእ ዛዝ ፡ አንቀጽ ።

መኳብ ፤ መደረብ ፡ ማነባበር ፤ ማመስገን ፡ መኰፈስ ።

መኳቢያ ፤ መደረቢያ ፡ ማነባበሪያ ፤ ቁመት ፡ አርመን ።

ካኳበ ፤ ደራረበ ፡ ቀጣጠለ ።

መካኳብ ፤ መደራረብ ።

አስኳበ ፤ ኳቡ ፡ አለ ፤ አሠራ ፡ ኳብን ።

አስኳቢ ፤ ያስኳበ ፡ የሚያስኳብ ።

ማስኳብ ፤ ኳብ ፡ ማሠራት ።

ማስኳቢያ ፤ ትእዛዝ ፤ የቤት ፡ ዙሪያ ፡ ም ሽግ ።

ተኳበ ፤ (ተከዐበ) ፤ ተደረበ ፡ ተነባበረ ፡ ደንጊያ ፡ በደንጊያ ፡ ላይ ፡ ኾነ ።

ተኳበ ፤ የሰው ፡ ስም ።

ተኳበች ፤ የሴት ፡ ስም ።

ኳብ ፡ (ቦች) ፤ የተኳበ ፡ የተደረበ ፤ ድርብ ርብ ፡ ንብብር ፡ ደንጊያ ፡ (ኢሳ፳፪ ፡ ፱) ። ጥሬ ፡ ኳብ ፡ ዐፈር ፡ ቃም ፡ ኳብ ፡ እንዲሉ ። (እንቧይ ፡ ኳብ) ፤ የማይረባ ፡ የልጆች ፡ ሥራ ፡ ፈራሽ ።

ኳብ ፤ (ከዐብ) ፤ የቅርብ ፡ ወንድ ፡ ትእ ዛዝ ፡ አንቀጽ ።